# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን


## መጽሐፈ መዝሙር

### ቍጥር ፩

# Choir Songs

## Volume No. 1

## Ethiopian Orthodox Tewahedo Church




ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

**ፊደል አሳታሚ**
Feedel
P. O. Box 88-1332
Los Angeles, CA 90009
(323) 299-9845

January 2001
1st Edition

# ማውጫ


ሆሣዕና ........................................................ 6
ሆሣዕና በዓርያም ............................................. 6
ሆሣዕና በዓርያም ለወልደ ዳዊት ......................... 8
ለሃይማኖቴ እሞታለሁ ........................................ 9
ልቤ አቤት በል እንጂ ....................................... 10
ልዕልት እልሻለሁ ........................................... 11
ሐረገ ወይን .................................................. 12
ሕዝቤ ምን አድርጌህ ........................................ 12
ሕዝቦቿን ባርክላት ለኢትዮጵያ ........................ 13
መስክሪ ቀራንዮ ............................................. 14
መንገዴን አደራ ............................................. 15
መከሩ ደረሰ .................................................. 15
መዓትህ የራቀ ................................................ 16
ማነው የሚለየን ............................................. 17
ማርያም ተደሰቺ ........................................... 17
ማርያም እመቤቴ .......................................... 18
ማርያም ደስ ይበልሽ ...................................... 19
ማነው የሚለየን ............................................. 20
ሚካኤል አማላጅ ነው ...................................... 20
ምሥጋና እናቅርብ .......................................... 21
ምንኛ ታጋሽ ነህ ........................................... 22
ሰላም ለኪ ..................................................... 23
ሰላም ሰጊድ .................................................. 23
ሰላም የታቦር ተራራ ...................................... 25
ሰማይ ተከፈተ ............................................... 25
ሰዓቱ ደረሰ .................................................. 26
ስላደረክልኝ ምን ልመልስልህ ........................... 27
ቅድስተ ቅዱሳን ............................................ 28
በልዩ መንበሩ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ ................ 28
በሲያል ስላየው ............................................. 29

በአንድ ላይ እንሰብሰብና ............................................ 30
በኪነ ጥበብህ .......................................................... 30
በክርስቶስ መሞት ሕይወትን ያገኛችሁ............................ 31
በጉብዝናዬ ወራት ..................................................... 31
በጌቴ ሴማኔ ........................................................... 32
ባርከን ባርከን፤ ባርኪን ባርኪን ..................................... 33
አስምሪን እመ አምላክ ድንግል ወላዲቱ ........................... 34
ቤተልሔም ሆይ ........................................................ 34
ቤተ ክርስቲያን ........................................................ 35
ቤትክን ሥራ............................................................ 35
ቤዛዊት ዓለም ድንግል .................................................. 36
ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ .............................. 37
ተናገሩ እዝራ ተናገሩ .................................................. 38
ተው ተመለስ .......................................................... 39
ተዋህዶ ................................................................. 40
ተክለሃይማኖት......................................................... 40
ተገኘ በበረት .......................................................... 41
ትንሣኤ የጌታዬ ........................................................ 43
ቸሩ መድኃኔ ዓለም .................................................... 44
ችግራችን ይቃለላል .................................................... 44
ኃያል .................................................................... 45
ና ጌታ ሆይ ............................................................ 45
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ ................................................ 46
ንስሃ ..................................................................... 47
ንጉሥ ተወለደ .......................................................... 48
አልተወኝም ጌታ ይወደኛል............................................ 49
አመስግኑት አመስግኑት .............................................. 50
አማኑኤል ተመስገን................................................... 50
አምላክ ሆይ ታረቀን .................................................. 51
አምላክ በአንቺ አደረ ................................................ 52
አምላክ አለ መሃላችን ................................................ 53
አምላክ ወደደሽ....................................................... 53
አምላካችን ተመስገን................................................. 54
አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት .............................................. 55

ዐሥርቱ ቃላት ........................................................ 56
አትተወኝ ................................................................ 56
አንተ ስትናገር እኔ እንድሰማ ........................................ 57
አንድ ሁኑ ............................................................... 58
አካሄዴን ጠብቅ ......................................................... 58
እልል በይ ቤተልሔም .................................................. 59
እልፍ አዕላፋት ......................................................... 60
እመቤታችን ለአንቺ እናቀርባለን ምስጋና ......................... 60
እመቤቴ ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ............................... 61
እመአምላክ ሙሽራ .................................................... 62
እምነቴን አጠንክር ..................................................... 63
እምድንግል ተወልደ አማኑኤል ..................................... 64
እሰይ ተወለደ .......................................................... 65
እሰይ እሰይ ሞትን ድል አድርጐ ተነሣልን ......................... 66
እስኪ ላመስግንሽ ...................................................... 67
እስከመቼ ከፊትህ እሸሻለሁ። ........................................ 68
እናመስግነው .......................................................... 69
እኔስ ተስፋ አልቆርጥም እጽናናለሁ እንጂ ........................ 70
እንግልድሃለን .......................................................... 71
እንዘምር ሁላችን ....................................................... 71
እዝራ ተናገራ ........................................................... 72
ከእምነት አደባባይ ..................................................... 73
ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ ............................................ 74
ከክርስቶስ ፍቅር ....................................................... 75
ከደጅህ ቆሜ ............................................................ 75
ከዳዊት ዘር ............................................................. 76
ከዚህ ከጠፋው ዓለም ................................................... 77
ከፍጡራን በላይ ....................................................... 78
ኪዳነ ምህረት .......................................................... 78
ክርስቶስ ያንተ ሞት .................................................. 79
ወሮታህ ብዙ ነው፥ቀቀ ................................................. 80
ወደ ሕይወት ተመለስ .................................................. 81
ወደ አምላኬ ልመና .................................................... 82
ወዳንተ እሰግዳለሁ ..................................................... 82

ወዳንተ ኢየሱስ ሆይ .................................................. 83
ዘላዓለማዊ ቃልህ ...................................................... 83
ዛሬም እንደድሮው .................................................... 84
ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ ............................ 84
የልመናዬን ድምፅ ...................................................... 85
የመስቀሉ ነገር ......................................................... 86
የመስቀሉ ፍቅር ....................................................... 87
የማነ የማነ ............................................................. 88
የምሥራች ደስ ይበለን ............................................... 89
የሞት ላብ አላበው .................................................... 90
የሞት ኃይል ተዋርዶአል ዛሬ ........................................ 90
የራማው ልዑል ......................................................... 91
የሰው ልጅ ሁልጊዜ .................................................... 91
የቅዱሳን አምላክ....................................................... 92
የብርሃን መውጫ ....................................................... 93
የብርሃን እናት ......................................................... 93
የብርሃን ጎርፍ.......................................................... 94
የተለየች አገር.......................................................... 94
የኃያላን ኃያል ........................................................ 95
የኃያላን ኃያል ልዑል እግዚአብሔር ............................... 96
የነፍሳችን ቤዛ.......................................................... 97
የአማኑኤል እናት ..................................................... 97
የአምላክ እናት.......................................................... 98
የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ................................... 98
የአብርሃም አምላክ ................................................... 99
የእቲስ አንበሳ ....................................................... 100
የዓለምን በደል ....................................................... 102
የደናግል መመኪያ .................................................. 103
የጌታ እናት .......................................................... 104
የጌቶች ጌታ.......................................................... 105
የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው ........................................ 106
ይመስገን እግዚአብሔር ይመስገን ................................ 107
ይቅር በለን .......................................................... 107
ይትባረክ እንደ አብርሃም .......................................... 108

ድንግል ሆይ ........................................................ 109
ድንግል ሆይ እመቤቴ ማርያም .................................. 110
ድንግል መከራሽን .................................................... 111
ገዳመ ቆሮንቶስ ...................................................... 112
ጋሻውን ይዞ በፈረስ ................................................. 112
ጌታ ሆይ ............................................................ 113
ጌታ ሆይ ተመልከት ................................................ 114
ጌታ ተነስቶአል ...................................................... 115
ጌታ ተነስቷል በክብር ............................................. 115
ጌታ ተወለደ ......................................................... 116
ጌታ ይመጣል ......................................................... 117
ጌታችን ሲመጣ ...................................................... 118
ጌታችን ሲመጣ ...................................................... 118
ግነዩ ለእግዚአብሔር ................................................. 119
ጐልጐታ ............................................................. 120
ጐልማሳነቴን ደስ ወደ አሰኘት ..................................... 120
የጥምቀት መዝሙር .................................................. 121
ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ........................................... 122
ፍቅሩ አይለወጥም ................................................... 122
ፍጡራን ይስገዱ ...................................................... 123
ወረብ ................................................................. 124

## ሆሣዕና

ሆሣዕና ሆሣዕና ሆሣዕና (2 ጊዜ)
በጌታ ስም ሆኖ መጥቶልናልና፥ አዝማች
ብሩክ ወልደ ዳዊት ይድረሰው ምስጋና፡፡
ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት

ሆሣዕና ሆሣዕና ሆሣዕና (2 ጊዜ)
በመንፈስ ተውጠው በረቂቅ ሚስጥሩ፥
ሕፃናት ጠቢባን ድንጋዮች ሳይቀሩ፥
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ፡፡
ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት

ሆሣዕና ሆሣዕና ሆሣዕና (2 ጊዜ)
በአህያ ላይ ሆኖ የሠራዊት ጌታ፥
ገባ እየሩሳሌም በታላቅ ደስታ፥
ዘንባባውን ይዘን እንዘምር በእልልታ፡፡
ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት

ሆሣዕና ሆሣዕና ሆሣዕና (2 ጊዜ)
በጌታ ስም ሆኖ መጥቶልናልና፥
ብሩክ ወልደ ዳዊት ይድረሰው ምስጋና፡፡
ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት

## ሆሣዕና በዓርያም

ሆሣዕና በዓርያም ሆሣዕና
ሆሣዕና ብለን እናቅርብ ምሥጋና አዝማች

ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና
ለወልደ ዳዊት ሆሣዕና
ትሕትናን ያሳየን ሆሣዕና
ስሙ ይባረክ ሆሣዕና

አዝማች
    ሆሣዕና በሉ    ሆሣዕና
    ለሰማይ ንጉሥ    ሆሣዕና
    ግርማን ለብሶ መጣ    ሆሣዕና
    እኛን ሊቀድስ    ሆሣዕና
አዝማች
    ሆሣዕና በሉ    ሆሣዕና
    ለወልደ ዳዊት    ሆሣዕና
    ነቢያት በትንቢት    ሆሣዕና
    ለተናገሩለት    ሆሣዕና
    ሐዋርያት በወንጌል    ሆሣዕና
    ለሰበኩለት    ሆሣዕና
አዝማች
    ሆሣዕና በሉ    ሆሣዕና
    ለአምላከ ምሕረት    ሆሣዕና
    ተወልዶ ከድንግል    ሆሣዕና
    እንደ ሕፃናት    ሆሣዕና
    እረኞች በዋሻ    ሆሣዕና
    የሰገዱለት    ሆሣዕና
    የአዳም ልጆች ሁሉ    ሆሣዕና
    ደግሞም መላእክት    ሆሣዕና
አዝማች
    ቅድስት ሀገር ሆይ    ሆሣዕና
    ኢየሩሳሌም    ሆሣዕና
    ምስጋናሽ ብዙ ነው    ሆሣዕና
    በመላው ዓለም    ሆሣዕና
አዝማች
    በአህያ ላይ ሆኖ    ሆሣዕና
    ወደ አንቺ የገባው    ሆሣዕና
    ኢየሱስ ክርስቶስ    ሆሣዕና
    የዓለም መድኃኒት ነው    ሆሣዕና
አዝማች
    እናውቃለን ባዮች    ሆሣዕና

ግብዞች ሲቀሩ ሆሣዕና
ወጣት ሽማግሌው ሆሣዕና
ሕፃናትም ሆነው ሆሣዕና
በአንድ ላይ ዘመሩ ሆሣዕና
አዝማች
ሰውማ ቢዘምር ሆሣዕና
ምን ያስገርመናል ሆሣዕና
ሆሣዕና ሰው ቀርቶ ሆሣዕና
ድንጋይ ያናግራል ሆሣዕና
አዝማች

## ሆሣዕና በዓርያም ለወልደ ዳዊት

ሆሣዕና በዓርያም (3 ጊዜ)

እናቶች አባቶች ሕፃናት በሙሉ÷
ለዓለም መድኃኒት ሆሣዕና በሉ። (2 ጊዜ)
ሆሣዕና (3 ጊዜ) ለወልደ ዳዊት

በአህያዋ ጀርባ ጌታ ቁጭ አለና÷
አሳየው ለሕዝቡ ታላቁን ትህትና። (2 ጊዜ)
ሆሣዕና (3 ጊዜ) ለወልደ ዳዊት

ቤተ መቅደስ ገብቶ የሰላሙ ዳኛ÷
ይውጣ ብሎ አዘዘ ሌባና ቀማኛ። (2 ጊዜ)
ሆሣዕና (3 ጊዜ) ለወልደ ዳዊት

የሻጭና ለዋጭ ገበያ የነበርሽ÷
ዛሬ ቤተ መቅደሰ በአምላክ ነፃ ወጣሽ። (2 ጊዜ)
ሆሣዕና (3 ጊዜ) ለወልደ ዳዊት

## ለሃይማኖቴ እሞታለሁ

ለሃይማኖቴ እሞታለሁ፥ አዝማች
በክርስቶስ ታዝገፎአለሁ፡፡

አልሰቀቅም ለመከራ፥
አምላክ ሳለ ከኔ ጋራ፥
የአምላክን ፍቅር ማን ያስተወኛል፥
ስለኔ ተዋርዶ ስለኔ ሞቷል፡፡
በአንድ ሃይማኖት በእውነተኛይቱ፥
አምላክን አምኜ አልሸሽም ከፊቱ፡፡

አዝማች

አምላክን ያመነ ያለጥርጣሬ፥
ለገናናቱ የሚያቀርብ ዝማሬ፥
ፍፁም ደስተኛ ሆኖ እንደሚኖር፥
መሆኑን ተረድተን በሉ እንዘምር፡፡

አዝማች

እምነት ያለ ሥራ ሥራ ያለእምነት፥
ከንቱ ናት ብሎናል ያዕቆብ አባት፥
ይህንን ቃል አምነን ብለን እንለምን፥
ከቅዱስ መንፈስህ አምላክ አትለየን፡፡

አዝማች

ሳናውቅ በስህተት አውቀንም በድፍረት፥
ይቅር እንድትለን በሠራነው ኃጢአት፥
እንለምንሃለን የምሕረቱ ጌታ፥
ምን ጊዜም አለና ካንተ ዘንድ ይቅርታ፥
በዚህ በይቅርታህ እንድትጠብቀን፥
ወዳንተ እንጮሃለን ቅዱስ ቅዱስ እያልን፡፡

## ልቤ አቤት በል እንጂ

ልቤ አቤት በል እንጂ አምላኬ ሲጣራ፥
በሐዘን በለቅሶ ትካዜህን አውራ።
በደሌን አምኜ ይቅርታ ልጠይቅ፥
ሁሉን ቻይ ነህና ፍጥረትህን የማትንቅ።

አለቅሳለሁ ዘወትር አነባለሁ፥ (አዝማች)
አውቃለሁ አምላኬ ብዙ በድያለሁ።
ለቅሶና ጩኸቴን ተቀበለኝ፥
ጐስቋላ ሆኛለሁ ኃጢአት ያደከመኝ።

መንገድ ተላልፌ ፈጣሪ አስቀየምኩህ፥
በሚጠፉ ንብረት አምላኬ ለወጥሁህ።
አሁን ግን አምኜ ብዙ እንደበደልኩህ፥
በረከሰ አንደበት ይቅርታ ለመንኩህ።

አዝማች

የኃጢአት መረጃ ፌቴን ሸፍኖታል፥
ኃይሌ ከእኔ ርቆ መቆም ተስኖኛል።
ነሽና በፊቱ ክብር ሞገስ ያለሽ፥
ድንግል ልመናዬን አድርሺ ከልጅሽ።

አዝማች

ጉልበት አንተ ሁነኝ መተማመኛዬ፥
በደሌን አጥፋልኝ ሁን አስተማሪዬ።
ከበደል እንድርቅ እጅህን ዘርጋና፥
ዳግም እንዳልበድል አፅናኝ በምሥጋና።

አዝማች

## ልዕልት እልሻለሁ

ልዕልት እልሻለሁ እመቤቴ ማርያም፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ምህረት ለምኝልን ከላይ ከአርያም።
በክቡርነቱ የሌለው አምሳያ፥
የዘላለም ንጉሥ ኃያል በዓለም ዙሪያ።
ከማይለወጥ ከሚያኮራው ልጅሽ፥
አስታርቂን ድንግል ሆይ አማልጅን እባክሽ።
አዝማች
ለአንድነት ለፍቅር እንድንነሳሳ፥
ተባብረን እንድንቆም እንዳንሆን አንካሳ።
ሕይወታችን በዓለም ተጠምዶ እንዳይቀር፥
አሳስቢው እናቴ ውዳሴ ለቸር እግዚአብሔር።
አዝማች
በዓለም ውጣ ውረድ የሥጋ ፈተና፥
እንዳያሸንፈን የሰይጣን ሽንገላ።
ብሎ ከማይጥለን ሊቀ ካህናችን፥
ከልጅሽ ከኢየሱስ ምህረት ለምኝልን።
አዝማች
ልጅሽን ለማዳን ስደት ሲያንገላታሽ፥
ምንም ሳይታክትሽ ውሀ ጥም ሳይረታሽ።
ጌታን እንደሰወርሽው ከሄሮድስ ስደት፥
እኛንም ሰውሪን ከዘላለም ሞት።

## ሐረገ ወይን

ሐረገ ወይን (4 ጊዜ) እመ ብርሃን (2 ጊዜ) አዝማች
ሐረገ ወይን (4 ጊዜ) እመ ብርሃን (2 ጊዜ)

የፀጋ ሁሉ ምንጭ የሕይወቴ ተስፋ፥
እስቲ ላመስግንሽ ሳላፍር በይፋ፡፡
ምርኩዜ ልበልሽ ጥላ ከለላዬ፥
የእኔ መመከቻ እንቁዋ ጋሻዬ፡፡ ሐረገ ወይን፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
መልካሚቱ ሽቶ የሕሙማን ፈውስ፥
የአብ ቃል እናቱ ድንቅ እፀጳጦስ፥
መዓዛሽ ተስማሚ የሕይወት ምግብ፥
የቅንነት መዝገብ የሰላም ርግብ፡፡ ሐረገ ወይን፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
የአቤል መስዋዕት የዳዊት መዝሙር፥
የአሮን ክህነት ልብስ ፀአዳ ፀምር፥
የስደተኞች ቤት ማረፊያ ድንኳን፥
የልባችን ደስታ እመቤታችን፡፡ ሐረገ ወይን፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## ሕዝቤ ምን አድርጌህ

ሕዝቤ ኧረ ምን አድርጌህ ምን አጉድዬህ ነው፥ አዝማች
ሕዝቤ ምን ጠይቀህ ምን ከልክዬህ ነው፥
ከኔ የራቅኸው፥ የጠፋኸው?
ሕዝቤ ምን አድርጌህ ምን አጉድዬህ ነው?
እኔው ፈጠርኩህ በኔው አምሳያ ለምስጋና፥
አንተ ሳታውቀኝ እኔው አውቄህ እንደገና፥
በተድላ ደስታ በገነት ውስጥ ትኖር ነበር፥
ሕዝቤ ሰብረህ ወጣህ እንጂ የደጄን በር፡፡
በራስህ ፈቃድ ከምድር ወድቀህ አሳዘንከኝ፥
በመረረ ሐዘን ጩኸትህን አሰማኸኝ፡
ያንተንም ወንድም አስነስቼ ባለኝ ፍቅር፥
ሕዝቤ አውጥቼህ ነበር ከግፍ ምድር፡፡

ሕጌን ሰጠሁህ ትኖርበት ዘንድ አልቻልከው፥
እኔ እንዳዘዝኩት እንደፈቀድኩት አልሆንክም፡፡
በአንድያ ልጄ ሁሉን ትቼ አንተን ወደድኩ፥
ሕዝቤ የአንተን ሸክም እኔ ወሰድኩ፡፡
አንተ ግን እራቅህ ከፊቱም ይልቅ ገረመኝ፥
ሕዝቤ ተመለስ እስኪ ምን ላድርግ ንገረኝ፡፡
በልጄ ልሳን እንድትድን እመክራለሁ፥
ሕዝቤ የትዕግሥት ጊዜ ሰጥቻለሁ፡፡
ከዚህስ ወዲህ ከዚህስ ይበልጥ ምን ትሻለህ፥
የጐደለህን በእምነት ጠይቅ ታገኛለህ፡፡
አታሳዝነኝ ያሰብኩትን እኔ አውቃለሁ፥
ሕዝቤ ከኔ ጋር እንድትኖር ናፍቄያለሁ፡፡

## ሕዝቦቿን ባርክላት ለኢትዮጵያ

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ሕዝቦቿን ባርክላት ለኢትዮጵያ፡፡

በዘር በሃይማኖት እንዳይለያዩ፥
አንድነት ስጣቸው በፍቅር እንዲቆዩ፡፡
ምድር እንድትለመልም እንድትሆን ሰላም፥
ልጆቿን ባርክላት መድኃኔ ዓለም፡፡
አዝማች
እጆቿን ዘርግታ ቆማ ስትፀለይ፥
በረከት ላክላት ሆነህ በሰማይ፡፡
ትሰግድልሃለች ወገቧን አጥብቃ፥
ቆይታለች እስከ አሁን ማተቧን ጠብቃ፡፡
አዝማች
አትርሳት ጠዋት ማታ እጿ እንዳትከፋ፥
ጥላቻ ይወገድ ጦርነትን አጥፋ፡፡
በረድኤትህ ጉብኛት ረሃብ ይወገድ፥
በሽታና ችግር ይገታ መሰደድ፡፡
አዝማች

## መስክረ ቀራንዮ

መስክረ ቀራንዮ ንገሪን ኅልጎታ÷
ካሣ እንደሆነልን እንደ አዳነን ጌታ፡፡ አዝማች
በአምላክነቱ ፈጥሮ ዓለማትን÷
ሥጋን መዋሃዱን ሰዎችን ለማዳን÷
ክብሩን ዝቅ አድርጎ በታላቅ ትህትና÷
ሞትን ሊያጠፋልን የአየውን ፈተና፡፡
አዝማች
ለፍርድ ሲወስዱት ሲቀበል መከራ÷
መሰቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ÷
አይሁድ በየተራ ሲገርፉት ሲፀፉት÷
እንደታገሣቸው በፍጹም ቸርነት፡፡
አዝማች
ምንም ሳያጠፋ በደል ሳይኖርበት÷
በመስቀል እንዲሞት ቅጣት ተፈርዶበት÷
ወደኋላ ታስሮ ተገርፎ ተመትቶ÷
ያየውን መከራ የእሾህ አክሊል ደፍቶ፡፡
አዝማች
በሞቱ ሙታንን ከመቃብር ጠርቶ÷
በእርሱ ውርደት ክብርን ለሰው ልጆች ሰጥቶ÷
በሕይወት እንድንኖር ዳግም እንዳንሞት÷
ትንሣኤን መስበኩን በከበረች ሰንበት፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## መንገዴን አደራ

መንገዴን አደራ አደራ÷
መንገዴን አደራ አደራ÷
በእሳት ውስጥ ሳልፍ ጌታ ፍፁም እንዳልፈራ፡፡

ሕይወቴን አደራ አደራ÷
ሕይወቴን አደራ አደራ÷
በእሳት ውስጥ ሳልፍ ጌታ ፍፁም እንዳልፈራ፡፡

ጌታ ሆይ አደራ አደራ÷
ጌታ ሆይ አደራ አደራ÷
በምንሄድበት ሁሉ ጌታ ሁን ከኛ ጋራ፡፡

## መከሩ ደረሰ

መከሩ ደረሰ የመሰብሰቢያው÷ አዝማች
የተዘራው ፍሬ የመታጨጃ ያው፡፡ (2 ጊዜ)
ገበሬው ሊያበጥር መንሾ ይዞ ጋይዳ÷
ሰብሉን ሊሰበስብ እየተሰናዳ÷ (2 ጊዜ)
ሲወቃ መከሩ ሲለይ ግርድ ምርቱ÷
እንክርዳድ ከመሆን ያውጣን በምሕረቱ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ከመካከል ሆኖ በነፋስ ሲለየን÷
አምላኬ ሰውረኝ ገለባ ከመሆን ፡፡ (2 ጊዜ)
መንሹ ማንጠርጠሪያው መለያው ሲመጣ÷
አፍርተን እንጠብቅ መድረሻ እንዳናጣ፡፡
አዝማች
አልበላም አልጠጣም ደስታው ይቅርብኝ÷
እንክርዳድ ነው ብሎ ኋላ እንዳይለየኝ፡፡ (2 ጊዜ)
ነቅተን እንጠብቀው ይመጣል ድንገት÷
በደብረ ዘይት ቀን ኋላ በሰንበት፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

## መዓትህ የራቀ

መዓትህ የራቀ ምህረትህ የበዛ፥ አዝማች
የፍቅር አምላክ ነህ የዓለም ልጆች ቤዛ፡፡

የእግዚአብሔር ምዕመናን የአምላክ ልጆች ሁሉ፥
ወደ ጎን በመተው ሃላፊውን ሁሉ፥
በምድራዊ ጣጣ ሳትከፋፈሉ፥
እባክህ ጌታ ሆይ ፍቅር ስጠን በሉ፡፡
አዝማች
በወንጌል ተጽፎአል ምሳሌና ትምህርት፥
በመመካታቸው በአብርሃም ልጅነት፥
አይሁድ ተወቅሰዋል በልባቸው ትዕቢት፥
በዮሐንስ መጥምቅ በርቱዕ አንደበት፡፡
አዝማች
በረቀቀ ተንኮል በሠይጣን ፈተና፥
ወድቀን እንዳንቀር ኃይልን ስጠንና፥
አንተን በወለደች በድንግል ማርያም፥
እንማልድሃለን እንዲሰፍን ሰላም፡፡
አዝማች
አያልቅበት አምላክ ባለሙሉሥልጣን፥
ያስነሳል ከድንጋይ ለአብርሃም ልጅን፡፡
ለካስ በከንቱ ነው ልቤ መሸበሩ፥
የዕውነት ዳኛ ሳለ በሰማይ መንበሩ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

**ማነው የሚለየን**

**ማነው የሚለየን ከአዳኛችን ፍቅር÷**
**ኃዘን ነው ጭንቀት ወይስ ችግር?**
**ስደት መራቆት ሰይፍና እሥራት**
**ሊለዩን አይችሉም ከሱ ሕይወት።**

**ብፁዕ ነው እሱ የሚታገስ÷**
**ፈተናውን ሲያልፍ በመከራ÷**
**የሕይወትአክሊል ያወርሳልና÷**
**በእምነት ተጋደል የአምላክ ጭፍራ።**

**ሞት ቢሆን ሕይወት መለየት ኃይል÷**
**ኃላፊም ቢሆን ወይም መጪ÷**
**ከፍታም ዝቅታም ፍጥረታት ሁሉ÷**
**ሊለዩን አይችሉም ከፍቅሩ።**

**ጳውሎስ ቢወገር እስጢፋኖስ÷**
**ያዕቆብ ቢሰዋ ዮሐንስ÷**
**ድል ነስተው ሄዱ በሱ መንፈስ÷**
**የአዳም ልጅ በተስፋ እንገስግስ።**

**ማርያም ተደሰቺ**

**ሰላምታና ምሥጋና ይገባሻል ለአንቺ÷ አዝማች** (2 **ጊዜ**)
**ሁሌ ደስ ይበልሽ ማርያም ተደሰቺ።**

> **ብርሃንና ሰላም ያጐናፀፍሽን÷**
> **የዓለሙን ቤዛ ያሰገኘሽልን÷**
> **ለእኛ ለልጆችሽ ፍቅር እንዲሰጠን÷**
> **ከአንድያ ልጅሽ አማልጅን እኛን።**

**አዝማች**

ጌታ በአንቺ ማህፀን ዘጠኝ ወር አደረ፥
ክርስቶስ ታላቅ ነው እጅግ የከበረ፡፡
ለእርሱ እናቀርባለን ክብርና ምሥጋና፥
እንዲሰጠን ለእኛ ሰላምና ጤና፡፡
አዝማች
የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው፥
ዛሬም፥ ለዘለዓለም ምሥጋና የሚገባው፡፡
ማርያም ሆይ ደስታ ለአንቺ ሆኖልሻል፥
ዓለምን የሚዋጅ ፍሬ አፍርተሻል፡፡
አዝማች
ይድረስሽ ሰላምታ በክበሮ በእምቢልታ፥
የአማኑኤል እናት የታላቁ ጌታ፥
ከሴቶች ለይቶ አብ የመረጠሽ፥
ድንግል ማርያም ሆይ ብፅዕት አንቺ ነሽ፡፡
አዝማች

## ማርያም እመቤቴ

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት፥
ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት፥
ከሴቶች ሁሉ አንቺ ነሽ፥ አዝማች
የተባረክሽ የነፃሽ በእውነት፡፡
ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔ ዓለምን፥
ሰማይና ምድር የማይችሉትን፡፡
ለዚህ የተመረጥሽ ታላቋ እድለኛ፥
ምሕረትን ከልጅሽ ለምኚልን ለእኛ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ምንኛ ድንቅ ነው ምሕረቱ ለወልድ፥
የአንቺን ሥጋ ለብሶ ሲሆነን ዘመድ፡፡
ከዙፋኑ ወርዶ ያመሰገነሽ፥
የሕይወት ሙሽራ ማርያም አንቺ ነሽ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ÷
መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ÷
እኛም የአዳም ልጆች ከመሬት ሆነን÷
ሰዓሊለነ ቅድስት እንልሻለን፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት÷
የሰማዕታት አክሊል የፃድቃን እናት÷
የእኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ÷
ወልድን በመውለድሽ ኀዘናችን ጠፋ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

## ማርያም ደስ ይበልሽ

ማርያም ደስ ይበልሽ (2 ጊዜ) በገብርኤል ሰላምታ÷ አዝማች
ባንቺ ስላደረ (2 ጊዜ) የዓለም ሁሉ ጌታ፡፡

የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን÷ (2 ጊዜ)
ጨለማው ተገፎ ሲመጣ ብርሃን፡፡
አዝማች
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ÷ (2 ጊዜ)
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ፡፡
አዝማች
ገብርኤል ገብርኤል ዜናዊ ሐዲስ÷ (2 ጊዜ)
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ፡፡
አዝማች
በቤተ መቅደስም ተቀምጣ ድንግል÷ (2 ጊዜ)
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል፡፡
አዝማች
ገብርኤል ሲያበሥራት ድንግል ስትሰማ÷ (2 ጊዜ)
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ፡፡
አዝማች
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች÷ (2 ጊዜ)
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

### ማነው የሚለየን

ማነው የሚለየን ከአዳኛችን ፍቅር÷
ኃዘን ነው ጭንቀት ወይስ ችግር?
ስደት መራቆት ሰይፍና እሥራት
ሊለዩን አይችሉም ከሱ ሕይወት፡፡
ብፁዕ ነው እሱ የሚታገስ÷
ፈተናውን ሲያልፍ በመከራ÷
የሕይወትአክሊል ያወርሳልና÷
በእምነት ተጋደል የአምላክ ጭፍራ፡፡
ሞት ቢሆን ሕይወት መለየት ኃይል÷
ኃላፊም ቢሆን ወይም መጪ÷
ከፍታም ዝቅታም ፍጥረታት ሁሉ÷
ሊለዩን አይችሉም ከፍቅሩ፡፡
ጳውሎስ ቢወገር እስጢፋኖስ÷
ያዕቆብ ቢሰዋ ዮሐንስ÷
ድል ነስተው ሄዱ በሱ መንፈስ÷
የአዳም ልጅ በተስፋ እንገስግስ፡፡

### ሚካኤል አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል÷
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል÷
ተረዳአይ መልአክ ጠባቂ የእሥራኤል÷
የመላእክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል፡፡
አማላጅ ነው ሚካኤል (2 ጊዜ) የአምላክ ባለሟል÷ አዝማች
ለነሙሴ ለሕዝበ እሥራኤል፡፡
ፈረዖን በእሥራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ÷
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ÷
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና÷
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና፡፡
አዝማች
ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን÷
እጆቹን ዘረጋ ገሠፀው ባሕሩን÷
እንደ ግንብ ቆመ ባህረ ኤርትራ÷
በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ፡፡

አዝማች

በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት፥
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት፥
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት፥
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት፡፡

አዝማች

መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን፥
እንለንምንሃለን እንድትጠብቀን፥
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ፥
ዋስ ጠባቂ ሁነን ሚካኤል አደራ፡፡

አዝማች (3 ጊዜ)

## ምሥጋና እናቅርብ

ምሥጋና እናቅርብ ለጌታችን ለእግዚአብሔር፥ አዝማች
ክብር ለአምላካችን ሃሌሉያ እልል እንበል፡፡

በደስታ በእልልታ እንዘምርለት፥
እኛን ለአዳነን ከኃጢአት፡፡
ውዳሴና ክብር ለሱ ይሁን፥
ሁሉን ለፈጠረ ለዓለም መድኅን፡፡

አዝማች

ስለ ኃጢአታችን ለሞተልን፥
ስለ በደላችን ለተሰዋልን፥
በመገረፍ ቁስል ለፈወሰን፥
ከዘለዓለም ጥፋትም ላዳነን፡፡

አዝማች

## ምንኛ ታጋሽ ነህ

ምንኛ ታጋሽ ነህ የእኔ ጌታ፥
እንዲያ ሲያንገላቱህ በጐልጐታ፥ አዝማች
አሳየሃቸው ያንተን ትዕግሥት፥
ይቅር በላቸው በማለት፡፡

ስለሰዎች በደል ሆነህ ጥፋተኛ፥
ጌታዬ ተሰቀልህ እንደ ወንጀለኛ፥
መስቀል አሸክመው ሲያንገላቱህ፥
ክፉ አልወጣህም ከአንደበትህ፡፡

አዝማች

አምላኬ እንዴት ቻልከው ያን ሁሉ መከራ፥
ሲዘባበቱብህ ሁሉም በየተራ፥
ላብህ ሲንጠባጠብ በዚያ መልካም ፊትህ፥
ተገረፍህ ተሰቀልህ ብዙ ተንገላታህ፡፡

አዝማች

ትዝ እንኳ ሳትለኝ ፍጹም ሳላስብህ፥
እንዲህ ስበድልህ እንደምን ይግረምህ፡፡
እባክህ አስበኝ ምንም ብበድልህ፥
ምሕረትህን ላክልኝ እንደ ቸርነትህ፡፡

አዝማች

እንደ እኔ አይደለህም እሩኅሩኅ ጌታዬ፥
አሳልፈህ አትስጠኝ ለባላጋራዬ፡፡
እለምንሃለሁ ፊትህ ተንበርክኬ፥
ይቅር እንድትለኝ ላለፈው ስህተቴ፡፡

አዝማች

## ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን፥ አዝማች
ማርያም ውድስት የሕይወት ብርሃን፥
ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን።
ሰላም ልበልሽ ተንበርክኬ፥
ለብጽዕናሽ ተማርኬ፥
መርከበ ኖህ አዳራሽ፥
ሰላም ለኪ ልበልሽ።
አዝማች
ድንግል የአብርሃም ድንኳን፥
ሰላም ሰላም ሐረገ ወይን፥
ያዕቆብ ያየሽ መሰላል፥
የሰሎሞን ክብረ አክሊል።
አዝማች
ጽላተ ሙሴ የኦሪት፥
የአሮን በትር መድኃኒት፥
የዋህ ርግብ የያቄም፥
የነቢያት ተስፋ የአዳም።
አዝማች
እሳተ መለኮትን የያዝሽ፥
ምሉዕ አምላክን የወሰንሽ፥
ቤተ መቅደስ የልዑል፥
ሰላም ለኪ እመ ወድንግል።
አዝማች

## ሰላም ሰጊድ

በላከ ጊዜ ብዙ ጭፍራ፥
ሄሮድስ ርጉም ክፉ አሞራ፥
ዮሳ ቢነግርሽ ክፉ ዜና፥
ሁከት ትካዜ ገባሽና፥
በዚያ ጉዜ ከሰለሜ ላይ በትካዜ፥
ተቀብለኝ አለቀስሽለት ምርር ብለሽ፥
ተቀብለሽ አለቀስሽለት ምርር ብለሽ ሰላም ሰጊድ።

አንዳንድ ጊዜ ደስ አለሽ፥
የልጅሽን ተአምር እያየሽ።
በሚያልፍበቱ በመንገዱ፥
ግመሎች ቀሞው ባያስኬዱ፥
ዳግም ምድረ ግብፅ የገባ ለት፥
ታሮች ሁሉ ሲሰግዱለት፥
ያስቸገሩት አምስት ድንጋዮች ሆነው ቀሩ፥
ጌትነት የልጅሽ ሥራ ማስደሰቱ ሰላም ሰጊድ።
እኔ በነበርኩ በስደቱ፥
አዝነው ነበረ ስለእናቱ።
አልሆነም እንጂ በምኞት፥
የእግሩንም ትቢያ በላስኩት።
የአንቺ ልጅ ትሁት እንጅ፥
ነው ሰው ወዳጅ።
በናፍቆት ፍቅሩ ነደፈኝ እንደ ቀስት
በናፍቆት ፍቅሩ ነደፈኝ እንደ ቀስት ሰላም ሰጊድ።
በደስታ አውሪ ናዝሬት ሆይ፥
ንጉሥሽ መጣ ያ ፀሐይ።
ከነዙፋኑ ምቹ አልጋው፥
የግብፅን ሽፍቶች ድል አርገው፥
እሰይ ለኛ፥
በደህና ገባ የዓለም ዳኛ፥
የመከሩ የእርሱ ጠላቶች አፍረው ቀሩ፥
የመከሩ የእርሱ ጠላቶች አፍረው ቀሩ ሰላም ሰጊድ
ድንግል ማርያም ሆይ እመቤቴ፥
መንግሥተ ሰማይ ይሁን ቤቴ።
በኃጢአት ጭቃ ብለወስ፥
ቆሜ ከፊቱ ስወቀስ።
አንቺ አማልጅኝ አንቺ አማልጅኝ ከዓለም ንጉሥ
አንቺ አማልጅኝ አንቺ አማልጅኝ ከዓለም ንጉሥ ሰላም ሰጊድ።
ጻድቅሽ ባየሽ ተክለሃይማኖት፥
በአንድ እግሩ ቆሞ ሰባት ዓመት፥
ጻድቅሽ ባየሽ አብርሃም፥
እንግዳ ሳይዝ አይበላ፥

ኪዳነ ምህረት ሩኅሩህ÷
ተይ አታቁሚኝ ከበረ÷
የዲያብሎስ ፊቱ መራራ ነው አሉ÷
አንቺ አማልጅኝ እስቲ እስከ ሁሉ ሰላም ሰጊድ። (3 ጊዜ)

## ሰላም የታቦር ተራራ

ሰላም ሰላም (2 ጊዜ) የታቦር ተራራ÷ (አዝማች)
ብርሃነ መለኮት ባንቺ ላይ አበራ። (2 ጊዜ)

ሙሴና ኤልያስ እንዲያ ሲሸበሩ÷
ምነው አንቺ አልፈራሽ ምንድነው ምሥጢሩ።
አዝማች
ደቀ መዛሙርቱ ከርሱ ጋር የዋሉ÷
የአምላክን ድምፅ ሰምተው ለመጽናት አልቻሉም።
አዝማች
የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይበልሽ÷
አምላከ መለኮቱን ስለገለጠብሽ።
አዝማች

## ሰማይ ተከፈተ

በአምላካችን አንፃር እንጸልያን÷
በእግዚአብሔር ቅዱሳን በግርማ ተከበን። (2 ጊዜ)
ከሰማይ ተሰማ የመላእክት መዝሙር÷
የሰላም የደስታ የእውነት የፍቅር። (2 ጊዜ)

ሰማይ ተከፈተ ደስ ይበለን÷ አዝማች
ማኅሌት ተሰማ ደስ ይበለን÷
ዛሬ ተከበናል ደስ ይበለን÷
በመለኮት ግርማ ደስ ይበለን። (2 ጊዜ)
ደመና ከበበን ድንግል ተደሰተች÷
የሕዝቡን መመለስ ትመለከታለች። (2 ጊዜ)
ታላቅ ደስታ ነው በሰማይ ሠራዊት÷
ሠይጣን ድል ተነስቶ እኛ ስንባረክ። (2 ጊዜ)
አዝማች

ሰዎች እልል በሉ ልባችን ይታደስ፥
አምላክ ከእኛ ጋር ነው በልባችን ሊነግሥ። (2 ጊዜ)
ሰዎች እልል በሉ ልባችን ይታደስ፥
አምላከ ከእኛ ጋር ነው በልባችን ሊነግሥ። (2 ጊዜ)

## ሰዓቱ ደረሰ

ሰዓቱ ደረሰ ደረሰ፥
የጌታችን መምጫው ፈጠነ፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ከደጃችን በራፍ ያንኳኳል፥
ጌታ ክፈቱልኝ ይላል።
የስንቱ ልብ ይሆን አልከፈት ያለው፥
እስከዛሬ ድረስ ተዘግቶ የኖረው።
አንተ ግን ጌታዬ ትዕግሥትህ ብዙ ነው፥
እድሜን ለንስሐ መስጠትህ ድንቅ ነው።
አዝማች (1 ጊዜ)
እስከ አሁን ትዕግሥትህ ጌታዬ ደንቆኛል፥
አለማስተዋሌ በጣም ያሳዝናል።
ዛሬ ግን ተነሳሁ ሊከፈት ነው በሬ፥
እራት ልበላ ነው ከአንተ ጋር አብሬ።
አዝማች (1 ጊዜ)
እራት አቅርቤአለሁ ጌታ በናፍቆት፥
በል እንግዲህ ባርከኝ ዓይኔ ይመልከት።
ተመስገን አየሁት አምላኬ ጌታዬን፥
ባርኮ በመስጠቱ ሥጋውን ደሙን።
አዝማች (1 ጊዜ)
በቤት በጓዳዬ ጠፍቶ በረከቱ፥
አሁን ግን ተባረክሁ ጌታ ገብቶ ቤቴ።
ይህንን በረከት ገና ያላያችሁ፥
ጌታችን ያንኳኳል ይከፈት በራችሁ።
አዝማች (1 ጊዜ)
መብራታችሁ ይብራ ሙሽራው ተቃርቦአል፥
አይቀርም ጌታችን እመጣለሁ ብሎአል።
ብቻ ይህ ቀን አልፎ መብራቱ ሳይጠፋ
በፀጋህ አድነን አምላክ የእኛ ተስፋ።
አዝማች (2 ጊዜ)

## ስላደረክልኝ ምን ልመልስልህ

ስላደረክልኝ ምን ልመልስልህ፥ (አዝማች)
ብርሃን ላሳየኸኝ ከጨለማ አውጥተህ፥
ስብሐት ልበል እንጂ ለቅዱሱ ስምህ።

አምላኬ ስምህን ብጠራው ብጠራው፥
አልጠገብ አለኝ ምንኛ ጣፋጭ ነው።
አቤት ያንተስ ሥራ የአንተ ልግስና፥
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና።
አዝማች
ሰማይ ዙፋንህ ናት ምድርም መረገጫህ፥
በዚህ በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ፥
በሄድኩበት ሁሉ ትከተለኛለህ፥
ከእንቅፋት ድንጋይ ትጠብቀኛለህ።
አዝማች
ስለመልካም ሥራህ አለብኝ ውለታ፥
እማይነገረው የማዳን ስጦታ፥
ተመስገን ልበልህ ከጠዋት እስከ ማታ፥
ሌላ ምንም የለኝ የምከፍልህ ጌታ።
አዝማች
መልሴን እንዳዘጋጅ ቶሎ ሳልጠራ፥
አንደበቴ ሳለ ምስጋናህን ያውራ።
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር፥
እስከዘለዓለም ለስምህ ልዘምር።
አዘማች

## ቅድስተ ቅዱሳን

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል የእኛ ተስፋ፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ተሰደደች በግብፅ አምለኬን ታቅፋ፡፡ (2 ጊዜ)

መናን የመገበ ከሰማይ አውርዶ፥ (2 ጊዜ)
ተሰደደ በዓለም ለእኛ ሲል ተዋርዶ፡፡ (2 ጊዜ)
ለዚች ጥፉ ዓለም ምሕረቱን ሊፈጽም፥ (2 ጊዜ)
ተሰደደ አምላክ ተርቦ በግብፅ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

እፁብ ድንቅ ነው የፍቅሩ ጽናት፥ (2 ጊዜ)
ከዙፋኑ ወርዶ በዓለም መንከራተት፡፡ (2 ጊዜ)
የዓለሙ ቤዛ የዓለም መድኅን፥
ሰውን ከጥፋቱ ከጭንቅ የሚያድን፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የትሁት እረኛ የፃድቅ አባት፥ (2 ጊዜ)
ፍቅሩን ሊገልጽልን ሄደ በስደት፡፡ (2 ጊዜ)
የሰላም መገኛ የፍቅር ንጉሥ፥ (2 ጊዜ)
ተሰዶ ሲጠራ እንዴት ያስለቅስ፡፡ (2 ጊዜ)

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል የእኛ ተስፋ፥ (2 ጊዜ)
ተሰደደች በግብፅ አምላኬን ታቅፋ፡፡ (2 ጊዜ)
ተሰደደች በግብፅ አምለኬን ታቅፋ፡፡ (2 ጊዜ)

## በልዩ መንበሩ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ

በልዩ መንበሩ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ (2 ጊዜ) አዝማች
ማማሩ ማማሩ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ
ማማሩ ማማሩ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ

ቅድስት አፎምያን፥ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ
ከሠይጣን ያዳናት፥ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ
የጌታ ባለሟል፥ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ
የባህራን አባት፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ

አዝማች

| | |
|---|---|
| ከእዳረበናት÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| ሶስናን ያዳናት÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| ሚካኤል ሚካኤል÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| መልአከ ምሕረት። | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |

አዝማች

| | |
|---|---|
| በኃዘን በትካዜ÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| ያለነውን እኛን÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| አጽናናን አረጋጋን÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| ቅዱስ ሚካኤል÷ | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |
| አማላጃችን። | ቅዱስ ሚካኤል ማማሩ |

አዝማች

## በሲዖል ስላየው

በሲዖል ስላየው የአዳምን ጣጣ÷
አጥፍቶ ኃጢአትን የጽድቅን ባላንጣ÷
ራሱን ለውጦ ሊታረቀን መጣ። (2 ጊዜ)

አምስት ሺ ዓመታት ደግሞም ከአምስት መቶ÷
ወድቆ የኖረውን ከገሃነም ገብቶ÷
አዳምን አወጣው ከሲዖል ኀትቶ። (2 ጊዜ)

እስቲ ነቅቶ ይስማው ዕዝነ ልባችን÷
ጌታ በወንጌሉ ያስተማረውን። (2 ጊዜ)

የወንጌሉን ትዕዛዝ ሁሉን አውቃችሁ÷
በዓለም ስትኖሩ በሕይወታችሁ÷
ይቅርታን አድርጉ ለበደሏችሁ። (2 ጊዜ)

## በአንድ ላይ እንሰብሰብና

በወርቅ መቅረዞች የሚመላለስ፥
ሁሉን አፍቃሪ ኃያሉ ንጉሥ፥
ጨለማን ገፎ ብርሃን የሚያለብስ፥
ከቶ ማን አለ ያለ ክርስቶስ፡፡
በአንድ ላይ እንሰብሰብና፥
ለሞተልን አምላክ እናቅርብ ምሥጋና፥ አዝማች
ለተቤዠን አምላክ እናቅርብ ምሥጋና፥
ምሥጋና መሀሪ ነውና፡፡
የሰይጣን ሥራ ያፈራረሰው፥
ሞትን ለመሻር የተገለጸው፥
በደመና ክብር ሰማይ ያረገው፥
አዳኙ ንጉሥ አማኑኤል ነው፡፡
አዝማች

## በኪነ ጥበብህ

የአማልክት አምላክ ሁሉን የፈጠርከው፥ (2 ጊዜ)
ሕዝብህን አድነህ ርስትህን ባርከው፡፡ (2 ጊዜ)
በኪነ ጥበብህ ማንም በማያውቀው፥ (2 ጊዜ)
ፍቅረ ሠላም ይውረድ አንድነትን ስጠው ፡፡ (2 ጊዜ)
አንተ አንድ እንደሆንክ ካንዱ ካባትህ ጋር፥ (2 ጊዜ)
እኛንም አንድ አርገን አድለኸን ፍቅር፡፡ (2 ጊዜ)

የኃያላን ኃያል ማንም የማይረታህ፥ (2 ጊዜ)
ሰውረን ከክፉ አኑረን በቤትህ፥ (2 ጊዜ)
ከሠይጣን ፈተና እጅግ ከረቀቀው፥ (2 ጊዜ)
እባክህ ታደገን መልአክህን ላከው፡፡ (2 ጊዜ)

ከመሥዋዕት ይልቅ ምህረትን የወደድክ፥ (2 ጊዜ)
ንስሐ ገብተናል ልንሄድ ባንተ መንገድ፡፡ (2 ጊዜ)
ፍትሕ ገንዘብህ ነች አንተ የእውነት ዳኛ፥ (2 ጊዜ)
ተስፋችን ባንተ ነው በመልካሙ እረኛ፡፡ (2 ጊዜ)

## በክርስቶስ መሞት ሕይወትን ያገኛችሁ

በክርስቶስ መሞት ሕይወትን ያገኛችሁ÷
ምስጋና አቅርቡለት እድለኞች ናችሁ። አዝማች
አመስግኑት ጌታን ባንድነት ሆናችሁ÷
ዘምሩለት በጣም ለውድ ፈጣሪያችሁ።
ምስክርነታችሁ በዓለም ይወራ÷
ክርስቶስ ሁልጊዜ በናንተ ላይ ይብራ።
አዝማች
ቀናውን መንገድ ለሕዝብ አስተምሩ÷
በገሀነም እሰት ኋላ እንዳይማረሩ÷÷
ወገኖቼ ተጽናኑ በቃሉ ጠንክሩ÷
በሠይጣን ፈተና እንዳትበገሩ።
አዝማች
መንፈስ ይሙላባችሁ በፀሎት ብዛት÷
እንዳትዳከሙ በሠይጣን ክፋት።
ለወንጌል ታጠቁ በእውነት÷
በገነት ለመኖር በአዲስ ሕይወት።
በክርስቶስ መሞት ሕይወትን ያገኛችሁ÷
ምስጋና አቅርቡለት እድለኞች ናችሁ። (2 ጊዜ)
እድለኞች ናችሁ።

## በጉብዝናዬ ወራት

ክፉ ቀን ሳይመጣ ሳይደክም ጉልበቴ÷
ጐልማሳነቴ አልፎ ሳያልቅ ሰውነቴ÷
ጠላቴን ልዋጋ ጸንቼ በእምነቴ። (2 ጊዜ)
ደስ በሚያሰኝ ሰዓት በጉብዝናዬ ወራት÷ አዝማች (2 ጊዜ)
አንተን ላገልግል ጌታ ሆይ በሙላት÷
አንተን ላገልግል ጌታ ሆይ በሙላት።
ታማኝ ሎሌህ ልሁን አንተን የማስከብር÷
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስምህን የማከብር÷
ከጠላት መንጋ ውስጥ ለአንተ የምመሰክር። (2 ጊዜ)
አዝማች

ቃልህን ልመስክር ለአሕዛብ ሁሉ÷
መንገዱ ጠፍቶአቸው ለሚንገዋለሉ÷
ከግንዱ ተቆርጠው በግፍ ከሚጣሉ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የእስከ አሁኑን ገድል በስምህ ታግሼ÷
የዓለምን እሩጫ በሕግህ ጨርሼ÷
ለአክሊልህ አብቃኝ አምላክ አለኝታዬ፡፡ (2 ጊዜ)

### በጌቴ ሴማኔ

በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ (2 ጊዜ)
ለእኛ ሲልጌታችን በዓለም ተንገላታ፡፡ (2 ጊዜ)
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት (2 ጊዜ)
ለእኛ ነበረብን የዘለዓለም ሞት፡፡ (2 ጊዜ)
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ (2 ጊዜ)
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ፡፡ (2 ጊዜ)
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው (2 ጊዜ)
እንዲህ ሲል ፀለየ አምላክ ሆይ ማራቸው፡፡ (2 ጊዜ)
ተጠማሁ ተጠማሁ ተጠማሁ ሲላቸው (2 ጊዜ)
ኮምጣጤ አመጠሉተ ከሃሞት ቀላቅለው፡፡ (2 ጊዜ)
ድንግል አልቻለችም ዕንባዋን ልትገታ (2 ጊዜ)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ፡፡ (2 ጊዜ)
በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ (2 ጊዜ)
በሰው እጅ ተገርፎ ሞተ ተቀበረ፡፡ (2 ጊዜ)

## ባርከን ባርከን፤ ባርኪን ባርኪን

ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን (2 ጊዜ)
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሃሳብ አድርገን። (2 ጊዜ)
ኧኸ
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሃሰብ አድርገን። (2 ጊዜ)

ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን(2 ጊዜ)
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሃሳብ አድርጊን። (2 ጊዜ)
ኧኸ
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን። (2 ጊዜ)

ጥሪህን ስንሰማ ወደ አንተ እንድንመጣ
በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ላንወጣ
በሕይውት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም
እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔ ዓለም።
ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን (2 ጊዜ)
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሃሰብ አድርገን። (2 ጊዜ)
ከተፈረደብን የባርነት ሕይወት
ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት
ከሲያል እሥራት እኛ የዳንንብሽ
ድንግል ሆይ ምን ጊዜም አይለየን ምልጃሽ።
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን(2 ጊዜ)
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሃሳብ አድርጊን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን
አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን
በምግባር ስንደክም ሲጐድል እምነታችን
በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ
በምህረትህ ጐብኘን አንተ ሁነን ተስፋ።
ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን (2 ጊዜ)
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሃሳብ አድርገን። (2 ጊዜ)
ርኅርኅተ ኅሊና ቅድስት እናታችን
አሳስቢ ሁልጊዜ ስለኃጢአታችን
ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ

አስምሪን እመ አምላክ ድንግል ወላዲቱ
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን(2 ጊዜ)
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሃሳብ አድርጊን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን።
ኧኸ
ድንግድ ሆይ በምልጃሽ አንድ ሃሳብ አድርጊን።
ድንግድ ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አሰታውቂን።

**ቤተልሔም ሆይ**

በምድረ ኤፍራታ በቤተልሔም፥ (2 ጊዜ) አዝማች
አምላክ ተወለደ መድኃኔ ዓለም። (2 ጊዜ)

ቤተልሔም ሆይ በጣም ደስ ይበልሽ፥ (2 ጊዜ)
ከይሁዳ ምድር ፍጹም ስለማታንሺ። (2 ጊዜ)
የዓለም መድኃኒት ወልደ አብ ዋህድ፥ (2 ጊዜ)
በአንቺ ላይ ተወልዶ አደረገን ዘመድ። (2 ጊዜ)
ካህናት ሁል ጊዜ አንቺን ያነሳሉ፥ (2 ጊዜ)
ኦ ቤተልሔም ተፈስሂ እያሉ። (2 ጊዜ)
አዝማች
ቤተልሔም የዳዊት አገር፥ (2 ጊዜ)
የሰላም መግለጫ የብርሃን አጀብ። (2 ጊዜ)
በአንቺ ላይ ሲገለጽ የልደት ምስጢር፥ (2 ጊዜ)
ሰውና መላእክት እንስሳት ጭምር። (2 ጊዜ)
ስብሐት ወሰማያት ወሰላም በምድር፥ (2 ጊዜ)
እያሉ ዘመሩ በመተባበር። (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)

## ቤተ ክርስቲያን

ወንሰኢ ኃይለ (4 ጊዜ) ቤተ ክርስቲያን፡፡
ቤተ ክርስቲያን በእውነት አንቺ ነሽ ክብራችን÷ (2 ጊዜ)
የምትመግቢን (4 ጊዜ) የምትሰጭን ሥጋውን ደሙን፡፡

ተቀድሲ ወንሰኢ ኃይለ÷ (2 ጊዜ) አዝማች
ወንሰኢ ኃይለ (4 ጊዜ) ቤተ ክርስቲያን፡፡

ለዘለዓለም ኑሪ (2 ጊዜ) ተዋህዶ÷ (2 ጊዜ)
በጸሎትሽ ኃይል (4 ጊዜ) በጸሎትሽ ዲያብሎስ ተወግዶ፡፡
አዝማች
ጨለማው ርቆ ብርሃን እንዲሆን÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
መድኃኔ ዓለም (4 ጊዜ) መድኃኔ ዓለም ፈቃድህ ይሁን፡፡
አዝማች
ከጥፋት ጠቃት (2 ጊዜ) ኢትዮጵያን÷ (2 ጊዜ)
ፈጥነህ አርቅልን (4 ጊዜ አርቅልን መንፈስ ርኩስን፡፡
አዝማች
ቤተ ክርስቲያን ክብርሽ ተገለጸ ደመቀልን÷ (2 ጊዜ)
በሠራዊት ጌታ (4 ጊዜ ) በክርስቶስ በአምላከ ብርሃን፡፡
አዝማች

## ቤትክን ሥራ

እግዚአብሔር ሆይ ቤትክን ሥራ አንተው አሰማምረው÷ አዝማች
የሰው ልጆች ሃሣብ ብቻውን ከንቱ ነው፡፡ (2 ጊዜ)

ብንወጣ ብንወርድ አንተ የሌለህበት
እጅግም ብንፈጥን ብንወጣ አቀበት
ጌታ ካልረዳኸን ቋቱ ጠብ አይልበት
ባዶ መባከን ነው በከንቱ መታከት፡፡
አዝማች

አንተ ካለህበት ነገሩ ሁሉ ይሰማራል
ጉቶ ተነቃቅሎ ለጥ ያለ ይሆናል
ተራራ አቀበቱ ፈርሶ ይቃለላል
ጌታ ከኛ ጋርሁን ማን ይቃወመናል።
አዝማች
ስለዚህ አምላክ ሆይ በአገልግሎታችን
አንተን እንከተል ቅደም ከፊታችን
ጌታ ካለህበት ይሣካል ጉዞአችን
የሠራዊት አምላክ ንገሥ በልባችን።
አዝማች

## ቤዛዊት ዓለም ድንግል

ቤዛዊት ዓለም ድንግል እመብርሃን ድንግል፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ምስጋና ለአንቺ ይገባል።

የልባችን ተስፋ የቅዱሳን ሃብት፥ (2 ጊዜ)
የብርሃን እናት (2 ጊዜ) አንቺ ነሽ በውነት።
ብርሃነ መለኮት የፀለለብሽ፥ (2 ጊዜ)
የጥበብ መገኛ (2 ጊዜ) ድንግል አንቺ ነሽ።
አዝማች (2 ጊዜ)
አንቺን መርጦ ለአንቺ ስለአደለሽ ክብርን፥ (2 ጊዜ)
የኃጢአት ቀንበር (2 ጊዜ) እኛ ቀለለልን።
እመ አምላክ ማርያም ምንኛ ከበርሽ
ከአዳም ልጆች ሁሉ (2 ጊዜ) አንቺ ተመረጥሽ። (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)
የሠራዊት ጌታ የመለኮት ኃይል፥ (2 ጊዜ)
ከአንቺ ተገለፀ (2 ጊዜ) ማርያም ድንግል።
የክርስቶስ እናት ምስጋና ይገባሻል፥ (2 ጊዜ)
ከሴቶች መካከል (2 ጊዜ) ባንቺ አድሮብሻል።
አዝማች (2 ጊዜ)
ንፅሕት ንፁሐን ቅድስተ ቅዱሳን፥ (2 ጊዜ)
የልጅሽ ይቅርታ (2 ጊዜ) ከእኛ እንዳይለየን
ችግር እንዳይገጥመን በላይኛው ቦታ፥ (2 ጊዜ)
ቃል ኪዳንሽ ለእኛ (2 ጊዜ) ይሁነን መከታ።
አዝማች (2 ጊዜ)

## ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ

ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ (2 ጊዜ)
የአምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ ዕርቅ
ደስ ይበለን በትንሣኤው ብርሃን አዝማች
እልል እንበል በአንድነት ሆነን
ተነሣልን መድኃኒታችን

ከፊት ለፊት በመሳሉ የመስቀሉ ነገር
የሚወደው ሐዋርያው የወንጌል መምህር
ዮሐንስ ስቅለቱን በማየቱ
አለቀሰ እስከዕለተ ሞቱ
ሲያሰቅቀው ሞቱ ግርፋቱ።

ሞኝነት ነው ለሚጠፉት መስናከያቸው
በዓለም ጥበብ ለሚኖሩ ዕውነት ተስኖአቸው
ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖረወ
የመዳን ቀን ዕውነተኛ ዓርማ ነው
ከገሀነም እሳት የሚያድነው።

አዝማች

እስከ መሞት ላልተለየው ቅዱሰ ሐዋርያ
ለዮሐንስ ለወንጌል ሰው የፍቅር ባለሙያ
ምስጋናችን ከምድር ይድረሰው
እንድናለን በሰጠን ምሳሌው
ሰዎች ሁሉ እንከተለው።

አዝማች (2 ጊዜ)

## ተናገራ እዝራ ተናገራ

ተናገራ እዝራ ተናገራ ዳዊት ዘመራ፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ተናገራ ያሬድ በመዝሙሩ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ የዘመረልሽ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ኤፍሬም በውዳሴው፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ያመሰገነሽ፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች
ተናገራ የመለኮት ዙፋን፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ የዓለም እናት፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ለምኚልን ለእኛ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ኪዳነ ምሕረት፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች
ተናገራ አምላክ በነቢያት፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ስለአንቺ ነገረን፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ይህች ለዘለዓለም፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ማረፊያ ናት አላት፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች
ተናገራ እሙ ለጸሐይ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ የሁላችን ተስፋ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ በማሕፀንሽ ፍሬ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ኃዘናችን ጠፋ፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች
ተናገራ የአብ ሙሽራው፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ለወልድ ወላዲቱ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ለመንፈስ ቅዱስ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ማረፊያ ነሽ ቤቱ፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች
ተናገራ እዝራ በመሰንቆ፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ እያጫወታት፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ሳታውቀው አለፈች፥ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ያን መላከ ሞት፥ ዳዊት ዘመራ
አዝማች

ተናገራ ዉሆች ቀለም ሆነው÷ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ እንጨቶች ብዕር÷ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ ቢጽፉት አያልቅም÷ ዳዊት ዘመራ
ተናገራ የማርያም ክብር÷ ዳዊት ዘመራ
አዝማች

## ተው ተመለስ

ተው ተመለስ ወገኔ ተው ተመለስ÷ (2 ጊዜ) አዝማች
መንገዱን ያዝ÷ መንገዱን ያዝ ጌታ ሳይመለስ፡፡ (2 ጊዜ)

ዋ ዘመዴ በዓለም ስትባክን÷
ሕይወት መስሎህ ስታስት ሞትን፤
ካለህበት የጨለማ ሕይወት |
ተው ተመለስ ሳትሸነፍ በሞት፡፡ | (2 ጊዜ)
አዝማች
ጌታ ከአለህ መንገድ ሕይወት÷
ጥሎ የማይጥል መሐሪ አባት÷
ተው ተመለስ ልብህን አስገዛ÷ | (2 ጊዜ)
እሺ በለው ይጠራሃል ጌታ፡፡ |
አዝማች
ሳትጠየቅ በፍርድ ቀን÷
ሳትሰቃይ በሰቀቀን÷
እንደዋዛ ቀኗ ሳትረታ÷ | (2 ጊዜ)
ተው ተመለስ ኋላ እንዳትገታ፡፡ |
አዝማች
ዛሬ ከየት መጣህ የማይልህ÷
ጌታ ማረኝ ብለህ ከጠየቅህ÷
የማይተውህ ነውና እግዚአብሔር÷
ሁሉም ያልፋል ከማያልፈው ጋር ኑር፡፡
አዝማች

### ተዋህዶ

ተዋህዶ ተዋህዶ ሰማያዊ፥
የጻናች እምነት የጻናች እምነት ሃሌሉያ፡፡
ተዋህዶ ተዋህዶ መንፈሳዊ፥
የመንፈስ መብራት የመንፈስ መብራት ሃሌ ሉያ፡፡
ተዋህዶ ተዋህዶ መለኮት፥
ንጽሕት እምነት ንጽሕት እምነት ሃሌ ሉያ፡፡
ባንቺ ቢያምኑ ባንቺ ቢያምኑ ቅዱሳን፥
ድል ነሱ ሠይጣንን ድል ነሱ ሠይጣንን ሃሌ ሉያ፡፡
ባንቺ ቢያምኑ ባንቺ ቢያምኑ ሰማዕታት፥
ተፈተኑ በእሳት ተፈተኑ በእሳት ሃሌ ሉያ፡፡
እንደ ወርቅ እንደ ወርቅ ተፈትነው፥
አበራ ገድላቸው አበራ ገድላቸው ሃሌ ሉያ፡፡
እንኑር እንኑር በእምነታችን፥
በተዋህዶ መክበሪያችን በተዋህዶ መክበሪያችን ሃሌ ሉያ፡፡

### ተክለሃይማኖት

ተክለሃይማኖት ፀሐይ የኢትዮጵያ ሲሣይ፥ አዝማች
ምዕራፈ ቅዱሳን (2 ጊዜ) በነፍስ በሥጋም አትርሳን፡፡

የቅዱሳን አርዕስት የዋሻው ብርሃን፥
የፀሎት ባለቤት የነዳያን መድኅን፥
ገና ሳትወለድ አምላክ የመረጠህ፥
የድውያንሕመም ፈዋሹ አንተ ነህ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ገና በሦስት ቀን በሕፃንነትህ፥
ጌታን አወደሰው ቅዱሱ አንደበትህ፥
ቀድሞም እግዚአብሔር አስቦሃልና፥
በወጣትነትህ ወጣህ ለምነና፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

ሌትና ቀን ሳትመርጥ ክረምትና በጋ፥
ስትፀልይ ውለህ ስትፀልይ አነጋህ፡፡
በመቆምህ ብዛት አንድ እግርህ ቢነሣ፥
ፀሎትህን ፈጸምክ ለሥጋህ ሳትሣሣ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ምንኛ ድንቅ ነው ቅዱስ የአንተ ብርታት፥
ሰባት ዓመት ሙሉ በአንድ እግርህ ፀሎት፥
የዓለም ግሣንግሷ ሃብቷ ሳይስብህ፥
ለኢትዮጵያ ፀለይክ ቆመህ በአንድ እግርህ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የሃይማኖት ተክል የኢትዮጵያ አባት፥
ምሕረትን ከአምላክ ለአገርህ አሰጣት፡፡
እኛንም አግዘን በቅን እንድንሠራ፥
በተሰጠህ ሥልጣን ጠብቀን አደራ፡፡ (2 ጊዜ)

## ተገኘ በበረት

ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ፥ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ተገኘ በበረት እራሱን አዋርዶ፡፡

| | |
|---|---|
| የነገሥታት ንጉሥ | ተገኘ በበረት |
| ቤዛ ኩሉ ዓለም | ተገኘ በበረት |
| መድኀን ተወለደ | ተገኘ በበረት |
| በቤተልሄም | ተገኘ በበረት |
| አራቀልን ከእኛ | ተገኘ በበረት |
| ቁጣን በትግዕሥቱ | ተገኘ በበረት |
| ታላቅ ነው ከሁሉ | ተገኘ በበረት |
| የጌታ ልደቱ | ተገኘ በበረት |

አዝማች (2 ጊዜ)

| | |
|---|---|
| ለቅዱሳን ክብር | ተገኘ በበረት |
| ፀጋ ሊያለብሳቸው | ተገኘ በበረት |
| መጣ ወልደ አምላክ | ተገኘ በበረት |
| በመካከላቸው | ተገኘ በበረት |

የጠፋው አዳምን ተገኘ በበረት
ከቦታው መልሶ ተገኘ በበረት
የተገፈፈውን ተገኘ በበረት
ፀጋውን አልብሶ ተገኘ በበረት
ፀጋውን አልብሶ ተገኘ በበረት
በበረት ተገኘ ተገኘ በበረት
ቡራኬ ቀድሶ ተገኘ በበረት
አዝማች (2 ጊዜ)
የጠፋው አዳምን ተገኘ በበረት
ከውድቀት ያነሳ ተገኘ በበረት
ተገኘ አምላካችን ተገኘ በበረት
ከቤተ እንስሳ ተገኘ በበረት
መላእክት መጡ ተገኘ በበረት
እረኞች ዘመሩ ተገኘ በበረት
የአጋንንት ሠራዊት ተገኘ በበረት
በሙሉ አፈሩ ተገኘ በበረት
አዝማች (2 ጊዜ)
ከልዑል መንበሩ ተገኘ በበረት
ከዙፋኑ ወርዶ ተገኘ በበረት
ትህትናን ሰበከ ተገኘ በበረት
በበረት ተወልዶ ተገኘ በበረት
ጽድቅን አበሰረ ተገኘ በበረት
ሠይጣን ድል ተነሳ ተገኘ በበረት
መርገምም ተሻረ ተገኘ በበረት
ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ፥ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ተገኘ በበረት እራሱን አዋርዶ
ተገኘ በበረት እራሱን አዋርዶ። (4 ጊዜ)

## ትንሣኤ የጌታዬ

አሸክመው መስቀል ገርፈውት፥
ይዘብቱ ጀመር ቸንክረው፥ ሰቅለውት፥
ሙታንም መስሎአቸው ቀበሩና፥
ድንጋይ ክብካብ ሠርተው ዘብ አቁመው፥ ጠበቁና፥
መች አገኙት ክርስቶስ ተነስቶአልና። (2 ጊዜ)
ትንሣኤ የጌታዬ (2 ጊዜ)
ክርስቶስ ድል አደረገ፥
መቃብር ጥሶ አረገ።
ተስፋ አለበሰን በጐልጐታ፥
ተነሳ ተነሳ ሞትም ተረታ። (2 ጊዜ)
ትንሣኤ የጌታዬ (2 ጊዜ)
የሰዱቃውያን ሃሰብ ከሸፈ፥
እውነትና ሕይወት አሸነፈ፤
የፈሪሳውያን ሕግ ፈረሰ፤
ሲያል ጨለማው ተበዘበዘ።
እምቢልታ፥ መለከት ይጐሰም ነጋሪት፥
ለሚጠፉ ዋይታ ለሚድኑ ደስታ።
ትንሣኤ የጌታዬ (2 ጊዜ)
ቅድመ ሐዲስ እባብ ይነሣ፥
ብሉይ ዘመናት ነፃነት ንሣ።
ቀጠቀጠልን አፈሩን ቀምሶ፥
መድኃኒታችን ገሥግሶ።
በዓል ፋሲካ ትንሣኤ፥ የእግዚአብሔር ወልድ፥
የአዳም ዘር ፍታት አርነት፥ ነፃ መንገድ።
ትንሣኤ የጌታዬ (3 ጊዜ)

## ቸሩ መድኃኔ ዓለም

ቸሩ መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)÷ ምስጋና ይገባሃል (2 ጊዜ)
እኛን ድውዮችን አንተ ፈውሰሃል፡፡ (2 ጊዜ)
ቸሩ መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)÷ ምስጋና ይገባሃል (2 ጊዜ)
እኛን ሕግ አፍራሾች በንስሃ አጥበሃል፡፡ (2 ጊዜ)
ቸሩ መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)÷ ምስጋና ይገባሃል (2 ጊዜ)
በብርሃን መስቀልህ ጠላት ድል ነስተሃል፡፡
ቸሩ መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)÷ ምስጋና ይገባሃል (2 ጊዜ)
ለብዙ ውለታህ ምን ይከፈልሃል፡፡
ቸሩ መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)÷ ምስጋና ይገባሃል (2 ጊዜ)

## ችግራችን ይቃለላል

ችግራችን ይቃለላል ኃዘናችንም ይጠፋል÷ አዝማች
ጌታችን ይጠብቀናል በክንፉ ሥር ያኖረናል፡፡

የዓለም ኑሮ ያስመረረን መከራ ሲከማችብን÷
ልቦናችን ሲያዝንብን ኢየሱስ ነው መከታችን፡፡
አዝማች
ሰይጣን እንዳንበሳ መስሎ ዘወትር በኛ ላይ ሲያገሳ÷
ዓለም እራሷ ስትንቀን መግቢያ መውጫ ስታሳጣን÷
ጌታችን አለኝታችን ነው የዘወትር ጠባቂያችን÷
ኃይልን ሰጥቶ የሚያቆየን ለመንግሥቱ የሚያበቃን፡፡
አዝማች
ክርስቲያኖች እንጠንክር ያለም ነገር ቶሎ ያልፋል÷
ጊዜያዊ ነው ሁሉም ነገር በሰይጣን ኃይል አንታለል፡፡
ጌታችን ቶሎ ይመጣል ብንዘጋጅ ይወስደናል÷
ባንዘጋጅ እንቀራለን ከሰይጣን ጋር እንኖራለን፡፡
አዝማች

## ኃያል

ኃያል (4 ጊዜ) ሰዳዴ ሳጥናኤል፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ኃያል ገባሬ ኃይል፡፡

ባህርን የረዳው ከዲያብሎስ እጅ ያዳነው፥ (2 ጊዜ)
መልአኩ ሚካኤል ነው፥
የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው፡፡

አዝማች

ከዕደ ዕረበናት፥ (4 ጊዜ)
ሶስናን ያዳናት፥
ሚካኤል መልአከ ምህረት፡፡

አዝማች

ዲዳብሎስን ያዋረድከው፥
በእሳት ሰይፍ የቀጣኸው፥ (2 ጊዜ)
ሚዛንህ ትክክል ነው፥ (2 ጊዜ)
ሚካኤል ፍርድህ ድንቅ ነው፡፡

አዝማች

በሐዘን በትካዜ ያለሁት ብላቴና፥ (2 ጊዜ)
አጽናኝ አረጋጋኝ፥
ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና፡፡

## ና ጌታ ሆይ

ና ጌታ ሆይ ተመላለስ፥
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕይወቴን አረስርስ፥ አዝማች
እንደ መቶ አለቃ እንደ ቆርኔሌዎስ፡፡

ጌታ ሆይ በፊትህ እንዲኖረኝ ሞገስ፥
ስጠኝ የሚያፅናና የሚባርክ መንፈስ፡፡
የሕይወትን ውኃ በልቤ ውስጥ አፍስስ፥
አንተን እንዳከብር ስምህን እንድቀድስ፡፡

አዝማች

ያለም ሥራ ከንቱ ይውጣ ድል ተመቶ፥
ሕይወቴ እንዲለወጥ በፀጋ ተሞልቶ፡፡
ሃሳቤን ለውጠው ስሙ ላንተ ይሁን፥
ሥጋ በመንፈስ ላይ እንዳይኖረው ሥልጣን፡፡

አዝማች

የፈተና ወጀብ እያንገዳገደኝ፥
መቆምም አልቻልኩም መሄድም ተሳነኝ፡፡
ስዝል ሳንቀሳፋ የሚቀሰቅሰኝ፥
የኃይልህን ደወል ድምፅህን አሰማኝ፡፡

አዝማች

የጠላትን ሾተል የምከላከለው፥
የነፃነት ጋሻ በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡
ተስፋው መነመነ ዘንዶው ተጨነቀ፥
ድል እንደተመታ አቅሙን ስላወቀ፡፡

አዝማች

በመንፈስህ ባርከኝ አድነኝ ከቅስፈት፥
ጌታዬ አንተ ነህ የዘላለም ሕይወት፡፡
የእውቀትን መንፈስ የሚገልጽ መንፈስ ነው፥
የእውቀትም መንፈስ እየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

አዝማች

## ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ

ንሴብሆ ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ፥ (2 ጊዜ)
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ፡፡

ንሴብሆ ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ንሰብሆ ለአምላክ እዝራ፡፡

ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩሉ ሌሊት፥
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልጀምር ማህሌት፡፡
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ፡፡
ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሃን፥
ግርማ ለብሶ አስገረመኝ የአምላኬ ዙፋን
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ፡፡

አዝማች

ኑ በዚያ ቤት ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር፥
እልል እንበል በምስጋና ፀጋውን እንጀምር፡፡
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ፡፡
አዕዋፉ በማለዳ መዝሙር ሲጀምሩ፥
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በሚስጥር ሲያወሩ፥
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ፡፡

አዝማች

ከበሮ ሆይ ፀናፅል ሆይ ለምስጋና ተነስ፥
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ፡፡
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ፡፡
ከበሮ ሆይ ፀናፅል ሆይ ለምስጋና ተነስ፥
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ፡፡
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ፡፡

አዝማች

## ንስሃ

ንስሃ፥ ንስሃ፥ ንስሃ፥
የመዳን ጥሪ የመንፈስ ውሃ፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ንስሃ፥ ንስሃ፥ ንስሃ

አዳም እራሱን አጥቦ፥
ዘር፥ አብራኩ እንዲፀዳ፥
ጌታ ስለ ንስሃ መጥቶ ከፈለን ዕዳ፡፡
ተመከር ቢሉት ፈርዖንን፥
እምቢ አሻፈረኝ ስላለ፥
ከነጠሩ ሰጠመ ገባ ከባሕር ማዕበል፡፡
አንተ ወዳጄ ሆይ ቀጥፈህ እንደሆነ ዕፀበለስ፥
ይቅርታ ጠይቅ በጊዜ፥
ዕለተ ምፅአት ሳትደርስ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ዮሐንስ ዛሬም ይጮሃል÷
በምድረ በዳ ወጥቶ÷
መንግሥተ ሰማይ መቅረቧን÷
ሳልሰማ ያሰማል ሰምቶ፡፡
በደም የፀደቀች ናት÷
የሰማይቱ ማረፊያ፡፡
ንስሃ ያዙ እጅ መንሻ÷
አምላክም ደጅ መታያ፡፡
ሐዋርያትም ተሾሙ ሁሉን ሊፈቱ ሊያጠሩ÷
መፍቻው ካህኑ ቤቱ÷
እየመጣችሁ ተማሩ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የእግዚአብሔር ፍቅር ይገርማል÷
በቸርነቱ ብዛት አዋጅ አስነገረልን፡፡
ዳግም የሰላም ጥሪ÷
ሞቶ አልቀረም ቃል በቁም፡፡
መናዘዝ ለካህን÷
በፀፀት መመለስ አለ፡፡
በምህረት ከታደሉ÷
ከለላ ያዙ ቀኑን በመርከቢቷ ዝለቁ፡፡
በንፅህና ታጥባችሁ÷
ፀድታችሁ ተጠባበቁ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

## ንጉሥ ተወለደ

ንጉሥ ተወለደ የዓለም መድኃኒት÷
መርገምን መለሳት ወደ ምርቃት÷
ሔዋንን አስፈታት ከወህኒ እስራት÷
ባለግምጃ ጥላ ሆነች እመቤት፡፡

አንተ ባትወለድ መድኃኒታችን÷ አዝማች
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን፡፡
አንተ ባትወለድ የእኛ አምላካችን÷
ባክነን እንቀር ነበር እኛ ሁላችን፡፡

ሰዎች እናክብራት የዛሬዋን ቀን፥
የንጉሥ ልደት ናት የዓለም መድኅን፡፡
ደግሞም እንዘምር የአማረ መዝሙር፥
ለአፍ የሚጣፍጥ ከማር ከስኳር፡፡
አዝማች
እናክብራት እስቲ የዛሬዋን ቀን፥
የዓለም ሁሉ ፀሐይ ስለወጣልን፡፡
ሠራዊተ ሄሮድስ ጠሉ ልደቱን፥
ክፉ የሚሠራ አይወድም ብርሃን፡፡

## አልተወኝም ጌታ ይወደኛል

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል፡፡
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነሽ ይለኛል፡፡

ተከልኩኝ ከእርሱ በኃጢአት ጫካ፥
ስጠፋበት እንኳን አልተወኝም ጌታ፥
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል፥ | (2 ጊዜ)
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል፡፡ |
አዝማች
ለሥልጣን ለክብሬ ብዬ ስክደው፥
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው፥
ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም፥ | (2 ጊዜ)
ዛሬም ይውደኛል ጌታ አልጠላኝም፡፡ |
አዝማች
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን፥
ከድቅድቅ ጨለማ ለአወጣኝ እኔን፥
በሕይወቴ ሙሉ ፍጹም ለመራኝ፥ | (2 ጊዜ)
ክብርና ምሥጋና አቀርባለሁኝ፡፡ |
አዝማች

## አመስግኑት አመስግኑት

አመስግኑት አመስግኑት ጌታን አመስግኑት አዝማች
አመስግኑት አመስግኑት ጌታን አመስግኑት

ይኖራል ዘላለም ለረጅም ዘመናት (2 ጊዜ)
ትናንትም ገንዘቡ ዛሬም የእሱ ናት
ነገም ገንዘብ ነች ዛሬም የእርሱ ናት
አመስግኑት አመስግኑት ጌታን አመስግኑት
መዝሙር 145

አዝማች

ይኖራል ዘላለም ጌታን አመስግኑት (2 ጊዜ)
አመስግኑት አመስግኑት ጌታን አመስግኑት
ዘመን ይለወጣል ዘመንም ይተካል
የሠራዊት ጌታ ዘላለም ይኖራል
አመስግኑት አመስግኑት ጌታን አመስግኑት
መዝሙር 150

አዝማች

## አማኑኤል ተመስገን

አማን በአማን አማን በአማን (2 ጊዜ)
አማኑኤል ተመስገን አማኑኤል ተመስገን
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ፡፡ (2 ጊዜ)
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ
ለኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ፡፡
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ፡፡ (2 ጊዜ)
በየደቂቃው ኃጢአት ስሠራ
ስሰርቅስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየርም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም፡፡
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ፡፡ (2 ጊዜ)

ምህረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ
በክንድህ ጥላ መኖር አቃተኝ፡፡
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ፡፡ (2 ጊዜ)
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ ምሩር ፍፁም አይጥምም
እንደበደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ፡፡
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ፡፡ (2 ጊዜ)

## አምላክ ሆይ ታረቀን

ቅያሜው ይቅርና አምላክ ሆይ ታረቀን አዝማች
አንተ ስለራከን ሞት ነው የከበበን (2 ጊዜ)
እስከ መቼ ድረስ ሕዝብህ ተጐሳቁሎ
በረከሰ መንፈስ በርኵሰት ተጥሎ
ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት
እባክህ አምላኬ ኢትዮጵያን ታረቃት
እባክህ አምላኬ ዓለምን ታረቃት፡፡
አዝማች
የዘመኑ ጣዖት ገንዘብ እያሳተን
ይህ ደካማ ሥጋ አምላክን አስተወን፡፡
ግብዝነት ሞልቶት ፈራሹ አካል
በነፍስ በሽታ ሕዝባችን ታሟል፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ክንፋችን ተመቶ መብረር አቅቶናል
በመንፈስ በሽታ ሕዝባችን ታውኳል
እራዕይ የሌለው ተራ ሰው ስለሆንን
እባክህ ጌታችን በፍጥነት ታረቀን፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ፀጋህ የተለየን ባዶነት ወሮናል
ፍቅር የተነፈገን ሰላም የጐደለን
ሆነን ስለቀረን እግዚአብሔር ታረቀን
ጽድቅህን አድለን ጽድቅ እንደተመኘን፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

እስከ መቼ ድረስ ሕዝብህ ተጐሳቁሎ
በረከሰ መንፈስ በርኵሰት ተጥሎ
ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት
እባክህ አምላኬ ኢትዮጵያን ታረቃት
እባክህ አምላኬ ዓለምን ታረቃት።

## አምላክ በአንቺ አደረ

አምላክ በአንቺ አደረ ንጽሕናሽን ወዶ÷ (2 ጊዜ) አዝማች
ከሥጋሽም ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ወስዶ። (2 ጊዜ)

ድንግል እመቤቴ የአምላክ እናት÷
ተስፋችን ነሽ አንቺ የመግቢያ ገነት።
ትንቢት በነብያት የተነገረልሽ÷
የኖህ መርከብ ማርያም ንጽሕት አንቺ ነሽ።

አዝማች

የሰሎሞን መቅደስ የሙሴ ጽላት÷
ካንቺ ተገኘልን የዓለም መድኃኒት።
በክብ በምስጋና እናመስግንሽ÷
አምባ መጠጊያችን ድንግል አንቺ ነሽ።

አዝማች

እናምናለን እኛ በእናትነትሽ÷
ድንግል ሆይ አማልጅን ከቸሩ ልጅሽ።
አምላክ በአንቺ አደረ ንጽሕናሽን አይቶ÷
ማደሪያ እንድትሆኝ ከፍጥረቱ መርጦ።

አዝማች

ድንግል ሆይ ስለአንቺ ነውና መሐሪ÷
አማልጅን ከልጅሽ ከቸሩ ፈጣሪ።
የኃጥኣን ተስፋ ነሽ ድንግል ዘለዓለም÷
የባለወልድ እናት የመድኃኔ ዓለም።

አዝማች

የምትለግሽን ለእኛ በረከት÷
እስቲ እናመስግንሽ ቅድስት እመቤት።
ምስጋና ይገባሻል በእልልታ ዝማሬ |(3 ጊዜ)
የተቀደሰ ነው የማኅጸንሽ ፍሬ። |

## አምላክ አለ መሃላችን

ደስ ይበለን (2 ጊዜ) አምላክ አለ መሃላችን፥ (አዝማች)
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ፥
ገናና ነው አምላክ ክብርህ።

ምሕረቱን አይተናልና፥
አድርሶናል አምላክ በጤና፥
ይህችን እድሜ የጨመረልን፥
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን።
አዝማች
ኃጢአትህን ይታገስሃል፥
በቸርነትህ አምላክ ያይሃል።
ደስታ ነው በሰማያት፥
በአንድ ኃጥእ የጽድቅ ሕይወት።
አዝማች
ድንግል ማርያም ትጸልያለች፥
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች፥
በድንግል ክብር እንኖራለን፥
በጽኑ ፍቅር አንዴ ቢያድነን።
አዝማች
እልል በሉ የጎበኛችሁ፥
በቸርነት አምላክ ያያችሁ፥
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ፥
አመስግኑት ዝምም አትበሉ።

## አምላክ ወደደሽ

ከዙፋን ወርዶ ወልደ እግዚአብሔር ጌታ እየሱስ
ወዳንቺ መጣ መረጠሽና ቅዱሱ መንፈስ
ከሴቶች ሁሉ ንፅህት ሆነሽ ስተተገኘሽ
በማኅፀንሽ አደረ ጌታ አንቺን ወደደሽ።

የመላእኩን ቃል እንዳልከው ይሁን በማለትሽ አዝማች (2 ጊዜ)
አምላክ ወደደሽ ባንቺ አደረ በማኅፀንሽ፡፡

ያልታሰበውን ስጦታ የሚሰጥ የፍጥረት ጌታ
ሥጋሽን ለብሶ ላንቺ ሆነልሽ ዕፁብ ስጦታ
ምሥጋና ይድረስሽ እንልሻለን እኛ ሁላችን
ባንቺ ምክንያት ስለታደሰ መላሕይወታችን፡፡

አዝማች

የሔዋን እዳ ባንቺ ተባሰ እመቤታችን
የገነትን ደጅ አስከፈትሽልን አስታራቂያችን
መመኪያችን ነሽ አለኝታችን ነሽ ድንግል ማርያም
ጌታን ያዘልሽው የሚኖረውን በላይ በአርያም፡፡

አዝማች

ለዚህ የታደልሽ የምህረት እናት አማላጃችን
ለኛ ሆንሽልን የሕይወተ መሰላል የመዳኛችን
አይጨክን ሆዴ ርኅርት እናት ባንቺ ተማምነን
በረድኤትሽ እንዳትለይን እንልሻለን፡፡

አዝማች

## አምላካችን ተመስገን

አምላካችን ተመስገን÷ (2 ጊዜ) አዝማች
ለዛሬ ያደረስከን፡፡
አምላካችን ተመስገን÷ (2 ጊዜ)
ለዚህ ቀን ያደረስከን፡፡

በኃጢአት ስንማቅቅ በምሕረትህ ጠራኸን÷
በዓለም ስንባዝን ነበር በይቅርታህ መራኸን÷
አምላክ ሆይ ተመስገን፡፡
ትዕግሥትህ ብዙ ነው አያልቅም ርኅራሄህ÷
የምንከፍልህ ምን ይሆን ብዙ ነው ውለታህ÷
አምላክ ሆይ ተመስገን፡፡

አዘማች

ከቶ የማትፈልግ ከሰው ልጆች ወሮታ፥
ቸር ፈጣሪህ ነህና ሥራህ ድንቅ ነው ጌታ፥
አምላክ ሆይ ተመስገን።
ይቅር ሆይ አምላካችን ሆይ አንተን እናመልካለን፥
ከመዓትህ ታግሰህ ሁሉንም ይቅር አልከን፥
አምላክ ሆይ ተመስገን።
አዝማች
ኃጢአታችን ጨለማ ቢያደርገው ኑሮአችንን፥
በአንተ ተጎናጽፈናል የማዳንህን ብርሃን፥
አምላክ ሆይ ተመስገን።
ስለአደረግህልን ሁሉ ስለግሩም ሥራህ፥
የራስህን እንስጥህ ተመስገን እንበልህ፥
አምላክ ሆይ ተመስገን።
አዝማች

## አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምንኛ ዕድለኞች ናቸው፥ (2 ጊዜ)
አዝማች
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ በጽዮን አዳራሽ የወረደላቸው፥
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ በጽዮን አዳራሽ (2 ጊዜ) የወረደላቸው።

ዞረው እንዲያስተምሩ በየምድባቸው፥(2 ጊዜ)
ሰባ ሁለት ቋንቋ (2 ጊዜ) ተገለጸላቸው። (2 ጊዜ)
ጴጥሮስ ሲጠባበቅ ያንን የተስፋ ቃል፥ (2 ጊዜ)
ወርዶ አጥለቀለቀው (2 ጊዜ) የመንፈስ ማዕበል። (2 ጊዜ)
አዝማች
ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ሲሞሉ፥ (2 ጊዜ)
ጉሽ ጠላ ነው ብለው (2 ጊዜ) አይሁድ አስባሉ። (2 ጊዜ)
አዝማች
በመንፈስ መሪነት ጽድቅን የሚመኙ፥ (2 ጊዜ)
ሦስት ሺ አማኞች በአንድ ቀን ተገኙ። (2 ጊዜ)
አዝማች
እንደባረካቸው ሐዋርያትን፥ (2 ጊዜ)
አቤቱ ጌታ ሆይ (2 ጊዜ) እኛንም ባርከን። (2 ጊዜ)

## ዐሥርቱ ቃላት

ለነቢዩ ሙሴ የሰው ሥርዓት (2 ጊዜ)
ዐሥር ቃላት ናቸው የሚከተሉት (2 ጊዜ)
የመጀመሪያቱ ሕገ አምልኮት (2 ጊዜ)
ከእኔ በቀር ሌላ አታምለክ ጣዖት (2 ጊዜ)
በሃሰት አትመስክር ተጽፏል መቅሰፍት (2 ጊዜ)
አባት እናትህን አክብር ሰንበትን ቀድሳት (2 ጊዜ)
አትግደል አትስረቅ አታመንዝር ከቶ (2 ጊዜ)
የገሃነም በሩ ይቆያል ተከፍቶ (2 ጊዜ)
ኦሪቱ ሲነበብ ከወንጌል ተስማምቶ (2 ጊዜ)
ጆሮ ያለው ይስማ ልቦናን አንጽቶ (2 ጊዜ)
የሃይማኖት ነገር እስከዚህ ይበቃል (2 ጊዜ)
ሕግን ቢያስረዝሙት መቼ ይዘለቃል። (2 ጊዜ)

## አትተወኝ

አትተወኝ አትጣለኝ፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ወድቄአለሁና ጌታ ሆይ አንሳኝ። (2 ጊዜ)

ቸሩ መድኃኔ ዓለም የአልዓዛር ቤት እራት፥
የኑኛዬ ጣዕም የሕይወቴ መብራት፥
በኃጢአት ጭቃ ላይ ወድቄአለሁና፥
ጌታዬ ሆይ አንሳኝ እጅህን ዘርጋና። (2 ጊዜ)

አዝማች

የሰጠኸኝን ክብር የልጅነት ሥልጣን፥
እንደ ሳምሶን ፀጉር ከገሊላ ጋጣን፥
እርቃኔን ቀረሁኝ ተላልፌ ሕግህን፥
አምላኬ ዘርጋልኝ የምህረት እጅህን። (2 ጊዜ)

አዝማች

ዘወትር እየበደልኩ ከሕግህ እርቄ
በኃጢአት ጭቃ ላይ ክፉኛ ወድቄ፥
በበደሌ እሥራት ተይዣለሁና፥
አባቴ ሆይ ማረኝ መሃሪ ነህና። (2 ጊዜ)

አዝማች (4 ጊዜ)

## አንተ ስትናገር እኔ እንድሰማ

አንተ ስትናገር እኔእንድሰማ
እንደ ልድያ ልቤን ክፈትና አዝማች (2 ጊዜ)
ወደ ልቤ ግባ እባክህ ጌታዬ
በእምነቴ እንድፀና ባርክልኝ ሕይወቴን

ጆሮየን ክፈት ደንቁሯል በዓለም
በሥጋ ተዘግቶ ቃልህን አይሰማውም
የማልኮስን ጆሮ እንደቀጠልክለት
የልቤንም ጆሮ ጌታ ክፈትልኝ።
አዝማች (1 ጊዜ)

አንተ ስታስተምር በሥጋ ቁጭ ብዬ
ሃሳቤ ተከፍሎ በእንቅልፍ ተታልዬ
እንደ ዛለው ወጣት ከደርቡ ላይ እንዳልወድቅ
በማስተዋል መንፈስ ካንተ ጋር ልታረቅ።
አዝማች (1 ጊዜ)

ሥጋ በመንፈስ ላይ ሠልጥኖ እንዳይጥለኝ
በመንፈስ አስተምረኝ ይኸው ከእግርህ ሥር ነኝ
በቃልህ ልመራ መንገድህን ልወቅ
በእውነተኛ ፍቅር ካንተ ጋር ልታረቅ
አዝማች (1 ጊዜ)

ቃልህ በሕይወቴ በእምነት ተዋህዶ
ካንተ የተቀበልኩት ኩልህ አጥርቶልኝ
አንተን ጠብቃለሁ ጌታ ሆይ ቶሎ ና
ያችን ጽዮን ሐገር ናፍቄአለሁና።
አዝማች (2 ጊዜ)

## አንድ ሁኑ

አንድ ሁኑ ብሎ ኅብረትን ያደለን
የፍቅር አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ አዝማች
እንደ ሐዋርያት እንደ አገልጋዮቹ
አንድ ልብ ይስጠን ጌታ ለልጆቹ፡፡

ምስገና እናቅርብ ለጌታ ለእግዚአብሔር (2 ጊዜ)
ዛሬም ረድቶናል በኅብረት እንድንኖር፡፡ (2 ጊዜ)
ሰውን ደስ አለው ዲያብሎስ አፈረ (2 ጊዜ)
የጠላት ወጥመድ ዛሬም ተሰበረ፡፡
አዝማች
በሰላም ኑሩ በአንድነት በፍቅር (2 ጊዜ)
አንድ ነኝና እኔም ከአባቴ ጋር፡፡ (2 ጊዜ)
እንድንገባ በሰማያዊው በር (2 ጊዜ)
በኅብረት ኑሩ ይለናል እግዚአብሔር፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ታላቅ ደስታ ነው ዛሬ ለሁላችን (2 ጊዜ)
ፍቅር ሲደራ ሲያብብ ኅብረታችን፡፡ (2 ጊዜ)
እንዳንሸነፍ ለሠይጣን ፈተና (2 ጊዜ)
እግዚአብሔር ይርዳን በኅብረት እንጽና፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

## አካሄዴን ጠብቅ

አካሄዴን ጠብቅ ጌታ ቸር አምላኬ ሆይ
ኋላ በፍርድ ቀን ስቃይአበሳ እንዳላይ አዝማች
አካሄዴ ፍፁም፥ ቅዱስ፥ ፍፁም ቅዱስ እንዲሆን
እዚህ አለሁኝ በላት ጌታ የዓለሙ መድህን (2 ጊዜ)

ከድንግል የወጣህ ከቅድስት ማረያም
ልብ የምትመረምር ሆነህ በአርያም
ድንቅ መካር ኃያል የዘለዓለም ንጉሥ
ክብር ለአንተ ይሁን ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡
አዝማች

መንገዴን ጌታ ሆይ አደራ እሰጣለሁ
ልቤንም አድሰው በአንተ እታመናለሁ፡፡
አባት ሆይ መንገዴን በመንገድህ ሳድርግ
እዚህ አለሁኝ በለው አንተኑ እንዲፈልግ፡፡
አዝማች
አምላክ ሆይ ስመጣፍለጋአንተን
ከቅዱስ ስፍራ ቤተ ክርስቲያን
የበረከት ሥፍራ መሆኗን በዕውነት
ጌታ ሆይ አኑራት በልቤ ፅላት፡፡
አዝማች
ምንም ብበድልህ ባስከፋህ አንተን
በርካሽ አንደበት ባስቀይም ጌታን
አባት ሆይ በምህረት እንድታስበኝ
ልቤን ተረከበው አንተ አስተዳድረኝ፡፡
አዘማች

## እልል በይ ቤተልሔም

እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ÷ አዝማች (2 ጊዜ)
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ÷
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ፡፡
ሣር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንበሌጥ ቄጠማው÷
በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም የነበረው÷
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው÷
ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
ያ ትሑት እረኛ የትህትና አባት÷
ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ሌሊት÷
ጥሪ ተደርጐለት ከሰማይ ሠራዊት÷
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
እረኝነት ትንሽ የወራዳ ግብር÷
ብሎ ሰው በግምት ደንግጐት ነበር፡፡
የብዙ ሰው እራስ መሆኑን እረኛ÷
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## እልፍ አዕላፋት

እልፍ አዕላፋት ወትእልፊት÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ቅዱሳን ንጹሐን መላእክት÷
ቆሙ ለአገልግሎት ጸንተው በአንድነት÷
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አምላክ በማለት፡፡

ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት አገር÷
የሃይማኖት የፍቅር የድኅነት አገር፤
እውነት የታየብሽ የመላእክት ክብር፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
እንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ÷
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ÷
ግማሹ እየካደ ቀረው ሲያመነታ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
ቅዱሳን መላእክት በእምነት የቆማችሁ÷
በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ÷
ስግደት ዘበፀጋ እንስገድላችሁ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## እመቤታችን ለአንቺ እናቀርባለን ምስጋና

እመቤታችን ለአንቺ እናቀርባለን ምስጋና÷ አዝማች
አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት (2 ጊዜ) ሆኖአልና፡፡

ያስጨናቂዎችሽ ልጆች አሕዛብ በሙሉ÷
ንስሐ በመግባት ወደ አንቺ ይመጣሉ÷
ይቅር በይን ብለው (2 ጊዜ) ከእግርሽ ይወድቃሉ፡፡
አዝማች
ሕፃናት ስላወቁ ደግነትሽን በሙሉ÷
ወደ አንቺ ሁልጊዜ ይማልዳሉ÷
ከፈጣሪሽ (2 ጊዜ) አማልጅን እያሉ፡፡
ነይ ነይ ወደ እኛ ማርያም ነይ ነይ ወደ እኛ (2 ጊዜ)
ድንግል ማርያም የእኛ መዳኛ ነይ ነይ ወደ እኛ ማርያም፡፡

በቃል ኪዳንሽ እኔ አምናለሁ እማፀናለሁ÷ (2 ጊዜ)
ያንን የእሳት ባሕር በአንቺ እሻገራለሁ÷
በቃል ኪዳንሽ እኔ አምናለሁ።

በቃል ኪዳንሽ በማመን በመተማመን÷ (2 ጊዜ)
በዓመት አንድ ጊዜ አልቀርም ግሸን በቃል ኪዳንሽ በማመን።
አዝማች
ሰማያዊ ሃገር አላርፍም እኔ ስሄድ÷
ስንቅ ትሆነኛለች ድንግል በመንገድ÷
ጠምቶኝም ርቦኝ ጠምቶኝም ርቦኝ ሲኦል እንዳልወርድ።
አዝማች
የመለኮት ዙፋን ድንግል ለመሆን በቅተሽ÷
መልአኩ ገብርኤል መጥቶ አበሰረሽ÷
የአዲስ ኪዳን ኪሩብ የአዲስ ኪዳን ኪሩብ እኛም እንበልሽ።
ነይ ነይ ወደ እኛ ማርያም ነይ ነይ ወደ እኛ÷ (2 ጊዜ)
ድንግል ማርያም የእኛ መዳኛ ነይ ነይ ወደ እኛ ማርያም።
የመስቀሉ ቃል አደራ ነሽ ስጦታ ነሽ÷ (2 ጊዜ)
ጣምሽም ፍቅርሽም ይደር በሚያምንሽ÷
የመስቀሉ ቃል እናት ነሽ።

## እመቤቴ ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ

እመቤቴ ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ÷
አድኚኝ ከችግር ከጭንቅ ከሥቃይ።
ያለሽን ቃል ኪዳን አውቀዋለሁና÷
ድንግል ሆይ ሰውሪኝ ከክፉ ፈተና።
የኤፍሬም እመቤት ያባህርያቆስ÷
አንቺ አማላጅ ነሽ ለኃጥአን ነፍስ።
ስምሽ ከሚጠራ በክፉ ነገር÷
እኔው በኃጢአቴ ልወጋ በጦር።
ምንም ታጥቦ ጭቃ ቢሆንም ሥራዬ÷
ድንግል አትለይኝ ጥላ ከለላዬ።
ስምሽን ላነሳሳው እመቤቴ ሆዴ÷

የችግሬ ደራሽ የቅርብ ዘመዴ።
እንግዲህስ ይብቃኝ ማዘን መተከዜ÷
መሸጋገሪያዬ ነይልኝ ምርኩዜ።
ከሞት ወዲያ ማዶ ላለችው ሕይወቴ÷
ጠበቃ እንድትሆኚኝ ድንግል እመቤቴ÷
አሥራት አገርሽን ኢትዮጵያን ባርኪያት።    |(2 ጊዜ)
ሠይጣን በተንኮሉ እንዳያጠቃት።    |
እመቤቴ ማርያም የአምላኬ እናት÷
አንቺን የመረጠሽ ይክበር መለኮት።

## እመአምላክ ሙሽራ

እመአምላክ ሙሽራ ነሽ÷ (2 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
የቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ። ኧኸ÷ ኧኸ÷ ኧኸ÷

አሥራ ሁለት ዓመት ቤተ መቅደስ ኖረሽ÷
የመመረጥ ፀጋ ከጌታ ያገኘሽ÷
አምላካዊ መልእክት እፁብ ድንቅ ዜና÷
ከሰማይ መጣልሽ አቋርጦ ደመና።

አዝማች

በስድስተኛው ወር ተልኮ ገብርኤል÷
ቤተ መቅደስ መጣ ሊያበስራት ለድንግል÷
በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ አለሽ÷
የክርስቶስ እናት ድንግል ደስ ይበልኝ።

አዝማች

መላእክት ከሰማይ ያመሰግኑሻል÷
ክብር ለአምላክ እናት ይድረሳት ይሉሻል።
በማኅፀንሽ ሊያድር የሠራዊት ጌታ÷
ለመሆን ተመረጥሽ የአምላክ ቅዱስ ቦታ።

አዝማች

የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ÷
ሰላም ለአንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነስቶ።
ከፍጡራን ሁሉ አንቺ ስለከበርሽ÷
ገብርኤል ተልኮ ደስታን አበሰረሽ።

አዝማች

ምንኛ ድንቅ ነው ድንግል የአንቺ ብሥራት፥
ሕይወት ትወልጃለሽ የሚል ቃልን መስማት፡፡
ይሁንልኝ ብለሽ ቃልን የተቀበልሽ፥
ድንግል ሆይ እናቴ እጅግ ልዩ እኮ ነሽ፡፡

አዝማች

ንጽሕት ሙሽራ ጌታ ያደረብሽ፥
ድንግል በእኛም ይደር ፀጋ በረከትሽ፡፡
ማንም አልታደለ ከፍጡር እንደ እርሷ፥
እኛን ይጐብኘን ቅዱሱ መንፈሷ፡፡

አዝማች (4 ጊዜ)

## እምነቴን አጠንክር

እምነቴን አጠንክር ጌታ በዚህች ዕለት፥ አዝማች
እንደ አባት አብርሃም አውርድልኝ ምሕረት፡፡
የምሕረት አምላክ የሰላም ንጉሥ፥
እርዳታ ያሻኛል ጌታዬ ኢየሱስ፡፡

የእምነቴ ፍቅር መተማመኛዬ፥
በጐኔ የምትኖር ኃያል መከታዬ፥
ዘለዓለማዊ አምላክ ጦርና ጋሻዬ፥
መንፈስህን ላክልኝ ክርስቶስ ጌታዬ፡፡

አዝማች

በእምነት ጌታ ሆይ መፅናት አቅቶኛል፥
በምሕረትህ ጐብኘኝ አሁን ይሻለኛል፡፡
ድህነቴ በአንተ ላይ ስለሆነ ጌታ፥
መንፈስ ያጽናናኛል ዛሬ እንዳልረታ፡፡

አዝማች

እንደ ይሁዳ ደግሞ እንዳልቀር በዋዛ፥
በደሌ በፊቱ ፍፁም እንዳይበዛ፥
እምነት ይሰጠኛል የዓለም ሁሉ ቤዛ፥
ፍቅርን ያድለኛል እንዳልሆን ከርታታ፡፡

አዝማች

በመንፈሳዊ ሕይወት እመላለሳለሁ÷
ስምህን ለመጥራት ዘወትር እፈራለሁ÷
የዚህች ዓለም ነገር በልቤ ውስጥ ሠፍሮ÷
ከአንተ ሊያርቀኝ ነው ወዮልኝ ዘንድሮ።

አዝማች

እንደምትረዳኝ እተማመናለሁ÷
ከሥጋ ምኞቶች አርቀኝ ብያለሁ።
ዝሙትና ርኵሰት ከእኔ አስወግድና÷
የልጅነት ሥልጣን ስጠኝ እንደገና።

አዝማች

እርዳታ ያሻኛል ጌታዬ ኢየሱስ (3 ጊዜ)

## እምድንግል ተወልደ አማኑኤል

እምድንግል÷ እምድንግል÷ አዝማች (4 ጊዜ)
እምድንግል ተወልደ አማኑኤል።

| | |
|---|---|
| ነቢያት ሁሉ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ትንቢት ሲናሩ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| የሠራዊት ጌታ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ይወርዳል እያሉ። | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| አዝማች (2 ጊዜ) | |
| መጣ ተወለደ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| መድኃኔ ዓለም÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ከድንግል ማርያም። | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| አዝማች (2 ጊዜ) | |
| መጣ ተወለደ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| የፍጥረታት ጌታ÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ድምጹንም ሰማነው÷ | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |
| ይኸው በኤፍራታ። | አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል |

አዝማች (2 ጊዜ)

በአጭር ቁመትና÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በጠባብ ደረት÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
ተወስኖ አየነው÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በከብቶች በረት፡፡ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
አዝማች (2 ጊዜ)
ሰባ ሰገድ መጡ÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በኮከብ ተመርተው÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
ዕጣን ወርቅ ከርቤ÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
እጅ መንሻ ይዘው፡፡ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
አዝማች
ሰላም ተወጠነ÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በምድር በሰማይ÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
እያሉ ዘመሩ÷ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
መላእክት ባንድ ላይ፡፡ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
አዝማች (4 ጊዜ)

## እሰይ ተወለደ

ነቢዩ ኢሳይያስ ተናገረ ትንቢት÷
ድንግል እንደምትወልድ የዓለምን መድኃኒት፡፡
ስሙ ፈውስ ለሚሆን ድንቅ መጠለያ÷
የሰላም አለቃ የዘለዓለም ሕይወት፡፡

እሰይ÷ ተወለደ እሰይ÷ ጌታችን እሰይ÷ ሃሌሉያ÷ አዝማች (2 ጊዜ)
እሰይ አሜን ተወለደ መድኅናችን÷
ሊያነፃን ከኃጢአታችን፡፡
እሰይ እሰይ እሰይ እንደተናረ÷
በድንግል ማህፀን ጌታችን አደረ፡፡
ክብር ለርሱ የሆነ የሁላችን ጌታ÷
ተወለደልን በከብቶቹ ቦታ፡፡
አዝማች
ከሰማይ ሰማያት ጌታችን ወረደ÷
ከድንግል ማርያም ሥጋን ተዋሃደ፡፡
አስወገደ ጌታ ኃጢአታችንን÷
ደህንነት አስገኘ ለእኛ ለሁላችን፡፡

አዝማች

ምስጋና ይድረሰው ለኃያሉ ጌታ÷
በደሉን ደምስሶ ለሰጠን ይቅርታ፡፡
ከፍ ይበል ይመስገን ክብር ይሁን ለእርሱ÷
ጌታችን ኢየሱስ ኃያል ነው ዘለዓለም፡፡

አዝማች

## እሰይ እሰይ ሞትን ድል አድርጐ ተነሣልን

እሰይ እሰይ (4 ጊዜ) (2 ጊዜ) አዝማች
ሞትን ድል አድርጐ ተነሣልን የጽድቅ ፀሐይ

| | |
|---|---|
| ትንሣኤን ለሰው ልጅ | እሰይ እሰይ |
| ፈንድቆ ሊያበስረው÷ | እሰይ እሰይ |
| ሞትን አሸንፎ | እሰይ እሰይ |
| ይኸው ተነሣልን፡፡ | እሰይ እሰይ |
| እልልታ እናቅርብ | እሰይ እሰይ |
| በአንደበታችን÷ | እሰይ እሰይ |
| አማኑኤል ተነስተኦል | እሰይ እሰይ |
| የምሥራች መድኃኒታችን፡፡ | እሰይ እሰይ |

አዝማች

| | |
|---|---|
| መሬት ተንቀጥቅጦ | እሰይ እሰይ |
| መጽናት አቅቶአት÷ | እሰይ እሰይ |
| መልኳ ተለውጦ | እሰይ እሰይ |
| ብርሃን ሲከባት÷ | እሰይ እሰይ |
| ሞትን አሸንፎ | እሰይ እሰይ |
| ሲነሣ ጌታችን÷ | እሰይ እሰይ |
| ባሉበት ወደቁ | እሰይ እሰይ |
| ጠባቂ እርሱን፡፡ | እሰይ እሰይ |

አዝማች

| | |
|---|---|
| እጅግ ተዋረደ | እሰይ እሰይ |
| ዲያብሎስ አፈረ÷ | እሰይ እሰይ |
| በክርስቶስ መስቀል | እሰይ እሰይ |
| ቀንዱ ተሰበረ፡፡ | እሰይ እሰይ |

| | |
|---|---|
| የአዳም ልጆች ሁሉ | እሰይ እሰይ |
| በጣም ደስ ብሎናል፥ | እሰይ እሰይ |
| አሸናፊያችን ሞት | እሰይ እሰይ |
| ይኸው ጠፍቶልናል፡፡ | እሰይ እሰይ |

አዝማች

| | |
|---|---|
| እንግዲህ ፍርሃት | እሰይ እሰይ |
| ከእኛ ይጥፋልን፥ | እሰይ እሰይ |
| ትንሣኤ አለልን | እሰይ እሰይ |
| አንድ የሚያደርገን፡፡ | እሰይ እሰይ |
| እንዳንቀር ያረገን | እሰይ እሰይ |
| በሞት ተሸንፈን፥ | እሰይ እሰይ |
| ፀጋን ያለበሰን | እሰይ እሰይ |
| አማኑኤል ተመስገን፡፡ | እሰይ እሰይ |
| ክብርን ያለበስከን | እሰይ እሰይ |
| አማኑኤል ተመስገን፡፡ | እሰይ እሰይ |
| ከሞት ያወጣኸን | እሰይ እሰይ |
| አማኑኤል ተመስገን፡፡ | እሰይ እሰይ |

## እስኪ ላመስግንሽ

እስኪ ላመስግንሽ እንደ ችሎታዬ፥ (2 ጊዜ) አዝማች
አንቺ ነሽ እመአምላክ ዋሴ ጠበቃዬ፡፡

ሰማይና ምድርን በቃሉ ያፀና፥ (2 ጊዜ)
ተዋህደልና ከአንቺ ንፅሕና፡፡
ድንግል ይገባሻል ውዳሴ ምስጋና፥ (2 ጊዜ)
ድንግል ይገባሻል ውዳሴ ምስጋና፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ምህረትን እንዳገኝ በነፍስም በሥጋ፥ (2 ጊዜ)
ወደ አንድዬ እናት እጆቺን ልዘርጋ፡፡
እፀ ሕይወት ዛፍ ነሽ ፍሬሽ መድኃኒት፥ (2 ጊዜ)
አንቺን የተጠጋ የለበትም ሞት፡፡

አዝማች

ድንግል በረድኤትሽ የባረክሽው ሁሉ፥ (2 ጊዜ)
ያድርበታልና የመለኮት ኃይሉ።
እንድታሻግሪኝ ከኃጢአት ባሕር፥ (2 ጊዜ)
አደራሽን ቅድስት የአምላክ ማኅደር።
ድክመቴን እያየ ሠይጣን ቢደነፋ፥ (2 ጊዜ)
እመቤቴ እያለች እኔ አልቆርጥም ተስፋ።
ስምሽም ያነፃል ከኃጢአት እድፍ፥ (2 ጊዜ)
የጌታዬን እናት አንቺን ልደገፍ።
እስቲ ላመስግንሽ እንደ ችሎታዬ እንደ ችሎታዬ፥ (2 ጊዜ)
አንቺ ነሽ እመ አምላክ ዋሴ ጠበቃዬ። (2 ጊዜ)

## እስከመቼ ከፊትህ እሸሻለሁ።

እስከመቼ ጌታ ከፊትህ እሸሻለሁ፥ (2 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
ከፀጋህ ርቄ እንከራተታለሁ። (2 ጊዜ)

ጊዜ የማይገድባት ዘለዓለማዊ ነች፥
ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥
ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና ። (2 ጊዜ)
ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ፥
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ጌታ፥
ሰማይም ብወጣ አንተ ነህ፥
ሲኦልም ብወርድ ከዚያው ነህ ጌታ።
አዝማች (2 ጊዜ)
ከፊትህ ርቄ በደሌን፥
ስባዝን ኖሬአለሁ በዓለም ተሸንፌ፥
የበደሌ ዋጋ ሞትን ሳትሰጠኝ፥
ተመልሻለሁኝ ጌታ ይቅር በለኝ። (2 ጊዜ)
ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ፥
ከፊትህስ ወዴት እሸሸለሁ ጌታ፥
ሰማይም ብወጣ አንተ ነህ፥
ሲኦልም ብወርድ ከዚያው ነህ ጌታ።
አዝማች (2 ጊዜ)

አመፃም ብሠራ ከአንተ ተደብቄ፥
ተሸሽጌ ብገዝ ከአንተ ርቄ፥
ከቶ አይሳንህም አንተ ሁሉን ማወቅ፥
ንፁህ ልብ ስጠኝ ሠይጣንን ከእኔ አርቅ።
ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ፥
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ጌታ፥
ሰማይም ብወጣ አንተ ነህ፥
ሲኦልም ብወርድ ከዚያው ነህ ጌታ።
አዝማች (2 ጊዜ)

## እናመስግነው

እናመስግነው፥ (4 ጊዜ) አዝማች
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው። (2 ጊዜ)
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው። (2 ጊዜ)

ከኃጢአት ገደል ከሞትም ጐትቶ፥
መንግሥቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ፥
ዘለዓለማዊ ክብር ታላቅ ሀብት ያደለኝ፥
መቼም የማይተወኝ ታላቅ አባት አለኝ።
አዝማች
ፍጡራን ቢንቁኝ መጐስቆሌን አይተው፥
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋ ቢስ ነው ብለው፥
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መች ተውከኝ፥
ሁለት እጄን ይዘህ ልጄ ተነስ አለከኝ።
አዝማች
ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ላደለን፥
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን?
ለታላቁ ረዳት ጌታ ለዋለልን፥
በእልልታ እንቅረብ በአንድነት ሆነን።
አዝማች

## እኔስ ተስፋ አልቆርጥም እጽናናለሁ እንጂ

እኔስ ተስፋ አልቆርጥም እጽናናለሁ እንጂ÷ (2 ጊዜ) አዝማች
እስኪዘረጋልኝ አምላክ የሱን እጅ፡፡ (2 ጊዜ)
ፈጣሪ አይተወኝም መሃሪ ነውና÷ (2 ጊዜ)
ምህረት እስኪሰጠኝ በሃይማኖት ልጽና፡፡
በሥጋ በነፍስ ወድቄስ አልቀርም÷ (2 ጊዜ)
ያነሳኛልና ቸሩ መድኃኔ ዓለም፡፡
አዝማች
አትጨነቀ ብዙ አትሸበር ሆዴ÷ (2 ጊዜ)
ተይዘህ አትቀርም በጨካኝ ወንበዴ፡፡
አቤቱ ፈጣሪ ቅዱስ አማኑኤል÷ (2 ጊዜ)
ሠይጣን እንዳይረታኝ አድለኝ የአንተን ኃይል፡፡
አዝማች
ይቅርታህ የበዛ ምህረት የምትሽ÷ (2 ጊዜ)
የማትፀየፈው የኃጥአንን ነፍስ÷
ከአንተ ተለይቼ እንዳልዋረድ÷ (2 ጊዜ)
ከአሁኑ አስለቅቀኝ ከኃጢአት ወጥመድ፡፡
አዝማች
ምቀኛው ዲያብሎስ ድል እንዳይነሳኝ÷ (2 ጊዜ)
እንደቸርነትህ አምላክ ሆይ ጐብኘኝ፡፡
ማርያም መግደላዊት ቸር መሆንክን አውቃ÷ (2 ጊዜ)
በእንባዋ አጠበችህ እግሮችህ ሥር ወድቃ፡፡
እኔስ አበሳዬ በደሌም ቢበዛ÷ (2 ጊዜ)
አንተነህ ተስፋዬ የዓለም ሁሉ ቤዛ፡፡
እንደምታድነኝ በነፍስ በሥጋዬ÷ (2 ጊዜ)
አልጠራጠርም አምናለሁ ጌታዬ
አዝማች

## እንማልድሃለን

እንማልድሃለን ጌታ ሆይ÷ አዝማች
በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበን÷
ሥራችን እንዲቃና ተገኝ በማዕከል በማዕከላችን፡፡

የነፍሳችን ቤዛ የዓለም መድኃኒት÷
የእውነተኞች ፀጋ ለአዳም ሕይወት÷
ፈቃድህ ይምጣልን በዛሬዋ ዕለት÷
ጀምረናልና በስምህ ፀሎት፡፡
አዝማች
ስምህን ለመቀደስ በረቂቅ ምስጢር÷
አንድነት በመሆን በመተባበር÷
እውነትን አጉልተን እንድንናገር÷
አድለን ለሁሉም አምላክ የአንተን ክብር፡፡
አዝማች
ፈቃድህ ሆኖልን ነበር ከኛ ጋራ÷
የጀመርነው ፀሎት ፍሬን እንዲያፈራ፡፡
ፀሎታችንንም ስማን ጌታችን ሆይ÷
በሕግህ ተመርተን ክብርህን እንድናይ፡፡
አዝማች
እንድትኖር ዘላለም በነፃነት÷
ጠብቃት ኢትዮጵያን፡፡
ለሕዝቦቿም ዕናትን÷
ሰላም እንዳይለየን ፈቃድህ ይሁንልን አሜን፡፡

## እንዘምር ሁላችን

እንዘምር እንዘምር እንዘምር ሁላችን÷ (2 ጊዜ) አዝማች
ለመድኃኔ ዓለም ለቸሩ አባታችን፡፡ እንዘምር ሁላችን፡፡
እንዘምር እንዘምር እንዘምር በእልልታ÷ (2 ጊዜ)
ለመድኃኔ ዓለም ለሠራዊት ጌታ፡፡ እንዘምር በእልልታ
የጠፋውን ሊያድን ወረደ ከላይ÷ እንዘምር በእልልታ
የበጐች እረኛ አምላክ አዶናይ፡፡ እንዘምር በእልልታ

አዝማች
ትንቢት ተናገሩ ነቢያት በሙሉ÷ እንዘምር ሁላችን
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ፡፡ እንዘምር ሁላችን
ለብርሃናት ጌታ ለቸር ጠባቂያችን÷ እንዘምር ሁላችን
ሃሌ ሃሌ ሉያ እንበል ሁላችን፡፡ እንዘምር ሁላችን
አዝማች
ገብርኤል ተላከ ልደቱን አብሳሪ÷ እንዘምር በልልታ
ሥጋን ለብሶ ሊታይ ረቂቅ ፈጣሪ፡፡ እንዘምር በልልታ
ቀድሞ ኢሣይያስ እንደተናገረ÷ እንዘምር በልልታ
የእግዚአብሔር አብ ቃሉ ሥጋን አከበረ፡፡ እንዘምር በልልታ
አዝማች
በለበሰው ሥጋ አምላክ የኛ ተስፋ÷ እንዘምር ሁላችን
በመስቀል ተሰቅሎ የኛን ሞት አጠፋ፡፡ እንዘምር ሁላችን
አማኑኤል አንድ ቀን በግርማ ይመጣል÷ እንዘምር ሁላችን
ምርቱን ከገለባው እርሱ ይለየዋል፡፡ እንዘምር ሁላችን
አዝማች

## እዝራ ተናገራ

ተናገራ እዝራ ተናገራ (ዳዊት ዘመራ) አዝማች
ተናገራ እዝራ ተናገራ (ዳዊት ዘመራ)
እዝራ በመሰንቆ እያጫወታት÷ (ዳዊት ዘመራ)
ሳታውቀው አለፈች ያን መላከ ሞት፡፡ (ዳዊት ዘመራ)
አዝማች
ዉ-ኖች ቀለም ሆነው እንጨቶች ብዕር÷ (ዳዊት ዘመራ)
ቢጽፉት አያልቅም የማርያም ክብር፡፡ (ዳዊት ዘመራ)
አዝማች
ድንግል እመቤቴ የአምላክ እናት÷ (ዳዊት ዘመራ)
አንቺን የመረጠ ይከበር መለኮት፡፡ (ዳዊት ዘመራ)
አዝማች
ካንቺ ተወለደ ወገኑን ሊዋጅ÷ (ዳዊት ዘመራ)
ቀዳማዊ ቃሉ የእግዚአብሔር አብ ልጅ፡፡ (ዳዊት ዘመራ)
አዝማች
የምህረትን ዝናብ ያስገኘሽልን÷ (ዳዊት ዘመራ)
በሲኦል በረሃ እንዳንቀር ጠፍተን፡፡ (ዳዊት ዘመራ)
አዝማች

## ከእምነት አደባባይ

ከእምነት አደባባይ አሻግሬ አይቼሽ÷
እስካነጋግርሽ በውኔ አግኝቼሽ፡፡
አነጋግሪኝ ማርያም ጆሮዬ እንዲነቃ÷
ልቦናዬን አንቂው አድርጊው ጥሩ ዕቃ፡፡ (2 ጊዜ)

ኦ ድንግል ሆይ አንቺ አንቺ ግሩም ነሽ÷ አዝማች
የልቤ እንዲደርስ እንዴት ልንገርሽ፡፡

ኪሩቤል ሱራፌል አዕላፍ መላእክት÷
ክብርት ናት አሉ የጌታዬ እናት፡፡
መልአክ የሚያጽናናሽ በቀኝም በግራ÷
የሲና ሐመልማል የታቦር ተራራ፡፡
አዝማች
ከልጅሽ ትህትና ያንቺን ደግነት÷
የክርስቲያን ምርኩዝ የሆንሽ እመቤት÷
እንዴት ላመስግንሽ የልቤ እንዲደርስ÷
የትህትና እናት የፍቅር ውቅያኖስ፡፡
አዝማች
መዐዛሽ ያማረ ጥሩ ጽጌረዳ÷
እኔ አንቺን አምኜ ፍጹም አልጎዳ÷
ትህትናን ልጫማ ፍቅርንም ልልበስ÷
በአንቺ አማላጅነት በመንፈስ ቅዱስ፡፡
አዝማች
ኧረ እንዴት ቢሆን ነው የምስተካከለው÷
የልጅሽን ዐይኖች በዐይኖቼ የማየው፡፡
እርሱን የማይበት ምንም ዐይን የለኝ÷
እንቅልፍ ሲወስደኝ በሕልሜ ጥሪኝ፡፡
አዝማች
ኃይልና ብርታቴ አንቺው ሁኚልኝ÷
ከጠላት ስዋጋ ጋሻ ሆነሽኝ፡፡
ማልቀስ አስተምሪኝ መሳቁ ይብቃኝ÷
የሲኦል እሳቱ ሳያቃጥለኝ፡፡
አዝማች

ሳስብሽ በአርምሞ ሰማዩን ሰንጥቄ፥
የምድሩን ሳሳድድ እንዳልቀር ወድቄ፡፡
ሳስብሽ በአርምሞ ሰማዩን ሰንጥቄ፥
የምድሩን ሳሳድድ እንዳልቀር ወድቄ፡፡

## ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁኝ፤ አዝማች
በደስታ በሃሴት ስሙን እጠራለሁኝ፡፡
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና፥
ሌሊት አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና፡፡
ዘወትር አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና፡፡

ሕዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን፥
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን፡፡
በረከት የሞላው ዝማሬው ይገርማል፥ | (2 ጊዜ)
ከዕጣኑ ጋራ ወደ ላይ ይወጣል፡፡ |
አዝማች
ቀሳውስቱ ሌሊት ማህሌት ሲያቀርቡ፥
ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ፥
ብርሃኑን ለብሰን በደስታ ስንዘምር፥ | (2 ጊዜ)
ትዝታው ልዩ ነው ሕሊና ሲሰውር፡፡ |
አዝማች
ዕራእይ ነውና ኑና ተመልከቱ፥
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ፡፡
የጽጌው ማህሌት የትንሣኤው ደስታ፥ | (2 ጊዜ)
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስልህ ተርታ፡፡ |
አዝማች
ዕራእይ ነውና ኑና ተመልከቱ፥
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ፡፡
የጽጌው ማህሌት የትንሣኤው ደስታ፥ | (2 ጊዜ)
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስልህ ተርታ፡፡ |
አዝማች

## ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው÷
ከአምላካችን ፍቅር የሚለየን ማነው÷
መከራ ችግር ሥቃይ ወይስ መራቆት ነው?
መከራ ችግር ሥቃይ ወይስ መራቆት ነው? (2 ጊዜ)
አንፈራም አንሠጋም አንጠራጠርም÷
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም፡፡ (2 ጊዜ)
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው÷
ግንቡ ንጹሕ ውኃ መሠረቱ ደም ነው÷
ግንቡ ንጹሕ ውኃ መሠረቱ ደም ነው፡፡ (2 ጊዜ)
ሳይነጋ ተራምደን እንግባ በጥዋት÷
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት÷
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት፡፡ (2 ጊዜ)
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት÷
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት÷
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት፡፡ (2 ጊዜ)
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ÷
ለኛ ሲል በመስቀል እንደተሰቀለ÷
ለኛ ሲል በመስቀል እንደተሰቀለ፡፡ (2 ጊዜ)
በክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው÷
ከአምላካችን ፍቅር የሚለየን ማነው
መከራ ችግር ሥቃይ ወይስ መራቆት ነው
መከራ ችግር ሥቃይ ወይስ መረቆት ነው፡፡

## ከደጅህ ቆሜ

ከደጅህ ቆሜ አንኳኳለሁ÷
ድምጼንም ብትሰማ እገባለሁ፡፡ አዝማች
ካንተም ጋር እራት እበላለሁ÷
በዛ ያሉትንም እባርካለሁ፡፡
በራድ ወይም ትኩስ ብትሆን መልካም ነበር÷
እንደው ለብ ስላልክ ከንቱ ያንተ ነገር÷
አሁኑኑ ምረጥ ቦታህን አደላድል÷
ሥጋህንም መርጠህ ደግመህ እንዳትጣል፡፡

አዝማች

ሃብታም ባለፀጋ ሆኛለሁኝና፥
አያስፈልገኝም ሁሉም አለኝና፡፡
ጐስቋላና ምስኪን መሆንክን የማታውቅ፥
በደከመ ሕይወት ያለህ የምትዋዥቅ፡፡

አዝማች

በእሳት የነጠረ ወርቅን ተጎናጽፈህ፥
ሐፍረትህ እንዳይወጣ ነጭ ልብስህን ለብሰህ፥
የምትኳለውን ኩሉን ከኔ ገዝተህ፥
ሁሉንም አስተውል ልቦናህን ገልጸህ፡፡

አዝማች

እምወዳቸውን እገስፃቸዋለሁ፥
የኔ የሆኑትን እቆጣቸዋለሁ፡፡
እንግዲህስ ቅና ንስሐ ግባና
አዲስ ሰው ሁን ልጄ ዛሬም እንደገና፡፡

አዝማች

## ከዳዊት ዘር

ከዳዊት ዘር የተገኘች፥
በቤተ መቅደስ ያደገች፥ (አዝማች 2 ጊዜ)
በድንግልና የወለደች፥
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አማላጅ ነች፡፡

እሳተ ነበልባል የሆነውን ጌታ፥
የዓለሙን መድኅን ያንን ኃያል ጌታ፥
የወለደችልን ቅድስተ ቅዱሳን፥
ዛሬ እናመስግናት ድንግል ማርያምን፡፡

አዘማች

ታላቅ ግርማ ያለው ጌታችን ኢየሱስ፥
ካንቺ በመወለድ ዓለምን ለማደስ፥
ከዙፋኑ ወርዶ ያለም ቤዛ ሊሆን፥
ባንቺ ላይ አደረ የዓለም ብርሃን፡፡

አዝማች

ድንግል ሆይ መጥተናል ልንማፀንሽ፥
እንድታማልጅን ከኃያሉ ልጅሽ፥
ፀሎት አድርጊልን ማርያም እናታችን፥
ፍቅርን እንዲሰጠን ቅዱስ አባታችን።
አዝማች

## ከዚህ ከጠፋው ዓለም

ከዚህ ከጠፋው ዓለም ወደ ቤቱ ጠርቶ፥
ልጆቹን ሲሰበስብ በመንፈሱ መርቶ። አዝማች (2 ጊዜ)
እዩት ተመልከቱት የእግዚአብሔርን ፍቅር፥
ከሳሻችንን ጣለው ከመስቀሉ ኃይል ሥር።
ዓለም ያነቀችህ ወገኔ ቶሎና፥
ሸክምህን ሁሉ ለእየሱስ ስጥና።
ወገኔ ተጠንቀቅ በፅድቅ መንገድህ ሁን፥
ሳይመጣ በድንገት የጭንቅ ቀን አሁን።
አዝማች
መጠራታችንን መመረጣችንን፥
ወደፊቱ እየሄድን እናፅናው አሁን።
በልብ መታደስ እንለወጥ እንጂ፥
ዓለምን እንምሰል ናትና አሳሳች።
አዝማች
የመዳን ቀን ዛሬ መሆኑን አውቀህ፥
ነገ ዛሬ ሳትል አሁን ወስነህ፥
ከልብ ተፀጽተህ ይቅር በለኝ ካልህ፥
ሁሉን ይቅር የሚል ቸር አምላክ አለህ።
አዘማች
ኋላ ይህ ቀን አልፎ በሩ ይዘጋና፥
ንፁሕ ጥርስ ማፏጨት ይሆንብንና፥
ተው እንዳይፈርድብን ኢየሱስ ክርስቶስ፥
ልቡናህን አቅና በጊዜ ተመለስ።
አዝማች (2 ጊዜ)

## ከፍጡራን በላይ

ከፍጡራን በላይ ቅድስና÷
ቃላት የማይገልጹት ልዕልና÷
ጊዜ የማይሽረው ድንግልና፡፡

ይህን ሁሉ ፀጋ ያስተባበርሽ እናት÷ አዝማች (2 ጊዜ)
አምላክ ያደረብሽ ንጽሕት እመቤት÷
ክብርሽ የበዛ ነው ኪዳነ ምህረት፡፡

ማንም ያልተሰጠው ትህትና÷
ከመላእክት ሁሉ ንጽሕና÷
የነቢያት ትንቢት መልካም ዜና፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
ከፍጡራን በላይ ቅድስና÷
ቃላት የማይገልጹት ልዕልና÷
ጊዜ የማይሽረው ድንግለና
አዝማች (2 ጊዜ)

## ኪዳነ ምህረት

ኪዳነ ምህረት እመቤት÷
ለዓለም ሁሉ መድኃኒት፡፡(2 ጊዜ)
ቅድስተ ቅዱሳን ብፅዕት÷
አንቺ ነሽ ለአምላካችን እናት፡፡
ጌታ አንቺን ፈጠረሽ ልዩ አድርጎ÷
በሚያስደንቅ ምስጢሩ ተዋህዶ፡፡
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ÷
ያለሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ፡፡
እናትነት ድንግልና÷
አስተባብረሽ ይዘሻልና፡፡ (2 ጊዜ)
ድንግልም እናትም እመብርሃን÷
ንጽሕት ንጹሐን እኛን አማልጅን፡፡ (2 ጊዜ)

## ክርስቶስ ያንተ ሞት

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን፥ አዝማች
የስቃይህ ነገር እንደምን በቀጨን። (2 ጊዜ)

እራስ መውደድ ካለ አዋቂ ነኝ ማለት፥
ማንም ሰው አይችልም ለመኖር በሕይወት።
ብናስታውሳቸው የአይሁድን ካህናት፥
ባለማወቅ ሳይሆን የኦሪትን ትምህርት፥
በምቀኝነት ነው ጌታን የሰቀሉት።
አዝማች
በሰው እጅ መውደቅ ምንኛ ክፉ ነው፥
ባለ መብት ሆኖ እርሙን ቢለምነው፥
የዝናቡን ጌታ ውኃ ከለከለው፤
ሐሞትና ከርቤ ሆምጣጤም አጠጣው።
አዝማች
እርሱ ግን ይህ ሁሉ በላዩ ላይ ሲደርስ፥
የተናገረውን ቃል ኪዳኑን ሳይጥስ፥
ሰዎች አፌዙበት ፍርድን ተቀበለ፥
ከወንበዴዎቹ ጋር አብሮ ተሰቀለ።
አዝማች
ከፈጠረው ፍጥረት ታላቁ ሰው ሲሆን፥
ቢሠራም በስህተት የማይገባውን፥
ኃጢአቱን ሳትቆጥር ሳትገነዘበው፥
ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር አንተ ይቅር በለው።
አዝማች

**ወሮታህ ብዙ ነው÷ቀቀ**

**እግዚአብሔር ሆይ ወሮታህ ብዙ ነው÷ አዝማች** (2 ጊዜ)
**ለጠራህ ሰው ሁሉ የእጅህን ሰጠኸው።**
**በብዙ በረከት ሕይወቱን ዳሰስከው÷**
**እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ፍቅርህ የበዛ ነው÷**
**ፍቅርህ የበዛ ነው።**

**ለድንግል ሰጠሃት ንጹህ የሆነ ደም÷**
**ለዳዊት አደልከው የበገናን ምስጢር÷**
**ለያሬድ ሰጠኸው የማሕሌት ጥበብ÷**
**ታድያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈልኃል÷**
**ውለታህን ሰስብ ውስጤ ይገረማል÷**
**ውስጤ ይገረማል።**

**በኃጢአት ስንኖር አመጸኛ ሆነን÷**
**ልዩ የሆነውን ፍቅርህን አቃለን÷**
**አንተ ግን ኃጢአቱን ፈጽመህ እረስተህ÷**
**የመድኀን በረከት ሳትሳሳ ሰጠኸን÷**
**አመጸኛውን ሰው ታስደስተዋለህ÷**
**ታስደስተዋለህ።**

**ለድንግል ሰጠሃት ንጹህ የሆነ ደም÷**
**ለዳዊት አደልከው የበገናን ምስጢር÷**
**ለያሬድ ሰጠኸው የማሕሌት ጥበብ÷**
**ታድያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈልኃል÷**
**ውለታህን ሰስብ ውስጤ ይገረማል÷**
**ውስጤ ይገረማል።**
**አዝማች** (3 ጊዜ)

## ወደ ሕይወት ተመለስ

የይሁዳ ጉዞ አያዋጣምና፥ (አዝማች)
ዴማስ ወደ ሕይወት እባክህ ቶሎ ና፡፡ (2 ጊዜ)

በወንጌል ገበታ መመገብ ጀምረህ፥
ወንድሜ ተመለስ ወዴት ትሄዳለህ፡፡
ይጠራሃልና መስቀሉን ተመልከት፥
የወንጌል ቡቃያ እውነተኛ ሕይወት፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ቸርነቱን አይተህ ፍቅሩን ቀምሰኸዋል፥
በረድኤት ሕይወት ደስታማ ሞልቶሃል፡፡
ቅዳሴው ዝማሬው እጣኑ ሸትቶሃል፥
ዴማስ ሆይ ተመለስ ሕይወት ይሻልሃል፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ብዙ ክርስቲያኖች መንገዱን ጀምረው፥
የዓለም አሸንክታብ ድንገት ሲጠራቸው፥
ፈተና ሲመጣ ወንጌሉን ወርውረው፥
ሞትን ይመርጣሉ ሕይወትን ሰርዘው፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የመስቀሉ እምነት ከልብህ ሳይጠፋ፥
በእግዚአብሔር ጉባዔ መስክረህ በይፋ፥
ልጄ የተባልከው በጥምቀት ቀለበት፥
እንዴት ትሄዳለህ ተነጥቀህ ወደሞት፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

የክብር አክሊሉ አዘጋጅቶልሃል፥
አምላክ ለሽልማት ዴማስ ሆይ ይልሃል፡፡
ወዴት ትሄዳለህ እባክህ ተመለስ፥
ክብርህን አትተው እጫፉ ስትደርስ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

በወንጌል ገበታ መመገብ ጀምረህ፥
ወንድሜ ተመለስ ወዴት ትሄዳለህ፡፡
ይጠራሃልና መስቀሉን ተመልከት፥
የወንጌል ቡቃያ እውነተኛ ሕይወት፡፡

## ወደ አምላኬ ልመና

ወደ አምላኬ ልመና አቀርባለሁ፥
ኃጢአቴንም ትቼ ንስሐ እገባለሁ፡፡ አዝማች

በምድር ላይ ስኖር ተሳስቼ፥
መልካም መሥራቱን ሁሉ ጠልቼ፡፡
የጌታን ትዕዛዝ እረስቼ፥
ስኖር ቆየሁ በምድር ጠፍቼ፡፡
አዝማች
ኃጢአቴን ሁሉ ሳስበው፥
ጌታን ያሳዘንኩ በከንቱ ነው፡፡
ሕጉን ሳልጠብቅ እስከዛሬ፥
አሁን ተረዳሁ ከንቱ መኖሬን፡፡
አዝማች

## ወዳንተ እሰግዳለሁ

ወዳንተ እሰግዳለሁ ሳለሁ በሕይወቴ፥
ላንተም እገዛለሁ እስከ ዕለተ ሞቴ፥
አንተ ነህና መድኃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ፡፡ (2 ጊዜ)
ሳይመሽብኝ ቀኑ ሳይጨልም ድንገት፥
በጽድቅ ጐዳና ልጓዝ ወደፊት፥
ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት፡፡ (2 ጊዜ)
የነፍስ የሥጋዬ የሕይወቴ ቤዛ፥
አትበለኝ ችላ በደሌም ቢበዛ፡፡
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እሄዳለሁ፥
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እደርሳለሁ፡፡

## ወዳንተ ኢየሱስ ሆይ

ወዳንተ ኢየሱስ ሆይ ልቤ ይናፍቃል÷
የአምላክ በግ ሆነህ ስለኔ ሞተሃል:: (2 ጊዜ)
ሰላም ለኔ ሰጠህ ተሸክመህ ቅጣት÷
ጠባቂዬም ሆነህ አወጣኸኝ ከሞት:: (2 ጊዜ)
ስፍራን ያዘጋጀ ለኔ ባባቱ ቤት÷
ዐይኖቼ ያላዩት ብርሃኔ ኢየሱስ ነው:: (2 ጊዜ)
ከዓለም መሄዴ በደረሰ ጊዜ÷
ምራኝ በብርሃንህ ልግባ ወዳገሬ:: (2 ጊዜ÷

## ዘላዓለማዊ ቃልህ

ዘለዓለማዊ ቃልህ (2 ጊዜ) ይሁን ዕቃ ጦሬ÷
በልቤ ውስጥ ይደር÷ ይደር÷
በልቤ ውስጥ ይደር ዛሬ አሁን ዛሬ:: አዝማች (2 ጊዜ)

ምልክቴ ምልክቴ ሰንደቅ አብነቴ÷
ትጥቄ ትጥቄ የጦር ሜዳ ስንቄ÷
ወንጌሉ ወንጌሉ መድኅን ለሁሉ÷
ከአንተ ጋራ ልሁን ቀንም ሆነ ማታ÷
ሥጋዬ እንዲጐሽም ነፍሴ እንዲበረታ::
ከእንግዲህ ምን አለኝ ከቃሉ በላይ÷
የዘለዓለም ሕልሜ የሕይወቴ ሠናይ::
አዝማች
አይሰለች አይሰለች ቃሉ ምሥራች÷
ትምህርት ትምህርት የሐዋርያት÷
ለነፍስህ ለነፍስህ ወንጌል ነው ሃብትህ::
ማቴዎስ÷ ማርቆስ÷ ሉቃስ÷ ዮሐንስ÷
ሕያው ቤትን ሠሩ በመንፈስ ቅዱስ::
ይሁዳ÷ ያዕቆብ÷ ጴጥሮስ÷ ጳውሎስ÷
ሕያው ቤትን ሠሩ በመንፈስ ቅዱስ::
አዝማች

## ዛሬም እንደድሮው

ዛሬም እንደድሮው እግዚአብሔር ይሠራል፥ አዝማች
ሕያው አምላክ አለ መቼ ይረሳናል፡፡ (2 ጊዜ)
በሥጋ ነገሮች ከብደው ቢታዩንም፥
እግዚአብሔርን ማምለክ ሞኝነት አይደለም፡፡
በጽንዓት ፈንታ ፍርሃት ቢከበንም፥
እግዚአብሔር ታላቅ ነው ልጆቹን አይተውም፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
የውስጥ የውጪም ፈተና ቢከበን፥
ሠይጣን ጦርነቱን በእኛ ቢያውጅብን፥
የጌታችሁ ማዳን ወዴት አለ ቢለን፥
እግዚአብሔር ይመስገን በሁሉም ድል አለን፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ሁሌ በእምነት ፀንተን እንድንጓዝ እርዳን፥
ከተፈናም ባሕር በክንድህም አውጣን፡፡
በፍቅርህ በፀጋህ አምላክ ሆይ ተራዳን፥
በቅዱስ ፈቃድህ በመንገድህ ምራን፡፡ (2 ጊዜ)

## ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ

ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ (2 ጊዜ)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በሉ፥
መላእክትን ሁኑምስጋናን ጨምሩቅዱስ ቅዱስ በሉ፡፡
የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን አንሺው፥
በምስጋና መዝሙር እግዚአብሔርን ጥሪው፥
አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ፥
ከእኛ ጋር ይሆናል የሠራዊት ጌታ፡፡ (2 ጊዜ)
ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ (2 ጊዜ)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በሉ፥
መላእክትን ሁኑ ቅዱስ ቅዱስ በሉ፡፡ (2 ጊዜ)
ፍጥረታቶች ሁሉ ሰማያት ዘምሩ፥
ስለቅድስናው ውዳሴ ጀምሩ፥
ዳዊት ሆይ ተነሣ ስለጽዮን ዘምር፥
ከበሮ ይመታ በገና ይደርደር፡፡ (2 ጊዜ)

ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ÷ (2 ጊዜ)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በሉ÷
መላእክትን ሁኑ ቅዱስ ቅዱስ በሉ ምስጋና ጨምሩ።
ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር÷
ውለታው ብዙ ነው ለእኛ ያለው ፍቅር÷
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ÷
ለጌታ ለእግዚአብሔር ለሠራዊት ጌታ። (2 ጊዜ)
ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ÷ (2 ጊዜ)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በሉ÷
መላእክትን ሁኑ ቅዱስ ቅዱስ በሉ። (2 ጊዜ)
ባሕሩን አቋርጦ እስቲ ያሻግራችሁ÷
ተራራውን ንዶ ያቀለለላችሁ÷
በአውሎ ነፋሰ መሃል መንገድ ላለው ጌታ÷
ለንጉሥ ክርስቶስ እንዘምር በእልልታ። (2 ጌታ)
ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ÷ (2 ጊዜ)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በሉ÷
መላእክትን ሁኑ ቅዱስ ቅዱስ በሉ። (2 ጊዜ)

## የልመናዬን ድምፅ

የልመናዬን ድምፅ ሰምቷልና÷
እግዚአብሔርን ወደድኩት። አዝማች
ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሏልና÷
እግዚአብሔርን ወደድኩት።
ጭንቀትና መከራ ባገኘኝ ጊዜ÷
ጌታዬን ጠራሁ አድነኝ ብዬ።
እግዚአብሔር ቸር አምላክ መሐሪ ነውና÷
ነፍሴን አዳናት ጩኸቴን ሰማና።
አዝማች
እግሬን ከመሰናክል አድኗል÷
በቸርነቱ ነፍሴን አጥግቧል።
በሱ ለዘላለም እመካለሁ÷
በፊቱ ሁልጊዜ በቤቱ እኖረለሁ።

አዝማች
የችግረኛን ጩኸት ሰምቶ የሚራራ፥
አዳኝ ነው አምላኬ ከመከራ፡፡
ስለዚህ በእግዚአብሔር እታመናለሁ፥
በምስጋና ስሙን ሁልጊዜ እጠራለሁ፡፡
አዝማች
ወደድኩት አምላኬን ተመካሁበት፥
ስላከበረኝ በጠላቶቼ ፊት፡፡
ከትቢያ አንስቶ ሞገስን ሰጥቶኛል፥
በድል እየመራ ከዚህ አድርሶኛል፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## የመስቀሉ ነገር

የመስቀሉ ነገር ለኔ ታላቅ ጥበብ ነው፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ሞኝነት አይደለም እርሱ የዕውቀት ራስ ነው፡፡

እውር ለነበሩት ብርሃን ሰጥቷቸዋል፥
የታወሩት አይኖች በእርሱ ኃይል በርተዋል፡፡
አሁንም በልቤ እኔ አምነዋለሁ፥
የመስቀሉን ነገር ኃይል ነው እላለሁ፡፡
አዝማች
ከክፉ ፈተና ከሰይጣን ባርነት፥
አምላኬ አውጥቶኛል ሰጥቶኛል ነፃነት፡፡
መስቀል ተሸክሞ ለሚከተለው ሰው፥
ባርነት አይደለም መስቀል ነፃነት ነው፡፡
አዝማች
መንገድና ሕይወት እውነትም የሆነ፥
አለን ጌታ አምላክ ፍፁም የታመነ፡፡
እውነት ስለሆነ በርሱ እታመናለሁ፥
መንገድም ነውና በርሱም እጓዛለሁ፡፡
አዝማች

## የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር (ነገር) ሲገባን (4 ጊዜ) አዝማች
እመቤታችንን እናያታለን።

መስቀሉ ፍቅር የገባቸው (4 ጊዜ)
እመቤታችን አለች ከጎናቸው።
አባ ሕርያዕቆስ አባታችን፥
የመስቀሉ ነገር ሲገባው፥
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር፥
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር።

አዝማች

ነይ ነይ እምዬ ማርያም፥
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም።
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው፥
ተዋሕደ ስትል መድኃኔ ዓለም አለችው።
ሕሙማን ሲፈውስ ኢየሱስ አለችው።
ተሰቅሎ ስታየው መድኀኑ አለችው።
ለመናኔው ጸሎት ልዩ ዕጣን፥
የዋሻው ሻማ ነሽ እመብርሃን።
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን፥
ትናፍቂኛለኝ ምንልሁን።
ትርቢኛለኝ ምን ልሁን።
ድንግል እመቤቴ የእኔ ረዳት፥
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሳሻል፥
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል።
የእግዚአብሔር ሀገር የሚሉሽ፥
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ። (2 ጊዜ)
ቤተ ልሔም ስሀድ አይሻለሁ፥
ቀራንዮ ስሀድ አይሻለሁ፥
ፍጹም አትለዪም ከልጅሽ፥
ያንችስ ልዩ ነው ፍቅርሽ። (2 ጊዜ)
ነይ ነይ እምዬ ማርያም፥
ነይ ነይ እምዬ ማርያም።

### የማነ የማነ

የማነ የማነ የማነ ሕይወት÷ (2 ጊዜ)
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
የማነ የማነ የማነ ብርሃን÷ (2 ጊዜ)
ሃደረ ሃደረ ሀበ ማርያም፡፡
ከሴቶች ለይቶ አብ የመረጠሽ÷
ድንግል ማርያም ሆይ ብፅዕት አንቺ ነሽ፡፡
መከራ ሲገጥመን ጭንቅ ሲይዘን÷
የምታማልጅን ከፈጣሪያችን÷
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
የማነ የማነ ሕይወት÷ (2 ጊዜ)
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
ስምሽ ግርማ ያለው ኪዳነ ምሕረት÷
የኃጥአን አማላጅ የጌታዬ እናት÷
በአንቺ በተገኘው በማህፀንሽ ፍሬ÷
ዓለም ተቀድሶአል ይኸውና ዛሬ፡፡
ሃደረ ሃደረ ሀበ ማርያም፡፡
የማነ የማነ የማነ ብርሃን÷ (2 ጊዜ)
ሃደረ ሃደረ ሀበ ማርያም፡፡
የምሕረትን ዝናብ ያስገኘሽልን÷
በሲዖል በረሃ እንዳንኮነን÷
ከፍጥረታት ሁሉ ድንግል ልዩ ነሽ÷
ሁሉንም ማርልኝ ብለሽ ያለቀስሽ÷
አንቺ ነሽ አንቺ ኪዳነ ምሕረት፡፡
የማነ የማነ የማነ ሕይወት÷ (2 ጊዜ)
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
አንቺን መርጦ ለአንቺ ስለሰጠሽ ክብር÷
ቀለለልን ለእኛ የኃጢአት ቀንበር፡፡
የኃጢአት ባርነት ከእኛ እንዲጠፋ÷
ተማጽነንብሻል እንትሆኚን ተስፋ፡፡
ሃደረ ሃደረ ሃበ ማርያም፡፡
የማነ የማነ የማነ ብርሃን÷ (2 ጊዜ)
ሃደረ ሃደረ ሃበ ማርያም፡፡

የሲና ሐመልማል የሰው ልጅ ሕይወት÷
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት፡፡
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት÷
እንዲያድለን ሰላም ፍቅር አንድነት፡፡
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
የማነ የማነ የማነ ሕይወት÷
አንቺ ነሽ አንቺ ነሽ ኪዳነ ምሕረት፡፡
የማነ የማነ የማነ ብርሃን÷
ሃደረ ሃደረ ሀበ ማርያም፡፡

### የምሥራች ደስ ይበለን

የምሥራች ደስ ይበለን÷ (2 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
የዓለም መድኃኒት <u>ተወለደልን</u>፡፡ (2 ጊዜ)

ኢየሱስ የዓለም ቤዛ÷ (2 ጊዜ)
የዓለም ቤዛ <u>ተወለደልን</u>፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)
የምሥራች ደስ ይበለን÷ (2 ጊዜ)
ጌታችን ተወልዶ <u>አይተነው መጣን</u>፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)
ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ÷ (2 ጊዜ)
ፈልጋችሁ አምጡት <u>በቀን በጨለማ</u>፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)
ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት÷ (2 ጊዜ)
በኮከብ ተመርተው <u>ሕፃኑን አገኙት</u>፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)
ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው÷ (2 ጊዜ)
ወርቅና እጣኑን <u>በረከቱን ሰጥተው</u>፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች (2 ጊዜ)

## የሞት ሳብ አሳበው

የሞት ሳብ አሳበው እጅግም ተሰቃየ፥ አዝማች
በኃጢአታችን ምክንያት መከራውን መከራውን፥ መከራውን አየ።

ከጥፋት ሊያድነን ሕይወቱን ሰውቶ፥
ስለኛ ሞተልን በጣም ተሰቃይቶ።
የዓለሙ ንጉሥ የኛ ቸሩ ጌታ፥
ሕይወቱም አለፈች በዚያች በጐልጐታ።
አዝማች
በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁኝ አለ፥
በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ቀራንዮ ዋለ።
እየሱስ ተወጋ ጐኑንም በጦር፥
ወደ ጥፋት ሄደን እንዳንቸገር።
አዝማች
ምራቅ እየተፉ ሁሉም ዘበቱበት፥
ለማን እንደመጣ ምስጢሩን ሳያውቁት።
ክርስቶስ ለመነ ምሕረትን ካባቱ፥
እኛ እንዳንጠፋ በቁጣ መዓቱ።
አዝማች

## የሞት ኃይል ተዋርዶአል ዛሬ

እዩና እመኑ ሰዎች ድንጋዩ ተፈነቃቅሏል፥ አዝማች
ኢየሱስ በእኩለ ሌሊት በኃይሉ ሞትን ድል ነስቷል። (2 ጊዜ)

እልልታ ለዚህ ይገባል ግርግርታ ለዚህ ይገባል፥
የሞት ኃይል ተዋርዷል ዛሬ ሲኦልም ተመሰቃቅሏል። (2 ጊዜ)
አዝማች
መላእክቱ ነጭ ለብሰው ምሥራቹን አበሰሩ፥
ተነስቶአል ኢየሱስ ብለው ለዓለም ነገሩ። (2 ጊዜ)
አዝማች
እልልታ ለዚህ ይገባል፥ ግርግርታ ለዚህ ይገባል፥ | (2 ጊዜ)
የሞት ኃይል ተዋርዷል ዛሬ፥ ሲኦልም ተመሰቃቅሏል። (2)|
የሞት ኃይል ተዋርዶአል ዛሬ፥ ሲኦልም ተመሰቃቅሏል። (4 ጊዜ)

## የራማው ልዑል

የራማው ልዑል ገብርኤል፥ (2 ጊዜ)   አዝማች
ተመላለሰ መሃላችን ስምህን ጠርተን ንዓ ስንል፡፡ (2 ጊዜ)

ብርሃን ልብሱ እሳታዊ መልአክ፥
አንተ አማልደን ከመሐሪው አምላክ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ለአመኑብህ ለተማጸኑብህ፥
ፈጥኖ ደራሽ አለኝታቸው ነህ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
የአናንያ፥ የአዛርያ፥ የሚሳኤል ከለላቸው፥ (2 ጊዜ)
ከእሳት ነበልባል ያዳንካቸው፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ምስሶ አምባችን መጠጊያችን፥
ቅዱስ ገብርኤል ጠባቂያችን፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ዕለት ዕለት የምንማልድህ፥
ልጆችህን ይምራን መንፈስህ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

## የሰው ልጅ ሁልጊዜ

የሰው ልጅ ሁልጊዜ በጣም ደስ ቢለው፥ (2 ጊዜ)
ደግሞም የጭንቁን ቀን ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ (2 ጊዜ)
ምንም ቢደሰቱ ቢበዛ ምቾት፥ (2 ጊዜ)
አይቀርም በኋላ መወሰድ በሞት፡፡ (2 ጊዜ)
ችግር ቢደራረብ ኀዘን ቢከበን፥ (2 ጊዜ)
ከክርስቶስ ፍቅር ማንም አይለየን፡፡ (2 ጊዜ)
ሳናውቀው ዲያብሎስ እንዳይነጣጥለን፥ (2 ጊዜ)
ነቅተን እንጠብቀው የእምነትን ሠይፍ ይዘን፡፡ (2 ጊዜ)

**የቅዱሳን አምላክ**

**አብርሃምን ከካራን የጠራኸው ጌታ፥**
**ለሙሴ በሲና የሆንከው መከታ፥**
**ልጠፋ ነውና በሥጋ ፍላጎት፥**
**የይስሐቅም ቤዛ ሕይወቴን ታደጋት፡፡** (2 ጊዜ)

**የኤርትራን ባሕር በኃይልህ የከፈልክ፥**
**በሲና በረሃ ሕዝብህን የመገብክ፥**
**ኖኅ ከጥፋት ውኃ የዳነብህ አምላክ፥**
**ሎጥን እንዳአዳንከው ፍጹም ምሕረትህን ላክ፡፡** (2 ጊዜ)
**የተነበዩልህ ነቢያት በሙሉ፥**
**አምላክ ሰው ይሆናል ይወለዳል ሲሉ፥**
**ከዓሣ አንበሪ ሆድ ዮናስን ያወጣህ፥**
**ዓለም ልትውጠኝ ነው አይለየኝ ፀጋህ፡፡** (2 ጊዜ)
**ሥጋን ተዋህደህ በወሰንከው ሰዓት፥**
**የሞትክልኝ አምላክ ያዳንከኝ ከሞት ሞት፥**
**እንደወንጌልህ ሕግ የምኖር አድርገኝ፥**
**በመጨረሻው ቀን በቀኝህ እንድገኝ፡፡** (2 ጊዜ)
**አልቻልኩኝምና ልፈጽም ሕግህን፥**
**የሐዋርያት አጽናኝ ስጠኝ ብርታትህን፥**
**ምግባረ ጎደሎ ሆኛለሁና፥**
**የቅዱሳን አምላክ እርዳኝ እንድፀና፡፡** (2 ጊዜ)

## የብርሃን መውጫ

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል፥
የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል፡፡ (2 ጊዜ)
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር፥
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር፡፡(2 ጊዜ)
የዳዊት መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር፥
በገነት መካከል ያለች ለምለም ሣር፥
አፍርታልናለች ያለወንድ ዘር፡፡
እስቲ እናመስግናት እንዲህ በማለት፥
ቅድስት እናታችን ስብሐት ወቡርክት፥
አንቀጸ ብርሃን ማዕረገ ሕይወት፡፡
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት፥
በደህና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት፡፡ (2 ጊዜ)
እንድናገኝ ፍቅርን እንደ ሐዋርያት፥
እንደ እመቤታችን አርምሞ ትዕግሥት፥
ያድለን ፈጣሪ ፍጹም መድኃኒት፡፡

## የብርሃን እናት

ያዕቆብ በቤቴል በራዕይ ያያት፥ (2 ጊዜ) አዝማች
የብርሃን እናት ማርያም ቅድስት፡፡ (2 ጊዜ)

ልቤ በፍቅር እንዲቃጠል ጌታን ለማገልገል፥ (2 ጊዜ)
የጌታዬ እናት ለምኚልኝ ድንግል፡፡
የአንቺ ሐዘን ልቤ ይግባ እኔም እንዳነባ፥ (2 ጊዜ)
ቤዛዊተ ዓለም ድንግል የእኔ አበባ፡፡ (2 ጊዜ)
በልቤ ውስጥ እንዲያበራ ፍጹም እንዲታተም፥ (2 ጊዜ)
የክርስቶስ መስቀል መከራ ሕማም፡፡
አዝማች
በኃጢአት እንዳልወድቅ በዚች ክፉ ዓለም፥ (2 ጊዜ)
ቅድስት ሆይ ደግፊኝ እስከዘለዓለም፡፡ (2 ጊዜ)
ክርስቶስ ሆይ ቸሩ እረኛ ነፍሴ ስትወጣ፥ (2 ጊዜ)
በማርያም እናትህ ሕይወት እንዳላጣ፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች

## የብርሃን ጎርፍ

የብርሃን ጎርፍ ናት ድንግል እናታችን፥ (አዝማች)
ከሰማይ እያበራች ደስ አለው ልባችን።
ፍቅርሽም ሰላምሽም ድኅነት ይሁነን፥ ኦ ኦ
ፍጥረት በሙሉ በሙሉ ፊትሽ ይወድቃሉ፥
ጸጋሽ ይድረሰን (2 ጊዜ) ይሰጠን እያሉ።

የኔ ልብ ምን ጽድቅ አለው አንቺን ለማስተናገድ፥
የኃጢአት ጎተራ ነው የተሞላ በስስት፥
ኧረ እንዴት! ኧረ እንዴት! ድንግል ትኑርበት፥ ኦ ኦ
አትጸየፍም የኔን ልብ ታሰናዳዋለች፥
ስለ ኃጢአቴ የኔ እናት ምልጃ ታቀርባለች።
አዝማች
ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት፥
ሕሊናቸው ይመለስ እንጸልይ ለዚህ ጥፋት።
አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትመጣው፥ ኦ ኦ
እሷን ስንመልስ ጌታን ነው የምናሰቀይመው።
አዝማች

## የተለየች አገር

የተለየች አገር የጻድቃን ከተማ፥
ብስጭት ትካዜ በዚያች የማይሰማ፥
የመላእክት ውዳሴ ዝማሬ ሲሰማ፥
ምስጋና እልልታ በታላቋ ከተማ።

ጻድቃን ሰማዕታት የሚዘምሩባት፥
በታላቁ ግርማ ጌታ የሚታይባት፥ አዝማች
ቅድስቷ ሀገሬ ዕየን ሆይ ቅድስት። (2 ጊዜ)

ብርሃኗ የማያቋርጥ የፃድቃን ጮራ፥
ሰላም የሠፈረባት የጽዮን ተራራ፥
ከበጉ ዙፋን ፊት ከወንዙ ባሻግር፥
ያውና ይታያል የነአብርሃም መንደር።

አዝማች

ያችን ቅድስት ሀገር በሩቅ ተመልክቼ÷
ይህች ዓለም ከንቱ መሆኗን አይቼ÷
ከዚያች ቅድስት ሀገር ለመድረስ ጓግቼ÷
በመንፈስህ ልጓዝ ባንተ ተመርቼ።

አዝማች

የተመረጡ ለዚያች ለሰማያዊ መና÷
አ የኔ መድኃኒት ያንተ ብፅዕና÷
ሁሌ ምግባቸው ነው ያንተ ታላቅ ግርማ÷
ጽዮን ለሚኖሩ በቅድስት ከተማ።

አዝማች

## የኃያላን ኃያል

የኃያላን ኃያል ሁሉን ቻይ ስሙ ጌታ ነው÷ አዝማች
አምላክ ሆይ እንዳንተ ያለ ማነው።

የሠራዊት ጌታ በጣም የከበረ÷
ዓለማትን ሁሉ በቃሉ የፈጠረ÷
ሞትን ያሸነፈ የነፃነት ጌታ÷
ዘለዓለም የሚኖር ኃይሉ እንደበረታ።

አዝማች

ጌታ መሐሪ ነው ለሚለምነው÷
ትንሽ ትልቅ አይልም እርሱን ለሚያምነው።
እንዳይናወጥም ዓለሙን አፀናው÷
ስለዚህ ሁላችን ጌታን እናምልከው።

አዝማች

ሁሉን በያይነቱ አድርጐ ፈጥሮታል÷
ምሕረትም ከእሱ ነው ሁሉም ይቻለዋል።
ለዘለዓለም ኗሪ ሕያው ክርስቶስ÷
ልባችንን አድስ በቀና መንፈስ።

አዝማች

## የኃያላን ኃያል ልዑል እግዚአብሔር

የኃያላን ኃያል ኃያል ኃያል ልዑል እግዚአብሔር፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በምድር፥
ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በሰማይ በምድር፥
ኧኸ፥ ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በምድር፥
ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በሰማይ በምድር፡፡

ዘወትር በጐ ነገርን ምስጢርን (2 ጊዜ) የምታደርግልን፥ (2 ጊዜ)
ምስጋና ይድረስህ አማኑኤል ቸር አምላካችን፥
ምስጋና ይድረስህ አማኑኤል አማኑኤል ቸር አምላካችን፥
ኧኸ፥ ምስጋና ይድረስህ አማኑኤል ቸር አምላካችን፥
ምስጋና ይድረስህ አማኑኤል አማኑኤል ቸር አምላካችን፡፡
አዝማች
ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ (2 ጊዜ) ወልደ እግዚአብሔር ቃል፥ (2 ጊዜ)
ኢትዮጵያን ታረቃት ታረቃት በማርያም ድንግል፥
ኢትዮጵያን ታረቃት ታረቃት ታረቃት በማርያም ድንግል፡፡ ኧኸ፥
ኢትዮጵያን ታረቃት ታረቃት በማርያም ድንግል፥
ኢትዮጵያን ታረቃት ታረቃት ታረቃት በማርያም ድንግል፡፡
አዝማች
የይቅርታ እጅህን እጅህን እጅህን እንድትልክልን፥ (2 ጊዜ)
እንለምንሃለን አምላክ ሆይ በአንድነት ሆነን፥
እንለምንሃለን አምላክ ሆይ አምላክ ሆይ በአንድነት ሆነን፡፡
ኧኸ፥ እንለምንሃለን አምላክ ሆይ በአንድነት ሆነን፥
እንለምንሃለን አምላክ ሆይ አምላክ ሆይ በአንድነት ሆነን፡፡
አዝማች
አቤቱ ፈጣሪያችን አማኑኤል አማኑኤል እንጠራሃለን፥ (2 ጊዜ)
ኢትዮጵያን ከጥፋት አድነህ እንድትባርከን፥
ሕዝቦችዋን ከስደት አድነህ አድነህ እንድትባርከን፡፡
ኧኸ፥ ኢትዮጵያን ከጥፋት አድነህ እንድትባርከን፥
ሕዝቦችዋን ከስደት አድነህ አድነህ እንድትባርከን፡፡
አዝማች
በጻድቁ አባት አባት አባት በተክለ ሃይማኖት፥ (2 ጊዜ)
ጌታ ሆይ አድነን እባክህ ከዳግመኛ ሞት፥

ጌታ ሆይ አድነን እባክህ እባክህ ከዳግመኛ ሞት፡፡
ኧኸ፥ ጌታ ሆይ አድነን እባክህ ከዳግመኛ ሞት፥
ጌታ ሆይ አድነን እባክህ እባክህ ከዳግመኛ ሞት፡፡
አዝማች

## የነፍሳችን ቤዛ

የነፍሳችን ቤዛ የቅዳሳን ሃብት፥
ፀጋን የሚያስጠን ጾም ነው መድኃኒት፡፡
ቅዱሳን አባቶች ጾም ነው ጋሻቸው፥
ወደ ሕይውት መንገድ የሚመራቸው፡፡
የእሥራኤል ልጆች በሙሴ ሲመሩ፥
በጾም በፀሎት ነው ባሕር የተሻገሩ፡፡
ክፍላችን እንዲሆን ከቅዱሳን ጋራ፥
የፍቅር ቤታችንን በፀሎት እንሥራ፡፡
ልባችንም ይሁን በፀሎት ጐዳና፥
የአምላክን መንግሥት እንድንወርስ በጤና፡፡

## የአማኑኤል እናት

የአማኑኤል እናቱ ጸለየች፥ አዝማች
ኢትዮጵያን አድናት ጌታ ሆይ አድናት እያለች፡፡
የጌታዬ እናቱ ጸለየች፥
ኢትዮጵያን አድናት ጌታ ሆይ አድናት እያለች፡፡

የምወደው ሕዝቤ አሥራት የሰጠኸኝ፥
በርሃብ በእርዛት ምነው ተጎዳብኝ፡፡
የፍቅር ርሃብ የመንፈስ ድርቀቱ፥
ምነው መንገላታት ምነው መዋተቱ፡፡
አዝማች
ሆኖ ተሠርታለች መንፈሳዊ በአት፥
የእመቤቴ ሀገር ቃል የተገባላት፥
ክህደት ቅጥፈቱ ስለማይስማማት፥
ከእንግዲህ ወገኔ መመለስ አለበት፡፡
አዝማች

## የአምላክ እናት

የጻድቃን መመኪያ አምላክን የወለድሽ÷ (2 ጊዜ)
ድንግል ማርያም ሆይ የተመረጥሽ ነሽ።

አማን በአማን አማን በአማን የአምላክ እናቱ÷ አዝማች
ተማፅነናል ባንቺ ተማፅነናል ባንቺ ድንግል ወላዲቱ። (2 ጊዜ)
ነቢያቱ ሁሉ ዕፁብ ናት ያሉሽ÷
ነቢያቱ ሁሉ ድንቅ ናት ያሉሽ÷
ደመና ኤልያስ ድንግል አንቺ ነሽ።
አዝማች
የመላእክት እህት የጻድቃን እናት
ባንቺ መመኪያነት አገኘን ሕይወት።
አዝማች
እሳቱ ሳይፈጃት ጫፏ ሳይቃጠል÷ (2 ጊዜ)
ድንግል ማርያም ነሽ ሙሴ ያያት ቀጠል።
አዝማች
ባለሟልነትን ከአምላክ ያገኘሽ÷ (2 ጊዜ)
ምህረት ለምኝልን ለአገልጋዮችሽ።
አዝማች
የተዋህዶ ልጆች ባንድነት ሆነን÷ (2 ጊዜ)
ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን።

## የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት

እመቤታችን ማርያም ቅድስት÷
የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት÷ አዝማች
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል÷
የእግዚአብሔር ልጆች ይባርኩሻል።

ጌታ ኢየሱስን እንድንሰማ÷
ድምፁን ለዓለም እንድናሰማ÷
የሚላችሁን አድርጉ ብለሽ÷
አዝዘሽናል ፀጋ ተሞልተሽ።
አዝማች

የኛ መመኪያ የአምላክ እናት፥
የፀሐይ መውጫ የብርሃን መስኮት፥
የወርቅ መሶብ የመለኮት ቤት፥
ድንግል አንቺ ነሽ የዓለም እመቤት።

አዝማች

ከሰማይ ወርዶ ካንቺ ተወልዶ፥
በመስቀል ሞቶ ራሱን አዋርዶ፥
አምላክ ሰው ሆነ ሥጋሽን ለብሶ፥
ዓለምን ዋዘ ደሙን አፍሰሶ።

አዝማች

የመልአክ ቃል ባንቺ ያደረው፥
አልፋ ኦሜጋ ዘላለማዊው፥
የልጅነትን ሥልጣን ሊሰጠን፥
ሥጋን ለበሰ አምላክ ይመስገን።

አዝማች

አዳምን ነፃ ሊያወጣ ወዶ፥
ቃል ሥጋ ሆነ በተዋህዶ።
የታሰሩትን ነፍሳት ሊፈታ፥
በማኅፀንሽ አደረ ጌታ።

አዝማች

## የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይሥሐቅም ቤዛ (2 ጊዜ)
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ (2 ጊዜ)
የሐሠት ምስክር አቁመው ከሰሱት (2 ጊዜ)
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት (2 ጊዜ)
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ (2 ጊዜ)
ከሮማዊ መንግሥት እንዲኖር ተፋቅሮ (2 ጊዜ)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ (2 ጊዜ)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ (2 ጊዜ)
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ (2 ጊዜ)
በችንካር ላይ ቆመው ምንም አልሰለቹም (2 ጊዜ)
የብርሃን አክሊልን ለሰማያት ያደለ (2 ጊዜ)
የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ። (2 ጊዜ)

## የእቲስ አንበሳ

የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ፥
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና፥
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፥
ዮሐንስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡

የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ፥
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና፥
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፥
ሉቃስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡

ያለ አንድ ምክንያት የተጣልከው ቅዱስ፥
የዋሁ መነኮሴ አባ ሕርያቆስ፥
ቅዳሴው አይጉደል ናና ዛሬ ቀድስ፥
በዕጣኑ መዓዛ ድውያኑን ፈውስ፡፡ (2 ጊዜ)
የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ፥
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና፥
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፥
ማርቆስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡
የወንጌል አንበሳ ጐርጐርዮስ ፍጠን፥
ምሰሶው ሳይወድቅ መንጋው ሳይበተን፥
መብረቁ አትናቲዎስ ሞገዱን ገሰጠው፥
አፈ ጉባዔያችን በመስቀልህ ዳኘው፡፡ (2 ጊዜ)
የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ፥
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና፥
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፥
ጳውሎስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡
መርከቧን የሚያውክ ነፋስ መጥቶአልና፥
አምላካችን ፈጥነህ አድነን ቶሎ ና፡፡

ጴጥሮስ ሆይ ቀስቅሰው ልንጠፋ ነው ብለህ÷
ሞገዱ እያየለ ዝም እንዳይል ጌታ፡፡ (2 ጊዜ)
የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ÷
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና÷
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና÷
ጳውሎስ ሆይ ዝም አተበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡
ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ቶሎ ና÷
ናላዌ እረኛ ያስፈልጋልና÷
ሥጋውን የኀዳ ነፍሱን የጠቀመ÷
ነቀፋ የሌለው ግብሩ የታረመ፡፡ (2 ጊዜ)
የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ÷
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና÷
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና÷
መርቆርዮሰ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡
መርከቧን የሚያውክ ነፋስ መጥቶአልና÷
አምላካችን ፈጥነህ አድነን ቶሎ ና፡፡
ጴጥሮስ ሆይ ቀስቅሰው ልንጠፋ ነው ብለህ÷
ሞገዱ እያየለ ዝም እንዳይል ጌታ፡፡ (2 ጊዜ)
የእቲስ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ÷
ወገንህን ታደገው ከኃጢአት አበሳ፡፡
ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቶአልና÷
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና÷
ዮሐንስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና÷
ጊዮርጊስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና÷
ማቴዎስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና፡፡

**የዓለምን በደል**

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ፥
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ፥
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ፡፡

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ፥ አዝማች (2 ጊዜ)
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ፡፡

የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ፥
ተወልዶ ሲጠመቀ እኛን ለመቀደስ፥
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ፥
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ፥
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት፥
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት፥
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)
እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ፥
መንፈሰ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ፥
በእርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ፡፡
አዝማች
ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር፥
ሰማዩ ሲከፈት ሰውየው ሲናገር፥
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምስጢር፡፡
አዝማች

## የደናግል መመኪያ

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳምራ
ኢትዮጵያን ባርኪልን ድንግል ማርያም። (2 ጊዜ)
ከሦስቱ ሥላሴ ሥልጣን ተሰጥቶሻል፥
ሕሙማን በስምሽ ይፈወሱብሻል።
የረከሱ ሁሉ ተባሉ ቅዱሳን፥
ከአንቺ በተገኘው በዓለም መድኅን።
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም፥
ኢትዮጵያን ባርኪልን ድንግል ማርያም። አዝማች
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም፥
ሃገራችንን ባርኪልን ድንግል ማርያም።
የሰቀቀን ዘመን ያ የዓለም ፍዳ፥
በልጅሽ መስዋዕት ቀረልን የእኛ ዕዳ።
ሰላምን አገኘን በልጅሽ መሞት፥
ታረቅን ከአምላካችን ከሕይወት አባት።
አዝማች
ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ከአምላክ ሲነግረው፥
እነሆ እናትህ ትዘንልህ አለው።
ይህ ቅዱስ ሕይወት ቃል የማይለወጠው፥
ለተማፀነብሽ መመኪያ ሕይወት ነው።
አዝማች
የአዲሲቷ ምድር መግቢያ በራችን፥
በአንቺ ንጽሕና ተከፈተልን።
የቅዱሳን ክብር የነፃነት ስም፥
ለኃጥአን ተስፋ ነሽ ድንግል ዘለዓለም።
አዝማች

## የጌታ እናት

የጌታ እናት ስለሆንሽ÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ክብር ለአንቺ ለክብርሽ፡፡
ከሴቶች ሁሉ ተመርጠሻል÷
ፀጋን በእውነት ተሞልተሻል፡፡

ልጅሽ ኢየሱስ የዓለም ቤዛ÷
ደሙን አፍስሶ ሕዝቡን ገዛ፡፡
በአንቺ አድሮ እኛን ዋጀን÷
ሃሌ ሉያ ስሙ ይመስገን፡፡
አዝማች
የአንቺማ ልጅ ጌታ ኢየሱስ÷
ከንቱን ሕይወት የሚቀድስ፡፡
ምስክር ነን ለእርሱነቱ÷
ክብር አለው እንደ አባቱ፡፡
አዝማች
ይህን ጌታ ወለድሽልን÷
እኛን ከሞት ሊመልሰን፡፡
ተሰቀለ ተቀበረ÷
በምስጋና ደግሞ አረገ፡፡
አዝማች
አንቺ ድንግል ደስ ይበልሽ÷
የዓለም ቤዛ ልጅ ወለድሽ፡፡
ለዚህ ፀጋ ለዚህ ክብርሽ÷
ምስጋና ለአንቺ ከልጆችሽ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## የጌቶች ጌታ

እጅግ ኃያል ነው ስሙ እጅግ ገናና፥
የጌቶች ጌታ እየሱስ ይሠራል ገና፥ አዝማች
ድንቅን ይሠራል ገና ምን አየንና።

ወንዶች እኔ ከባሕር ዳር አሣ አጥማጅ ነበርኩኝ፡
ጌታ ግን ተነሣ ተከተለኝ አለኝ።
እከተልሃለሁ እኔ አንተን እስከሞት፥
እንዳላልኩት ሁሉ በመከራው ካድኩት።
እርሱ ግን ቂም የለው መልሶ ታረቀኝ፥
የቤተ ክርስቲያን መሠረት አረገኝ። አሜን

አዝማች

ሴቶች በሰዎች ዘንድ ስናቅ ስባል ያቺ መካን፥
እግዚአብሔር ቤት ሄጄ ሳለቅስና ሳዝን፥
ማኅፀኔን ከፍቶ ሳሙኤልን ሰጥቶኛል፥
ወላዷን አምክኖ እኔን አጽናንቶኛል። አሜን

አዝማች

ወንዶች - በመስቀል ላይ ሆኖ በመከራ ሲዋኝ፥
ካጠገቡ ሳልርቅ ተጨንቄ ቢያየኝ፥
ሕማሙን ታግሶ እኔን አይዞህ አለኝ፥
እነሷት እናትህ ብሎ ረዳት ሰጠኝ። አሜን

አዝማች

ሴቶች - በኃጢአት በዝሙት ተሳስቼ ስኖር፥
ትሙትልን አሉ በድንጋይ ትወገር።
ያልጠበኩትን ቃል ጌታ ተናገረ፥
ኃጢአትን አትሥሪ ምሬሻለሁ አለ። አሜን

አዝማች

ወንዶች - የማመልከው መስሎኝ ሳሳድድ ጌታዬን፥
ሳያል አለኝና ጠራኝ በብርሃን።
ስለምን ጌታህን ታሳድደኛለህ፥
ጳውሎስ እልሃለሁ ትከተለኛለህ። አሜን

አዝማች

ሴቶች - በወንድሜ መሞት እጅጉን አልቅሼ፥
ተጨንቄ ሳዝን ተስፋዬን ጨርሼ፥
እየሱስ ክርስቶስ ወደኔ መጣና
አልዓዛር ይነሣል አለኝ እንደገና። አሜን

## የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ፥ (አዝማች)
የበላየሰብ እመቤት የአምላክ እናት፥
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት፡፡

በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል፥
በምልጃሽም ጽድቅን አግኝተዋል፥
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል፡፡

አዝማች

የእሳት ባሕር ባንቺ ተሻረዋል፥
የሰይጣን ቁልፍ ባንቺ ድል ነስተዋል፥
ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል፡፡

አዝማች

ነፍሳቸውም ጽድቅን አግኝታለች፥
ሕይወታቸው በአንቺ ትድናለች፥
ድንግል ሆይ አትጣይን ትላለች፡፡

አዝማች

እኔም በአንቺ እታመናለሁ፥
የአምላክ እናት አትርሽኝ እላለሁ፥
በአማላጅነትሽ እድናለሁ፡፡

አዝማች

እኛም ባንቺ እንታመናለን፥
የአምላክ እናት አሳስቢን እንላለን
ባማላጅነትሽ እንድናለን፡፡

አዝማች

ምዕመናንም ባንቺ ያምናሉ፥
የአምላክ እናት አሳስቢን ይላሉ፥
በአማልጅነትሽ ይድናሉ፡፡

## ይመስገን እግዚአብሔር ይመስገን

በአንተ ደስ ይለኛል ሃሴት አደርጋለሁ÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ልዑል ሆይ ለስምህ ሁሌ እዘምራለሁ። (2 ጊዜ)
ይመስገን (2 ጊዜ) እግዚአብሔር ይመስገን። (2 ጊዜ)

በጽዮን ለሚኖር ለአምላክ ዘምሩ÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
በአሕዛብ መካከል ታምራቱን አውሩ። (2 ጊዜ)
አቤቱ አምላክ ሆይ ክንድህንም አንሳ÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
በግፍ ተራዳቸው ድሆችን አትርሳ። (2 ጊዜ)
ይመስገን (2 ጊዜ) እግዚአብሔር ይመስገን። (2 ጊዜ)
የዕውቀት ባለቤት ፈጽመህ አድነኝ÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ከዲያብሎስ ተንኮል እባክህ ታደገኝ። (2 ጊዜ)
አንተ ነህ አምላኬ አምባ መድኃኒቴ÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
መተማመኛዬ መጠጊያ ረዳቴ። (2 ጊዜ)
ይመስገን (2 ጊዜ) እግዚአብሔር ይመስገን። (2 ጊዜ)
ኃይልህ የሚያስታጥቅ መንገድ የሚያቀና÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን አለና። (2 ጊዜ)
ማን ያስተውላታል ጥፋት ስህተትን÷ (2 ጊዜ) (2 ጊዜ)
ከስውር ኃጢአቴ አንጻኝ አደራህን። (2 ጊዜ)
ይመስገን (2 ጊዜ) እግዚአብሔር ይመስገን። (2 ጊዜ)

## ይቅር በለን

አምላክ ሆይ ማረን÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ማረን አምላክ ይቅር በለን።

እውነተኛው ንጉሥ ለፍርድ ሲመጣ÷
ጻድቁን ሊያከብር ኃጥኡን ሊቀጣ÷
መለከት ሲነፋ ነጐድጓድ ሲሰማ÷
ክርስቶስ ሲገለጥ በሚያስደንቅ ግርማ።
አዝማች
የነበረው ሁሉ ሲሆን እንዳልነበር÷
ተነስተው ሲቆሙ ሙታን ከመቃብር÷
ፀሐይ ስትጨልም ሰማያትም ሲያልፉ÷
ምድርም ቀውጢ ስትሆን ቀላያት ሲጠፉ።

አዝማች

ፍጥረት ሲናጥ ሲርድ ግርማው እያስፈራው፥
የአዳም ዘር በሙሉ ሲቆም ከነሥራው፥
ማነው የሚገኘው በጎ ምግባር ሠርቶ፥
ቅዱሳንን መስሎ በሃይማኖት ጸንቶ።

አዝማች

በምድራዊ ሕይወት ትሩፋት የሠሩ፥
ጻድቃን ሲደሰቱ ተግተው ሲዘምሩ፥
ኃጥአን ሲጠፉቸው የሚሰውሩበት፥
እኛስ ከየት ይሆን የምንገኝበት።

አዝማች (3 ጊዜ)

## ይትባረክ እንደ አብርሃም

ይትባረክ እንደ አብርሃም(2 ጊዜ)
ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም።
አብርሃምና ሣራን ዘለዓለም፥
እንደባረካቸው ዘለዓለም፥
ዛሬም እንደዚሁ ዘለዓለም፥
እኒን ሙሽሮች ባርክ ዘለዓለም።
ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም።
ዳንኤል ወይንሸት፥ ዘለዓለም፥
እንኳን ደስ ያላችሁ፥ ዘለዓለም፥
በቅዱስ ጋብቻ፥ ዘለዓለም፥
ዛሬ አንድ ሆናችሁ፥ ዘለዓለም።
ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም።
አንድ ያደረገውን፥ ዘለዓለም፥
ጌታችን በቃሉ፥ ዘለዓለም፥
ሊለያይ አይችልም፥ ዘለዓለም፥
የሰው ልጅ በኃይሉ፥ ዘለዓለም፥
ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም።
ፍቅርና ሰላሙን፥ ዘለዓለም፥
ጌታ ያብዛላችሁ፥ ዘለዓለም፥
አንድነት ይስጣችሁ፥ ዘለዓለም፥
ትዕግሥት ያብዛላችሁ፥ ዘለዓለም።

ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም፡፡
　　የአብርሃም የሣራ÷ ዘለዓለም÷
　　ይሁን ጋብቻችሁ÷ ዘለዓለም÷
　　መልካም ዘርን አፍሩ÷ ዘለዓለም÷
　　አምላክ ይባርካችሁ÷ ዘለዓለም÷
ዘለዓለም (4 ጊዜ) ይትባረክ እንደ አብርሃም፡፡
　　ሙሽሪት ሙሽራው÷ ዘለዓለም÷
　　እንኳን ደስ ያላችሁ÷ ዘለዓለም÷
　　ተከበረ ዛሬ÷ ዘለዓለም÷
　　መልካም ጋብቻችሁ÷ ዘለዓለም፡፡

## ድንግል ሆይ

ድንግል ሆይ! (3 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
እንባሽ የፈሰሰው በአደባባይ÷
እንደምን አያማልድ÷
እንደምን አይታይ፡፡ (2 ጊዜ)

　　በኮረብታ ሆኖ በቀራንዮ አምባ÷
　　ከእግሩ ተጐንብሰሽ ያፈሰስሽው እምባ÷
　　ሁሉን አሳስቢና ድንግል ሆይ ለልጅሽ÷
　　ጌታ እንዲታረቀን አይለየን ምልጃሽ፡፡
አዝማች
　　የዓለም መድኃኒት የሰው ልጆች አዳኝ÷
　　ከነፍሿ ነፍስ ነስቶ ከድንግል ጋር ሲገኝ÷
　　ፍፁም ከማይጨክን ሩኅሩኅ ልጅሽ÷
　　ፀሎታችን ሰምተሽ አማልጅን እባክሽ፡፡
አዝማች
　　ከፍጥረታት በፊት እግዚአብሔር ያወቃት÷
　　ከዓለማት በፊት ፈጣሪ ያሰባት÷
　　አንፅቶ ቀድሶ ቃል ያደረብሽ÷
　　ማኅደረ አምላክ ድንግል አንቺ ነሽ፡፡
አዝማች (2 ጊዜ)

## ድንግል ሆይ እመቤቴ ማርያም

የብርሃን ደጃፍ ያደረብሽ ጌታ፥
ፈጥነሽ ድረሽልኝ ካለሁበት ቦታ፡፡
ሐዘኔ ቢበዛ ብወድቅ በኃጢአት፥
ታማልደኛለች ድንግል ከእኔ ጋር ናት፡፡

ድንግል ሆይ እመቤቴ የአምላክ እናት፥ አዝማች
ስደክም ሲያገኘኝ መከራ ሁኚኝ ረዳት፡፡

ጭንቀቴ ቢበዛ የሚያፅናና አጥቼ፥
ሕይወቴም ቢሸበር ሰላም ተነስቼ፥
ኃጢአት ቢፈትነኝ ተሸናፊም ብሆን፥
አማላጅ አለችኝ ለእኔ የምትለምን፡፡
አዝማች
ደስታዬ ርቆ ቢበዛ ሐዘኔ፥
ድንግል ሆይ አስታርቂኝ ለምኚ ስለእኔ፡፡
የኃጢአት ብዛት ሲያቆስለው መንፈሴን፥
ከጌታ ከልጅሽ አሰጪኝ ምሕረትን፡፡
አዝማች
ስምሽ ከሚነሳ በክፉ ነገር፥
እኔ ኃጢአተኛ ልወጋ በጦር፡፡
ከአዳም ልጆች ሁሉ ተመርጠሻልና፥
ለአንቺ ይገባሻል ክብርና ምስገና፡፡
አዝማች

## ድንግል መከራሽን

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታውሰው፥
በሔሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው፥ አዝማች
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት፥
እንደ ችግረኛ ተነሣሽ ስደት።

ኧረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ፥
ስትንከራተቺ በረሃውን ቆርጠሽ፥
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ፥
በሔሮድስ ዘመን መከራሽን አየሽ፥
መከራሽን መከራሽን አየሽ።

አዝማች

አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ፥
እንድትደርሺልኝ በመከራ ጊዜ።
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም፥
አትጨክኝብኝ አደራሽን ማርያም፥
አደራሽን አደራሽን ማርያም።

አዝማች

አቤት የዛን ጊዜ ያየሽው መከራ፥
ያለቀስሽው ለቅሶ ጭራሽ አይወራ።
ያማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
ዕድሜሽን ጨረስሽው ሁነሽ ኀዘንተኛ፥
ኀዘንተኛ ሁነሽ ኀዘንተኛ።

አዝማች

ደፋ ቀና ስትይ በፀሐይ ሐሩር፥
ስትንከራረተቺ በሽፍቶች መንደር፥
ሽፍቶቹም መጡና እንደልማዳቸው፥
ልብስሽን ለመግፈፍ ተዘረጋ እጃቸው፥
ተዘረጋ ተዘረጋ እጃቸው።

አዝማች

## ገዳመ ቆሮንቶስ

ገዳመ ቆርንቶስ የትምህርት ገበታ፥ አዝማች
የዓለሙ ንጉሥ ባንቺ ተንገላታ።

አርባ ቀንና ሌት ክርስቶስ የጾመው፥
ካጠፋነው በደል ሊያንደን እኮ ነው።
መሪያችን ኢየሱስ መሆኑን ካወቅን፥
ጾምና ፀሎትን ማነው የከለከለን።
አዝማች
ገዳመ ቆሮንቶስ የትምህርት ገበታ፥
ባንቺ ተፈተነ መምህርና ጌታ።
ጌታዬ ፈታኝህ አንተ ያሳፈርከው፥
ይፈታተናል ዛሬም ከኛ ጋር ነው።
አዝማች
ላቡና ደሙ እንደ ውሃ ወረደ፥
በአማኑኤል ኃይል ንስሃችን ነጐደ።
የዓለሙ ንጉሥ በደለኛ መስሎ፥
ሕይወቱን ሰጥቶናል ስለኛ ተሰቅሎ።
አዝማች

## ጋሻውን ይዞ በፈረስ

ጋሻውን ይዞ በፈረስ አቤት ማማሩ ቅዱስ ጊዮርጊስ፥ (2 ጊዜ)
ቡሩታዊትን አዳናት ዘንዶ እንዳይበላት ደራጎን። (2 ጊዜ)

| | | |
|---|---|---|
| ጋሻውን ይዞ በወጣትነቱ፥ | ጋሻውን | ይዞ |
| ዕድቅን ለይቶ አውቆ፥ | " | " |
| ለዘመቻ ወጣ፥ | " | " |
| ጋሻ ጦሩን ታጥቆ። | " | " |

አዝማች

| | | |
|---|---|---|
| ጋሻውን ይዞ በሕፃንነቱ፥ | ጋሻውን | ይዞ |
| በአምላኩ ተጠርቶ፥ | " | " |
| ድል ነሣ ጠላቱን፥ | " | " |
| ጥበብን ተሞልቶ። | " | " |

አዝማች
ጋሻውን ይዞ ኃይሉ ጊዮርጊስ÷ ጋሻውን ይዞ
የፅድቅ ወታደር÷ " "
በተጋድሎው ፀና÷ " "
በአምላኩ ሳያፍር:: " "
አዝማች
ጋሻውን ይዞ አራት ሞትን ሞተ÷ ጋሻውን ይዞ
ለሥጋው ሳይሳሳ÷ " "
ለአምላኩ ክብር÷ " "
ተቀበለ አበሳ÷ " "
የልዳው ንጉሥ÷ " "
ቅዱስ አንበሣ:: " "
አዝማች

## ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ እንደፈቃድህ መሆንን አስተምረን÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ላንተ የሚበጅ አካሄድ እንዲኖረን÷
ፈቃድህን አስተምረን::
የእኔነቴን ክብር ጥዬ ወደኋላ÷
ታምኜ እንድኖር በክንዶችህ ጥላ÷
ና ምራኝ ጌታዬ በፈቀድከው መንገድ÷
የሥጋዬ ፈቃድ ከእኔ እንዲወገድ::
አዝማች (2 ጊዜ)
ብቻዬን ስደክም በከንቱ ስለፋ÷
መንገዴንም ትቼ ባክኜ እንዳልጠፋ÷
ጌታዬ ሲደክመኝ ሁንልኝ ከፊቴ÷
ለዚያች ጽዮን ደጃፍ ትታደል ሕይወቴ::
አዝማች (2 ጊዜ)
ወዳንተ ስመጣ አትሂድ ይለኛል÷
ልቤን ለማሸፈት በዙሪያዬ ቆሞአል÷
ዲያብሎስ ግዛቱ ሊያደርገኝ አስቧል::
አንተ ግን ስለእኔ በመስቀል ሞተሃል::
ባፈሰስከው ደምህ ከእጁ አውጥተኸኛል::
አዝማች (2 ጊዜ)

## ጌታ ሆይ ተመልከት

ጌታ ሆይ ተመልከት ባክነዋል ጠፍተዋል ልጆችህ፥ አዝማች
ከእቅፍህ ወጥተው ርቀዋል ሄደዋል ከፊትህ፥
ጠፍተዋልና ጌታ ባሮችህ፥ | (2 ጊዜ)
ዛሬ ጥራቸው አምላክ ይወቁህ፡፡ |

የባከነው ያ ሰው በዓለም እንደዋዛ፥
አንተን እንዳያመልክ ለአንተ እንዳይገዛ፥
ዓለም ያነቀው ጌታ ፍጡርህ፥ | (2 ጊዜ)
ጥሪህን ይስማ ይቅረብ ከፊትህ፡፡ |
አዝማች
ሕይወቱን ለውጦ ያልተረዳ ቢኖር፥
ሕዝብህን መልሰው አንተን እንዲያከብር፡፡
በሠይጣን ወጥመድ የወደቁትን፥ | (2 ጊዜ)
ጌታ ሆይ አስብ ከአንተ የራቁትን፡፡ |
አዝማች
ከሕግህ ወጥቶ ጌታ ከትዕዛዝህ፥
ለሥጋ የአደረ አብልጦ ከቃልህ፥
ዛሬም አለና አንተን የሚረሳ፥ | (2 ጊዜ)
በደሉን ሳታይ ከውድቀቱ አንሳ፡፡ |
አዝማች
ለእርሱ መሞትህን ጌታ ያልተረዳ፥
ለምን እንደሚኖር እንዳለበት ዕዳ፥
ደንግጦአልና አምላክ ይህ ሕዝብህ፥ | (2 ጊዜ)
ጌታ ሆይ ጐብኘው በምህረትህ፡፡ |
አዝማች

## ጌታ ተነስቶአል

እንዘምር በእልልታ ለጌታ ኢየሱስ÷
የአብ የተስፋ ቃል ለሆነው ክርስቶስ፡፡
በዐይነ ሕሊናዬ ሲቃትት ሳየው÷
ነፍሴ ተዘጋጂ ላንቺ እኮ ነው ይህ ሁሉ ስቃይ፡፡

ጌታ ተነስቶአል ደስ ብሎናል÷ (2 ጊዜ) አዝማች
ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶናል፡፡ (2 ጊዜ)
ሁሉ ሲቻለው ኃይል እንደሌለው ሆኖ÷
በእንጨት ተሰቅሎ በደለኛ ተብሎ÷
ተገርፎ ተሰቅሎ የተሰዋውን÷
ነፍሴ አመስግኚው ሊያድንሽ ነው ደሙን ያፈሰሰው፡፡
አዝማች
ሁሉ ከንቱ ሲሆን ለመልካም ነበረ÷
ሞትን አሸንፎ ጌታችን ተነስቶአል÷
የሰማይ የምድሩን ሥልጣኑን ተረክቦአል÷
ሃሌ ሉያ ደስ ይበለን ጌታ ድል አድርጎአል፡፡
አዝማች

## ጌታ ተነስቷል በክብር

እውነት በእውነት ጌታ ተነስቷል÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ተነስቷል በክብር ሞትን ድል አድርጎአል፡፡ (2 ጊዜ)

በሞቱ አጥፍቶ ሙስና መቃብር÷
የሙታን በኵር ሆኖ ተነስቷል ጌታችን፡፡ (2 ጊዜ)
አዝማች
ሳጥን ቢደረደር አፈር ቢረበረብ÷
ድንጋይ በድንጋይ ላይ ደግሞም ቢደራረብ÷
ምድር አልቻለችም አምላኳን ለመቅበር፡፡
አዝማች
የንጉሦች ንጉሥ ሰማያዊ አንበሳ÷
ሞትን ድል አድርጎ በሰንበት ተነሣ፡፡ (2 ጊዜ)

አዝማች

ተቀድሰናል በጌታችን ደም፥
ፍቅሩንም የሰጠን እንደርሱ የለም፡፡
ሕያው ነው የሚኖር ለዘለዓለም፡፡

አዝማች

## ጌታ ተወለደ

ተወለደ ጌታ ተወለደ፥ አዝማች(3 ጊዜ)
ተወለደ አምላክ ተወለደ፡፡

አንዲት ብላቴና የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ፥
ጌታን ወለደችው በመላዕክት (ገብርኤል) አዋጅ፡፡
በሕቱም ድንግልና ተወለደ ጌታ፥
ዓለምን የሚያድን የሰዎች አለኝታ፡፡

አዝማች

ይህ ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት፥
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት፡፡
እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋህዶ፥
አየነው አምላክን እንደ ሰው ተወልዶ፡፡

አዝማች

አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም፥
በምድር ተፈልጐ እንደ አንቺ አልተገኘም፡፡
በሃሳብ በግብር ንፁሕ ስለሆነች፥
ለአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች፡፡

አዝማች

ፍፁም ድንግልና ክብር የተሞላች፥
እንደምን አምላክን በማህፀን ያዘች፡፡
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ፥
ወለደችው ድንግል የሔዋን አለኝታ፡፡

አዝማች

## ጌታ ይመጣል

በእርግጥ ጌታ (2 ጊዜ) ይመጣል÷ (2 ጊዜ)
ምርቱን ከግርዱ ይለያል÷ አዝማች (2 ጊዜ)
እንደ ሥራችን (2 ጊዜ) ይፈርዳል÷ (2 ጊዜ)
እንደተስፋው ቃል ይመጣል።

ከሰው ዝርያ ከመላእክት÷
የመውጣውን ቀን ማንም አያውቅ÷
በቅፅበት ጌታ ድንገት ይመጣል÷
ምርቱን ከአውድማ ይሰበስባል።
አዝማች (2 ጊዜ)
በደሙ ታጥበው በቃሉ ያሉ÷
ከጌታ ጋራ ይደሰታሉ።
በጽዮን ዙሪያ ይሰለፋሉ÷
በዙፋኑ ፊት ይዘምራሉ።
አዝማች (2 ጊዜ)
በአመፃ ሥራ የተሳተፉ÷
ከጥፋት ጋራ የተሰለፉ÷
በቁጣው በትር በሰይፍ ይወድቃል÷
ፀጉር ይናጫል ጥርሱን ያፏጫል።
አዝማች (2 ጊዜ)
በመላእክቱ የመለከት ድምፅ÷
በክብሩ ውበት ጌታ ሲገለጽ÷
በማይጠፋ እሳት ወድቀህ እንዳትቀር÷
ከአሁኑ እወቅ መኖር በምግባር።
አዝማች (2 ጊዜ)

## ጌታችን ሲመጣ

ጌታችን ሲመጣ በግርማ መንግሥት፥ (2 ጊዜ) አዝማች
ተማፅነናል በአንቺ ድንግል ወላዲቱ። (2 ጊዜ)

በመላክት ጋራ በግርማ ሲመጣ (2 ጊዜ)
እንደ እሳት ይነዳል የጌታችን ቁጣ፥ (2 ጊዜ)
ምድርም አደራዋን ለርሱ ስታገባ፥ (2 ጊዜ)
ያን ጊዜ ይወርዳል የኃጥአን ዕንባ። (2 ጊዜ)
አዝማች
ፈቃዱን ያደረጉ ቅዱሳን በሙሉ፥ (2 ጊዜ)
እንደ ተደሰቱ በቀኝ ይቆማሉ። (2 ጊዜ)
አቤቱ ፈጣሪ አስብ ቃልህን፥ (2 ጊዜ)
የዘለዓለም ሕይወት አለ ያልከውን። (4 ጊዜ)

## ጌታችን ሲመጣ

ጌታችን ሲመጣ በፍርድ ዕለት፥ አዝማች (2 ጊዜ)
ምን ትመልስ ይሆን ወንድም የዛን ዕለት።
ጌታችን ሲመጣ በፍርድ ዕለት፥
ምን ትመልሽ ይሆን እትህ የዛን ዕለት። አዝማች (2 ጊዜ)

ጌታችን ሲመጣ በዚያች ክብርት ዕለት፥
ምን አዘጋጅተናል የምንመልስለት?
ለነፍሳችን ክብር መሰብሰብ እንወቅ፥
በቅዱሳኑ ፊት በፍርድ ሳይጠየቅ።
አዝማች
ጌታችን ሲመጣ ከመላዕክት ጋራ፥
ለመቆም እንድንችል አብረን ከሱ ጋራ፥
በተሰበረ ልብ ቀርበን በአንድነት፥
መጠበቅ አለብን ያችን የፍርድ ዕለት።
አዝማች

ጌታችን ይለያል ስንዴውን ከእንክርዳድ፥
ዳግመኛ ሲመጣ በዓለም ላይ ሊፈርድ።
ፃድቃን ሲደሰቱ የኃጥአን ፋንታ፥
ሰሚ የሌለው ነው የዛን ዕለት ዋይታ።
አዝማች
ወንድሞች እህቶች በእምነታችን ፀንተን፥
የአባቴ ብሩካን እንባል ሁላችን።
የመንግሥቱ ወራሽ እንዲያደርገን ጌታ፥
በፀሎት እንቅረብ በእምነት እንበርታ።
አዝማች

### ግነዩ ለእግዚአብሔር

| | |
|---|---|
| ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር፥ | (2 ጊዜ) |
| እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም። | (2 ጊዜ) |
| እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ፥ | (2 ጊዜ) |
| የዓለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ። | (2 ጊዜ) |
| በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ዕንስ፥ | (2 ጊዜ) |
| ለድኩማኖች ብርታት ነው ለሕሙማን ፈውስ። | (2 ጊዜ) |
| ከሰማይ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ፥ | (2 ጊዜ) |
| መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ። | (2 ጊዜ) |
| በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችንን ፋቀ፥ | (2 ጊዜ) |
| በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን። | (2 ጊዜ) |
| እመቤታችን እናታችን ማርያም፥ | (2 ጊዜ) |
| የተማፀነሽ ይኖራል ለዘለዓለም። | (2 ጊዜ) |
| ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ፥ | (2 ጊዜ) |
| በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ። | (2 ጊዜ) |

## ጐልጐታ

ለአዳም ወገኖች እጅግ ተሰቃይቶ÷
ፀለየ ወደ አባቱ ተለይቶ።
ብርሃኑን እያየ ሲወጣ ተራራ÷
ገረፉት አምላኬን በየተራ።
ጐልጐታ (2 ጊዜ) የጣር ቦታ÷
የዓለም መድኃኒት በዚያ ተንገላታ÷
በጐልገታ ተንገላታ ተንገላታ።
መስቀል ተሸክመህ ስትደፋ ለኔ÷
ተራራ ስትኳትን ለእኔ÷
ወደ ክፉ ግብዣ ሲጠባበቅ አሁን÷
ገረፉት አምላኬን በሀሰት።
አዝማች
ተጠማሁ ተጠማሁ ተጠማሁ ሲላቸው÷
ሆምጣጤ አመጡለት እንዲጠጣ ብለው።
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ÷
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ።
አዝማች

## ጐልማሳነቴን ደስ ወደ አሰኛት

ጐልማሳነቴን ደስ ወደ አሰኛት ጌታ እጓዛለሁ÷
ለእግዚአብሔር ምስጋና ከልቤ አቀርባለሁ። አዝማች (2 ጊዜ)

በእውነትና በጽድቅ ልሰማራ÷
ሕይወቴ በቃልህ ትመራ።
ወደ ቅድስና ተራራ÷
ጉዞዬ ይሁን ከአንተ ጋራ።
አዝማች
በንስሐ ጥሪ ደወል ድምፅ÷
ኃጢአቴም በሙሉ ይገለጽ።
በመልካም ሥራ ላይ ልታነጽ÷
መንፈስህ በልቤ ውስጥ ይሥረጽ።

አዝማች

 የብርሃኑን መንገድ አሳየኸኝ÷
 በታላቁ ፍቅርህ የማርከኸኝ።
 ኃይልህ የማይጠፋ ነውና÷
 ጌታ ይገባሃል ምስጋና።

አዝማች

## የጥምቀት መዝሙር

ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ÷ (2 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
ሃሌ ሉያ (4 ጊዜ)

 ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች÷
 አልችለውም ብላ ወደ ፊት ሸሸች።
 ብርሃነ መለኮት በወንዙ ሲሞላ÷
 ዮርዳኖስም ሸሸ ቀረ ወደ ኋላ።

አዝማች (2 ጊዜ)

 ማን ነበር የመጣው ደመናውን ጭኖ÷
 መንፈስ ቅዱስ ታየ በእርግብ አምሳል ሆኖ።
 ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና÷
 አብም ተናገረ ሆኖ በደመና።

አዝማች (2 ጊዜ)

 ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ ዓመት÷
 ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት።
 ሰማይ ተከፈተ ወኮነ ፀአዳ÷
 ከሩቅ መጥቶአልና አብ ታላቁ እንግዳ።

አዝማች (2 ጊዜ)

 እልል በይ ዮርዳኖስ የዕድቅ መገኛ÷
 የሕይወት መሰላል ድህነታችን የእኛ።
 ቀላያት አብረኸት ብዙዎች እያሉ÷
 እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ።

አዝማች (2 ጊዜ)

## ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ

ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ፥ (2 ጊዜ) አዝማች (2 ጊዜ)
ሃሊ ሉያ። (4 ጊዜ)

ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች፥
አልችለውም ብላ ወደፊት ሸሸች።
ብርሃነ መለኮት በወንዙ ሲሞላ፥
ዮርዳኖስም ሸሸ ቀረ ወደ ኋላ።
አዝማች
ማን ነበር የመጣው ደመናውን ጭኖ፥
መንፈስ ቅዱስ ታየ በእርግብ አምሳል ሆኖ።
ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና፥
አብም ተናገረ ሆኖ በደመና።
አዝማች
ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ ዓመት፥
ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት።
ሰማይ ተከፈተ ወኮነ ፀአዳ፥
ከሩቅ መጥቷልና አብ ታላቁ እንግዳ።
አዝማች
እልል በይ ዮርዳኖስ የፅድቅ መገኛ፥
የሕይወት መሰላል ድኅነታችን የእኛ።
ቀላያት አብረኸት ብዙዎች እያሉ፥
እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ።
አዝማች (2 ጊዜ)

## ፍቅሩ አይለወጥም

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ አዝማች (2 ጊዜ)
ለስሙ ይሁን ምስጋና

ፍቅሩ አይለወጥም ቃሉም አያረጅም፥
ክብር ለርሱ ይሁን እስከ ዘለዓለም።
እግዚአብሔር ነውና መድኃኒቴ ክብሬ፥
አወድሰዋለሁ በማቅረብ ዝማሬ።

አዝማች

አልፋና ኦሜጋ ሁሉን የሚገዛ÷
ዓለም በእጁ ያለች ጥበቡ የበዛ።
ሁሉን የምትችል ፈጣሪ ጌታዬ÷
ሃሌ ሉያ ላንተ ጋሻ መከታዬ።

አዝማች

ውለታው በዛብኝ ያደረገልኝ÷
በፊትህ ወደቅሁኝ ተንበረከኩኝ።
ሃሌ ሉያ ይክበር የኔ አምላክ መድኃኔ÷
እያልኩ ልጽናና ቆርጫለሁ እኔ።

አዝማች

የነገሩትን የማይረሳው ጌታ÷
የለመኑትን የማይነሳው ጌታ።
ሳይወሰንለት ሰዓትና ቦታ÷
ምስጋና ይገባዋል ከጥዋት እስከ ማታ።

አዝማች

ሥራው ታላቅና እጅግ ድንቅ ነው÷
ፍርዱም በቅንነት የተሞላ ነው።
መሐሪና ፍጹም ለሆነው ጌታችን÷
ክብርና ምሥጋና ለእርሱ ብቻ ይሁን።

አዝማች

## ፍጡራን ይስገዱ

ፍጡራን ይስገዱ ለከበረው ለርሱ÷ አዝማች (2 ጊዜ)
ለኃያሉ ጌታ ምሥጋና ያድርሱ።

ሁሌ እንዘምርለት እልል እንበልለት÷
መሐሪ ጌታችን ደስ እንዲለው በዕውነት።
ቅድመ ዓለም የነበር ዓለም ሳይፈጠር÷
ጌታ አምላካችን ለዘለዓለም ይክበር።

አዝማች

ለፈረን ጌታ ምሥጋና እናቅርብ÷
ለዘለዓለም ከብሮ ሰይጣንም እንዲያፍር።
በለቅሶ በፀሎት እንትጋ ሁላችን
ይቅር ባይ ነውና ቸሩ አምላካችን።

አዝማች
ጌታን አናስቀይም ሰዎች በሥራችን፥
ጥበብን ልቦናን ሁልጊዜ እንለምን።
ይሰጣል ጌታችን ቸር አምላክ ነውና፥
ምሥጋና እናቅርብ ዛሬም እንደገና።
አዝማች

## ወረብ

1. በአምሳለ ያፍ አምሳለ ያፍ፥
ፀአዳ እንተ ትመስል ማርያም ድንግል። (2 ጊዜ)

ይእቲ ማርያም ድንግል፥
ደመና ቀሊል እሙ ለእግዚእነ። (2 ጊዜ)

2. ሰላም፥ ሰላም፥ በአርያም፥ (2 ጊዜ)
ሰላም ለእግዚእትዬ ለማርያም። (4 ጊዜ)

ኣዕርጊ ፀሎትነ ውስተ ኖሃ ሰማይ፥ (2 ጊዜ)
ከመ ታስተሥርይ ኃጢአትነ። (4 ጊዜ)

3. መላከ ሰላም ተናገራ፥ (2 ጊዜ)
ወይቤላ ተፈስሂ ብፅዕት። (4 ጊዜ)

መላከ ሰላም ተናገራ፥ (2 ጊዜ)
ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ አላት። (4 ጊዜ)

4. መሠረተ ሕይወት ማርያም፥
ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ፥ (2 ጊዜ)
ለወልድኪ (2 ጊዜ) አምሳለ ደሙ። (2 ጊዜ)

5. እንተ በምድር ስረዊሃ÷
ወበ ሰማይ አይፆኪሃ ÷ (2 ጊዜ)
ሃረገ ወይን÷ ሃረገ ወይን÷
ድንግል ሃረገ ወይን። (2 ጊዜ)

6. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስለአደረግልኝ ምን እመልሳለሁ÷ (2 ጊዜ)
ምሥጋና ነው እንጂ (2 ጊዜ) ሌላ ምን እላለሁ። (2 ጊዜ)

7. እናመስግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ÷ (2 ጊዜ)
በሞቱ ሞትን ሻረልን እንዳንረታ። (2 ጊዜ)

8. ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መድኃኒት÷ (2 ጊዜ)
እናወድሳት እናመስግናት እንውደዳት። (2 ጊዜ)

9. ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ÷ (2 ጊዜ)
ታምሩን ለዓለም ንገሩ ÷ (4 ጊዜ)
ድንቅ ሥራውን መስክሩ።

10. ተዋህዶ ንፅሕት ቅድስት እምነታችን÷ (2 ጊዜ)
ኑሪ ለዘለዓለም ተከብረሽ በአምላካችን። (2 ጊዜ)--(2 ጊዜ)

11. መድኃኔ ዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ÷ (2 ጊዜ)
ደስ ይበለን (2 ጊዜ) እልል በሉ (2 ጊዜ) አዳነን በማይሻር ቃሉ። (2 ጊዜ)

12. ክርስቶስ ተንሥአ በአማን÷
ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን።
አማን በአማን መድኃኔ ዓለም (2 ጊዜ)
ዲያብሎስ ተመታ በመስቀል÷ (2 ጊዜ)
የአዳም ልጆች ሁሉ እንበል እልል። (2 ጊዜ)

13. አማን በአማን አማን በአማን፥ (2 ጊዜ)
ተንሥአ እምነ ሙታን። (2 ጊዜ)

14. አምላካችን አዳነን በማይሻር ቃሉ፥ (2 ጊዜ)
ደስ ይበለን (2 ጊዜ) እልል በሉ፥ (2 ጊዜ)
አዳነን በማይሻር ቃሉ።
ደስ ይበለን (2 ጊዜ) እልል በሉ፥ (2 ጊዜ)
አዳነን በኃድለ መስቀሉ።

15. ትንሣኤከ ለእለ አመነ፥ (2 ጊዜ)
ፈኑ ዲቤነ ብርሃነከ። (2 ጊዜ)

ለምናምነው ትንሣኤህን፥ (2 ጊዜ)
ብርሃንና ሰላም ጌታ ሆይ ስጠን። (2 ጊዜ)

16. አምላክ ተነሳልን ተነሳልን፥ (2 ጊዜ)
እልል እንበል ደስ ይበለን።
ሞትን በሞቱ ደመሰሰልን፥
የሕይወት በርም ተከፈተልን፥
አምላክ ተነሳልን ተነሳልን፥ (2 ጊዜ)
እልል እንበል ደስ ይበለን።
የሲኦልን በሮች ሰባብሮ፥
አዳራሿም ገብቶ በርብሮ፥
አምላክ ተነሳልን ተነሳልን፥ (2 ጊዜ)
እልል እንበል ደስ ይበልን።

17. ለምናውነው ትንሣኤህን፥ (2 ጊዜ)
ብርሃንና ሰላም ጌታ ሆይ ስጠን። (2 ጊዜ)

18. እናመስግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ፥ (2 ጊዜ)
በሞቱ ሞትን ሻረልን እንዳንረታ። (2 ጊዜ)

19. <u>በኪዳነ ምሕረት በዓል የሚባል</u>

ክነፈ እርግብ በብሩር ዘግቡር፥
ወገበዋቲ ሃኒ ሐመልማለ ወርቅ። (2 ጊዜ)
አንቲ ምሥራቀ ወወልኪ ፀሐዩ ፅድቅ አማን በአማን፥
<u>አማን በአማን</u> (2 ጊዜ) ኢየሐልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ። (2 ጊዜ)

20. <u>ለቅዱስ ገብርኤል በዓል የሚባል</u>

ሠለስቱ ደቂቅን ያዋጣሀ ከእሳት፥(2 ጊዜ)
እኛንም ታደገን ታደገን ሊቀ መላእክት፥
እኛንም ታደገን ታደገን ገብርኤል ሊቀ መላእክት፥ (2 ጊዜ)
ኸኸ
ቂርቆስ ኢየሉጣን ያወጣሀ ከእሳት፥ (2 ጊዜ)
እኛንም ታደገን ታደገን ሊቀ መላእክት።
እኛንም ታደገን ታደገን ገብርኤል ሊቀ መላእክት። (2 ጊዜ)
ኸኸ
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣሀ ከእሳት፥(2 ጊዜ)
እኛንም አድነን አድነን አምላከ ምሕረት።
እኛንም አድነን አድነን አድነን አምላከ ምሕረት። (2 ጊዜ)
ኸኸ
አድነን አምላከ ምሕረት። (2 ጊዜ)

21. ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፥ (2 ጊዜ)
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብዕ ሃሌ ሉያ።
ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ፥ አማን ሃሌ ሉያ።

22. አማን በአማን አማን በአማን፥ (2 ጊዜ)
መንክር ስብሐተ ልደቱ።(2 ጊዜ)

23. በቤተ ልሔም <u>ተወልደ</u> (2 ጊዜ) አማኑኤል፥ (2 ጊዜ)
እምዘርዓ ዳዊት (2 ጊዜ) ተወልደ አማኑኤል።

24. እምሰማያት ወረደ፥ ወእማርያም ተወልደ፥ (2 ጊዜ)
ኧኸ! ከመይኩን ቤዛ (2 ጊዜ) ለኩሉ ዓለም፥ (2 ጊዜ)
ለብሰ ሥጋ ማርያም።
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወልደ፥ (2 ጊዜ)
እንዲሆነን ቤዛ (2 ጊዜ) ለዓለሙ ሁሉ፥ (2 ጊዜ)
ለበሰ የማርያምን ሥጋ።

25. በጐለ እንስሳ፥ በጐለ እንስሳ፥ (2 ጊዜ)
በጐለ እንስሳ ተወልደ አማኑኤል፥ (2 ጊዜ)
በጐለ ሰከበ በአፅርቅት ተጠብለለ፥ (2 ጊዜ)
ቤዛ ኩሉ ዓለም (2 ጊዜ) ዮም ተወልደ። (2 ጊዜ)

26. ክንፎ ፀለላ፥ ክንፎ ፀለላ፥ ክንፎ ፀለላ፥ (2 ጊዜ)
ተፈሥሒ ለድንግል ይቤላ። (2 ጊዜ)

27. ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ - ዘወርቅ፥ (2 ጊዜ)
ተዋነይ በጽድቅ ተዋነይ በጽድቅ፥ (2 ጊዜ)
ገብርኤል ሀመልማለ ወርቅ።

28. ተወከፍ ፀሎተነ ውስተ ኖኃ ሰማይ፥ (2 ጊዜ)
ገብርኤል ገብርኤል - ገብርኤል ገብርኤል፥
ገብርኤል መልዓከ ሰላም።

29. እግዚእ አዕምሮ እግዚእ አዕምሮ - እግዚዕ አዕምሮ፥ (2 ጊዜ)
ወዜናዊ ጥበብ፥ ወዜናዊ ጥበብ ከሰተ ለነ። (2 ጊዜ)

30. ፈነዎ ለገብርኤል ምዕአተ ዚአሁ፥ (2 ጊዜ)
ይኸ ስብክ ፈነዎ ለገብርኤል፥ (2 ጊዜ)
ዘእም ቅድመ ዓለም ኧኸ! (2 ጊዜ)
ኅላዌሁ ዓለም ዘእምቅድመ ዓለም (2 ጊዜ)

31. ዜናዊ ስቡህ - ስቡህ ዘለዓለም፥ (2 ጊዜ
ወእስከ ለዓለም ወእስከ ለዓለም ንጉሥ ውእተ። (2 ጊዜ)

32. ሊቀ መላእክት - ሊቀ መላእክት፥ (2 ጊዜ)
ገብርኤል ገብርኤል - ሊቀ መላእክት፥ (2 ጊዜ)
ኧኸ ገብርኤል ገብርኤል - ሊቀ መላእክት። (2 ጊዜ)

33. ሐመልማለ ወርቅ ሐመልማለ ወርቅ፥ (2 ጊዜ)
ሚካኤል ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ፥ (2 ጊዜ)
ኧኸ ሚካኤል ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ። (2 ጊዜ)

34. እግዝእትዬ ውስተ ምድረ ነኪር ትሄልዊ፥ (2 ጊዜ)
ገሊላ እትዊ (4 ጊዜ) ሀገረኪ ገሊላ እትዊ፥
ኧኸ ገሊላ እትዊ ሀገረኪ ገሊላ እትዊ።

3፤. እምነ እምነኒ፥ (4 ጊዜ)
በሰላም በሰላም ነይ ማርያም።
አምላከ ነነአ ነአ፥ (4 ጊዜ)
በሰላም በሰላም አምላክ ነአ። (2 ጊዜ)

36. ተዋህዶ ንጽሕት ቅድስት እምነታችን፥ (2 ጊዜ)
ኑሪ ለዘለዓለም ተከብረሽ በአምላካችን፥ |
ተከብረሽ በአምላካችን። | (2 ጊዜ)

37. ማርያም (2 ጊዜ) ድንግል ማርያም፥ (2 ጊዜ)
አማልጅን ከልጅሽ (2 ጊዜ) ከመድኃኔ ዓለም።
ኧኸ አመልጅን ከልጅሽ (2 ጊዜ) ከመድኃኔ ዓለም፥ | (2 ጊዜ)
አማልጅን ከልጅሽ (3 ጊዜ) ከመድኃኔ ዓለም። |

38. መንክረ ግርማ ኃይለ ልዑል ፀለላ፥ (2 ጊዜ)
አማን አማን መላእክት ይኬልልዋ። (2 ጊዜ)
በሚያስደቅን ግርማ የልዑል ኃይል ጋረዳት፥ (2 ጊዜ)
በእውነት በእውነት መላእክት አመሰገኑዋት። (2 ጊዜ)

39. ክንድህን ዘርጋ ይቅር በላት ኢትዮጵያን፥
ክንድህን ዘርጋ ደግፋት ኢትዮጵያን፥
የሠራዊት ጌታ አንተ ነህ ኃይላችን። (2 ጊዜ)

40. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረግልኝ ምን እከፍለዋለሁ÷ (2 ጊዜ)
ምስጋና ነው እንጂ (2 ጊዜ) ሌላ ምን እላለሁ።

41. ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ÷ (2 ጊዜ)
በክርስቶስ ጌታችን የዓለም ቤዛ። (2 ጊዜ)

42. በቤተልሔም ተወልደ (2 ጊዜ) አማኑኤል÷ (2 ጊዜ)
እምዘርዐ ዳዊት (4 ጊዜ) ተወልደ አማኑኤል። (2 ጊዜ)

43. በጐል ሰከበ በአዝዕርት ተጠብለለ÷ (2 ጊዜ)
ቤዛ ኩሉ ዓለም (2 ጊዜ) ዮም ተወልደ። (2 ጊዜ)
በበረት ተኛ በጨርቅ ተጠቀለለ÷ (2 ጊዜ)
የዓለም መድኃኒት (2 ጊዜ) ዛሬ ተወለደ። (2 ጊዜ)

44. መድኃኔ ዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ÷ (2 ጊዜ)
ደስ ይበለን (2 ጊዜ) እልል በሉ (2 ጊዜ) አዳነን በማይሻር ቃሉ።
(2 ጊዜ)
መድኃኔ ዓለም ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ÷ (2 ጊዜ)
በልደትህ (2 ጊዜ) ሕዝቦችህ (2 ጊዜ) ዳኑ በልደትህ። (2 ጊዜ)
መድኃኔ ዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ÷ (2 ጊዜ)
ደስ ይበለን (2 ጊዜ) እልልበሉ (2 ጊዜ) አዳነን በማይሻር ቃሉ።
(2 ጊዜ)

45. መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት÷
ተመስሎ (5 ጊዜ) በነደ እሳት።

46. ጥንትም የነበረ አሁንም ያለ ወደፊት የሚኖር÷ (2 ጊዜ)
ኃያል ጌተ ቸሩ ፈጣሪ ይመሰገን እግዚአብሐር። (4 ጊዜ)

47. እንዘ ይብሉ ይዜምሩ በልሳነ በኢያረምም÷ (2 ጊዜ)
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም። (2 ጊዜ)

48. አማን በበአማን አማን በአማን÷ (2 ጊዜ)
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም። (2 ጊዜ)

49. **የኃያላን ኃያል ኃያል፥ ልዑል እግዚአብሔር፥** (2 ጊዜ)
**ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በምድር፥**
**ታምራተ ብዙ በሰማይ** (3 ጊዜ) **በምድር።**
**ኧኸ**
**ታምራተ ብዙ በሰማይ በሰማይ በምድር፥**
**ታምራተ ብዙ በሰማይ** (3 ጊዜ) **በምድር።**

50. **ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ** (2 ጊዜ)
**ሶበ ሰቀልዋ ለእግዚእነ**
**እምድር አድለቅለቀት**
**ፀሐይ ሀ ፀሐይ ፀለመ።**

51. **አማን በአማን አማን በአማን፥** (2 ጊዜ)
**ተወልዳት እመብርሃን፥** (2 ጊዜ)
**ኧኸ፥ ተወልዳት እመብርሃን።**

52. **አማን በአማን፥** (2 ጊዜ)
**ተሰብሐ በደብረ ታቦር፥** (2 ጊዜ)
**ኧኸ ተሰብሐ በደብረ ታቦር።** (2 ጊዜ)

53. **ንግሥተ ሰማያት ወምድር ማርያም ድንግል፥**
**ተፈፀመ** (5 ጊዜ) **ማሕሌተ ጽጌ።**

54. **ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቁቅ፥** (2 ጊዜ)
**አይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥ ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥**
**ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥ ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥**
**ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ።**
**ኧኸ አይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥ ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥**
**ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ፥ ዐይኑ ዘርግብ ዐይኑ**
**ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ።**

55. **ፅላት ዘሙሴ ፅላት፥** (2 ጊዜ)
**ፅላት ዘሙሴ ፅላት ሕግወ ሥርዓት።**

ሙሴ ከፈጣሪው የተቀበላት፥
አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፈባት፥
ፅላት ዘሙሴ ፅላት።

56. ትንስዒ ፅዮን ተንዒ ፅዮን፥ (2 ጊዜ)
ፅዮን (2 ጊዜ) ልበሲ ኃይልኪ። (2 ጊዜ)
ኧኸ (3 ጊዜ)
ፅዮን (2 ጊዜ) ልበሲ ኃይልኪ። (2 ጊዜ)

57. መልአከ ሠላም ተናገራ፥ (2 ጊዜ)
ተፈስሂ ወይቤላ ብፅዕት።(2 ጊዜ)
ኧኸ ተፈስሂ ወይቤላ ብፅዕት። (2 ጊዜ)

የሠላም መልአክ አበሠራት፥ (2 ጊዜ)
ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ አላት። (2 ጊዜ)
ኧኸ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ አላት። (2 ጊዜ)